የፌስቡክ ትሩፋት

በፍቃዱ ዘ ኃይሉ

2009

መግቢያ

ፌስቡክ ላይ የምናጋራቸው ጽሑፎች ቆየት ብለን ስንመለከታቸው ብዙዎቹ ከንቱ እንቶ ፈንቶዎች ሲሆኑ ከፊሎቹ ደግሞ ትልቅ ቁምነገሮችን የያዙ ይሆናሉ፡፡ በተለይ እንደኔ ሥራዬ ብሎ በወቅታዊ እና ጠቅላላ ጉዳዮች ለዓመታት ፌስቡክ ላይ ለጻፈ ሰው ጽሑፎቹ መልሰው ማንነቱን ሲቀርፁት ማየት የተለመደ ነው፡፡ እንግዲህ ወደፊት "የሰውን ማንነት ለማወቅ ከፈለግክ የፌስቡክ ጽሑፎቹን ገርብ" የሚል አባባል እስኪመጣ ቢያንስ ይጠቅማሉ የምንላቸውን ጽሑፎች ሰብስቦ መጠረዙ አይከፋም - አንድም ራስን ለመታዘብ፣ አንድም ትሩፋቱን ለመቃመስ፡፡ ለዚህ ግብ ነው ይህንን ስብስብ ‹ሦስተኛ› የፌስቡክ ጽሑፎቼ ስብስብ አድርጌ በፒዲኤፍ ያዘጋጀሁት፡፡

ከዚህ በፊት ‹የፌስቡክ ትሩፋት› በሚል በፒዲኤፍ የጠረዝኳቸው ሁለት ስብስቦች በ2004 እና በ2005 የጻፍኳቸው ጽሑፎች ነበሩ፡፡ ከዚያ በፊትም በ2003 እና በ2004 የጻፍኳቸውን ጦማሮች፣ እንዲህ በተደራጀ መንገድ ባይሆንም በአንድ አንድ ብሎግ (ካታሎግ) አዘጋጅቼላቸው ነበር፡፡ የ2006ቱን ጽሑፎቼን ግን ሳልሰበስባቸው መንግሥት ቀደመኝ፤ ታሰርኩ፡፡ በ2007 ጥቅምት ወር ላይ ከተፈታሁ በኋላ ልክ እንደበፊቱ ባልተጋም ቀስበቀስ መጻፌን ቀጥያለሁ፡፡ ከዚያ በፊት የነበረኝን ሰብስቦ የማዘጋጀት ነገር ግን ቸል ብዬው ነበር፡፡ ቢሆንም ጽሑፎቼን ሰብስቦ የማስቀመጡ ልምድ መልካም ስለመሰለኝ የ2009 ዓመት መሰናበቻን አስታክኬ ሦስተኛ ጥራዝ አዘጋጅቼያለሁ፡፡

በሦስተኛው - የፌስቡክ ትሩፋት - ስብስቤ ከእስር ቤት ውስጥ ከላክኋቸው ጀምሮ ከወጣሁ በኋላ እስከ ጻፍኳቸው ድረስ እንዲያካትቱ አድርጌያለሁ፡፡ ሆኖም፣ በዚህ ስብስቤ የጻፍኳቸውን ሁሉ ማካተት አሰልቺ ሆኖ ስለታሰበኝ፣ በኔ ሚዛን የተሻሉትን ብቻ ሰድሬ አሰናድቻለሁ፡፡ ጠቅላላ ስብስቡን - *የጦማሪነት ማኒፌስቶዬ ኅሠሣ* - አድርጋችሁ እንድትወስዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡

ጽሑፎቹ እንዳያሰለቹ በማሰብ አልፎ አልፎ ፌስቡክ ላይ የማጋራቸውን ግጥሞቼን መሐል መሐል ላይ ሰግስጌያለሁ፡፡ ጽሑፎቼን (ጦማሮቼንም) ዘመድ እየፈለግኩላቸው በየፈርጁ ሰብስቤያቸዋለሁ፡፡ ሆኖም ከየጽሑፉ ርዕስ ግርጌ ለሕዝብ የተጋሩበትን ግዜ አስቀምጫለሁ፡፡ ሌላው ማሳሰብ ያለብኝ በቀሽም እንግሊዝኛ የጻፍኳቸውን ጥቂት ጽሑፎችም ማካተቴን ነው፡፡ ብዙዎቹን ብተዋቸውም አንዳንዶቹን ግን ለስብስቡ ውበት መቅረት የሌለባቸው ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

ጦማሪው

ማውጫ

አብዛኛው አቋማችን የሰውን ልጅ የምንረዳበት መንገድ ነፀብራቅ ነው! 4

፩ - ኢትዮጵያዊነት እና ዘውጌኛነት..6

Is Ethiopianism Re-examined or Replaced by Ethnopianism? 6

ኢትዮጵያ ያለ«ኢትዮጵያዊነት» ልትኖር አትችልምን? 8

"ዘውጌኝነት" እና "ዘውግ ዘለልነት" 16

Is OLF Dead or Alive?...24

የተዘለለው ምዕራፍ...30

"ጉንዳን እንኳ ሲሔድ ተሰልፎ ነው"..40

የመሐል አገር ሰው መልዕክት ለትግራይ ሰው!..45

"ወያኔ" vs "ሕወሓት" vs "ኢሕአዴግ" 48

"የትግራይ ሕዝብ እና ሕወሓት አንድ ናቸው/አይደሉም"!?.......................................50

የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት የተሻለ "ወዳጅ" አለው? 53

፪ - የትግል ስልት..57

"ጨዋ" ነዎት "ባለጌ"?..57

Are Revolutions Meant to be Betrayed? 75

Confession of the Ex-Revo...78

የ"ተቃራኒ" ወገን የትግል አጋርነት...83

ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት እስከ ማበሳጨት 87

፫ - አባታዊው ስርዓት እና ሴታዊነት 93

የፌሚኒዝም ሀሁ... 93

“ፆተኝነት” (sexism) ውስጤ ነው 100

የተዋሐደን ፆተኝነት 102

የቃላት ጥቃት ጠባሳው አይሽርም!.. 111

፬ - ምርቃት 114

ቋንቋችንን እንታዘበው 114

አብዛኛው አቋማችን
የሰውን ልጅ የምንረዳበት መንገድ
ነፀብራቅ ነው!

(ታኅሣሥ 9፣ 2006)

የሰው ልጆች በተፈጥሮ ጥሩ ናቸው ወይስ ክፉ? አንዳንዶች 'ጥሩ ናቸው ማድረግ የሚገባን በሥነ ምግባር ቀርፆ ማሳደግ፣ በመልካም መኮትኮት (nurturing) ብቻ ነው' ይላሉ፤ ሌሎች 'ሰዎች በተፈጥሮ አደገኞች ናቸው ስለዚህ በሕግና ደንቦች ተግባራቸውን መገደብ፣ የሚያጠፉን በመቅጣት ማስፈራራት ነው ያለን አማራጭ' ይላሉ። ጥቂቶች መሐል ላይ እውነት ይፈልጋሉ።

ስለሰው ልጆች በጥቅሉ የቱንም ዓይነት አመለካከት ቢኖረንም ቅሉ፥ ስለራሳችን ግን ያለን አመለካከት ግን 'ጥሩ ነኝ' የሚል ነው፤ 'የሠራሁት ስህተት እንኳን ቢኖር የምር ተሳስቼ ወይም በስሜታዊነት ተነሳስቼ የሠራሁት እንጂ ክፉ ሆኜ አይደለም' እንላለን። በዚህ መንገድ ግን ብዙ ጊዜ ሌሎችን መረዳት አንችልም። ሁላችንም የዚህ የአስተሳሰባችን ግዳይ (victim) ነን። የሰው ልጅን የምንረዳበት መንገድ ከማጀት እስከ አደባባይ ይከታተለናል።

ዴሞክራት ነን ወይስ ዲክታተር?

(በሰዎች መልካምነት እናምናለን ወይስ አናምንም?)

'ሰዎች በጥቅሉ ጥሩ ናቸው' ብሎ ከማያስብ ሰው (ማኅበረሰብ) ዴሞክራትነት መጠበቅ የዋሕነት ነው። ምክንያቱም ዴሞክራሲ ሰዎችን (ከተጠያቂነት የማያድን ቢሆንም) በነጻነት እንዲያስቡና እንዲወስኑ/እንዲተገብሩ የሚፈቅድ ፅንሰ-ሐሳብ ነው። ስለዚህ በዴሞክራቶች ምናብ ውስጥ ቀድሞ የሚመጣው 'መፍቀድ' የሚለው ቃል ነው፤ ከዚያ 'ተጠያቂነት'። በተቃራኒው ደግሞ በዲክታተርሺፕ ቀድሞ የሚመጣው ቃል 'መከልከል' ሲሆን ተከታዩ ደግሞ 'ቅጣት' ነው።

ዴክታተሮች 'እኔ ጥሩ ነኝ፤ ሌሎች ግን ችግር ፈጣሪዎች ናቸው። ስለዚህ አደገኝነታቸው ዓለምን እንዳያጠፋ መታደግ አለብኝ' በሚል አስተሳሰብ አሳሪ ስርዓት ይዘረጋሉ። ዴሞክራቶች 'ሰዎች ካልተሳሳቱ በቀር ለክፉ አይገዙም፤ የተለየ ሐሳብ ቢኖራቸው እንኳ ዓለማችን የተሻለች እንድትሆን አዲስ መንገድ እየታያቸው ሊሆን ስለሚችል እንደአማራጭ ሐሳባቸውን ከኔ ሐሳብ ዕኩል የሚያራምዱበት መንገድ ያስፈልጋቸዋል' በሚል ነጻ ስርዓት ይገነባሉ።

እንግዲህ፤ የዴሞክራትነታችንን ልክ ለማወቅ የሰውን ልጅ የምንረዳበትን መንገድ ማወቅ ሊኖርብን ነው።

(እንዳትሳሳቺ)

ቆንጆ ነሽ! ውበትሽ ከሩቅ ይጣራል፣
ዝነኛ ነሽ! ስላንቺ ባገር ይወራል፣
ባለፀጋ ነሽ! ገንዘብሽ አገር ያኖራል።
እኔም ለዛ ነው የወደድኩሽ፣
የኔ ‘ንድትሆኚ የለመንኩሽ።

ግን እንዳትሳሳቺ!
ቁንጅናሽን አጥቤ አልጠጣም፣
ዝናሽንም በልጬ አልወጣም፣
በአንቺ ገንዘብ ወጪ አላወጣም።

የኔ ዓላማ!
የቆንጆዎች ቆንጆ፣ የዝነኞች አውራ፣
የሀብታሞች ቁንጮ፣ ከኔ ጋራ ኖራ፣
ለራሴ ያለኝን፣ የመ-ፈለግ ምኞት
የረብነት ጉጉት፥ ከልቤ አኑራ፣
ነፍሴ እንድትኩራራ።

አስቢው!
አንቺን ያስወደደኝ፣
ለኔ ያለኝ ፍቅር፥ ትርጉም ተቀይሮ፣
በተመልካቾች ዓይን፣ ከገለባ ቀሎ
ይነገር ይሆናል፥ "አፈቀራት" ተብሎ፣
No!
No! No! No! No!

እንዳትሳሳቺ!
የራስ፣ የመውደዴ መለኪያ ነሽ አንቺ።

(ሚያዝያ 24፣ 2009)

፩ - ኢትዮጵያዊነት እና ዘውጌኛነት

Is
Ethiopianism Re-examined
or
Replaced by Ethnopianism?

(Saturday, February 15, 2014)

'Ethiopiawinet' is an Amharic term equivalent to 'Ethiopianism'. But, the context it is recently being discussed in social media, is very different from it has been used in English and historical scripts. The old Ethiopianism (as written in the scripts) is more theological thought than political, and pan-Africanist concept than Ethiopian nationalist. The debate now ranges from denying the existence of it (as a self-standing identity) to worshiping it (as the only thought to save Ethiopian unity). The former is mainly opinion of ethno-nationalists who have concerns that the term might be used as term pseudo-term used by Abyssinians. They think the so-called 'Ethiopianism' is not inclusive of all but is just an identity built on the cultures and religion of Ethiopian highlanders. I am guessing the debate ends with a new definition of what Ethiopianism is (should be). It seems Ethno-nationalism (which I would like to call in this piece Ethnopianism) is its biggest challenge.

Encyclopedia Britannica described Ethiopianism as "religious movement among sub-Saharan Africans that embodied the earliest stirrings toward religious and political freedom in the modern colonial period. The movement was initiated in the 1880s when South African mission workers began forming independent all-African churches, such as the Tembu tribal church (1884) and the Church of Africa (1889). An ex-Wesleyan minister, Mangena Mokone, was the first to use the term when he founded the Ethiopian Church (1892). Among the main causes of the movement were the frustrations felt by Africans who were denied advancement in the hierarchy of the mission churches and racial discontent encouraged by the colour bar. Other contributing factors were the desire for a more African and relevant Christianity, for the restoration of tribal life, and for political and cultural autonomy expressed in the slogan "Africa for the Africans" and also in the word Ethiopianism.

"The mystique of the term Ethiopianism derived from its occurrence in the Bible (where Ethiopia is also referred to as Kush, or Cush) and was enhanced

when the ancient independent Christian kingdom of Ethiopia defeated the Italians at Adwa in 1896."

It was Garvey who first demanded 'Africa for Africans'. A Study of Ethiopianism in Rastafarianism with a Focus on the Concept of Ethiopia as Zion (by Jennifer Skowera) stated that 'the man most responsible for bringing the ideals of Ethiopianism to Jamaica is Marcus Garvey. Barrett describes the man as ". . . the prophet of African redemption . . . [and through him] the spirit of Ethiopianism came into full blossom" (77).'

The term – Ethiopianism - was first coined in a desperate attempt of strengthening Africans and black people who were under colonization and slavery around the world. It is a huge ideal which conceived free and united Africa. That dream was big and isn't fulfilled yet.

Every sane African loves the idea of United Africa and even most pragmatic politicians want to come to it through regional integration of the east, of the west, of the north, of the south and of the center. As compared to this dream, it is difficult to grasp that how African countries are splitting into many for little differences. In east Africa alone, the number of independent countries is doubled within two decades.

These things happen because immature but accidentally influential politicians misunderstand systematic-inequality as inability to co-exist. In the process of states making and independence, some people were disproportionately favored. However, this doesn't mean that [due to historical injustices,] the favored and disfavored ones can't exist together, many a self-claimed freedom fighters come and plant hate among people. In this way, the dream of African Union walks two steps away as Africans walk to have it a step.

The case in Ethiopia isn't different. Ethiopia is a small Africa where state fails to bond its people beyond tribal differences.

Discussions on Ethiopianism (as in unity and pride) give more sense to other Africans than us. That's why we need to stop and realize that unity is not the enemy of equality. Unity isn't becoming one but untied for better. Perhaps, it is because we aren't united that dictatorship isn't gone.

ኢትዮጵያ ያለ«ኢትዮጵያዊነት» ልትኖር አትችልምን?

(ጳጉሜ 1፣ 2009)

በአዲስ አበባና ዙሪያዋ በጣም ተወዳጁ ኤፍኤም ሬዲዮ ሸገር ነው ቢባል የሚያጣላን አይመስለኝም። ሸገር መፈክሩ "ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር" የሚል ነው። አሁን ደግሞ ፖለቲከኞችም ይህንኑ መፈክር የንግግራቸው ማሳረጊያ ዓረፍተ ነገር እያደረጉት ነው። ሰማያዊ ፓርቲ ከመግለጫዎቹ ግርጌ “ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር” የሚል ዓረፍተ ነገር ያስቀምጣል። አዲሱ በእነሰይፉ ፋንታሁን እና ሠራዊት ፍቅሬ... የተከፈተው ኢትዮ ኤፍኤም ሬዲዮ "ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ" የሚል መፈክር ይዞ መጥቷል። በቅርብ ጊዜ ከተከፈቱት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች አንዱ - ጄቲቪ - መፈክሩ "ኢትዮጵያዊነት መልካምነት" የሚል ነው። "ኢትዮጵያ" የተሰኘው የቴዲ አፍሮ ዘፈን የአገር ውስጥ ሽያጭ ሪከርድ ሰብሯል። የሐበሻ ቢራ ማስታወቂያ ‘ኢትዮጵያዊነት’ የሚለውን ቃል ማዕከል ያደረገ እና ስለኢትዮጵያ ‘ገናና ታሪክ’ የሚያወሳ ዓይነት ነው። ሐበሻ ቢራ ገና ከመተዋወቁ ገበያው ደርቶለት የነበረውን ዋልያ ተቀናቅኖ ወጣ። ገበያው ከማስታወቂያው ነው ብለው ይመስላል፣ ሌሎቹም ቢራዎች ተቀራራቢ ይዘት ያላቸው ማስታወቂያዎችን ይዘው ብቅ-ብቅ ማለት ጀምረዋል። የቴሌቪዥን ትዕይንቶች፣ የግጥም ምሽቶች፣ ሌሎችም የጥበብ ሥራዎች ከመቼውም ግዜ በላይ ‘ኢትዮጵያዊነት’ን እያንቆለጳጰሱ ነው። በምላሹም ቀላል የማይባል ጭብጨባ ይቀበላሉ።

እነዚህ ሁሉ በተለምዶ "ኢትዮጵያዊነት" የሚባለው የአንድነት ኃይሉ ፖለቲካዊ ንቅናቄ ማኅበራዊ መገለጫዎች ይመስላሉ። ነገር ግን እነዚህ ይፋዊ መፈክሮች “ንቅናቄው እያደገ መምጣቱን ያረጋግጣሉ ወይስ፣ የዘውግ ፖለቲካ ንቅናቄ እና ዕድገት ድንጋጤ የፈጠረው ግብረ መልስ ይሆን?” የሚለውን ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ለዚህ ጥያቄ የግሌን መልስ በመስጠት ብቻ አይወሰንም። ይልቁንም፣ “ለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ተቆርቋሪ ነን የምንለው ሰዎች እውን ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ስሜት እና ፍላጎት ታማኝ ነን ወይ?” የሚለውንም ጥያቄ እግረ መንገዴን አንስቼ ለውይይት ክፍት ማድረግ ነው።

ግን፣ ግን ‘ኢትዮጵያዊነት’ ራሱ ምንድን ነው?

“ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር” ከሚለው መፈክር የምንረዳው ነገር ቢኖር ‘ኢትዮጵያዊነት’ መሠረቱ ኢትዮጵያ እንደ አንድ አገረ መንግሥት መቀጠል

አለባት የሚለውን ቁምነገር ያነገበ መሆኑን ብቻ ነው። "እንዴት?" ለሚለው ጥያቄ ግን አንድ ወጥ መልስ ያለው አይመስልም።

'ኢትዮጵያዊነት' ከሚለው ቃል በፊት 'ኢትዮጵያኒዝም' የሚለው የእንግሊዝኛ ፅኩያው-መሳይ በጥቅም ላይ ውሎ ነበር። የእኛው 'ኢትዮጵያዊነት' እና የአፈ እንግሊዞቹ 'ኢትዮጵያኒዝም' ግን ለየቅል ናቸው። 'ኢትዮጵያኒዝም' የተባለው ንቅናቄ የተጀመረው በ1880ዎቹ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ላይ 'ኢትዮጵያ' የሚለው መጠቀሱ፣ እና ኢትዮጵያ ውስጥ ቄሱም፣ ምዕመኑም ጥቁር መሆኑ ነበር መነሻቸው። በወቅቱ ክርስትና የነጩ ዓለም ጭቆና መሣሪያ ስለነበር ቄስ መሆን የሚችለው ነጭ እንጂ ጥቁር አልነበረም። ጥቁሮች ለመብታቸው መቆም ሲጀምሩ፣ ከፊሉ ክርስትናቸውን በእስልምና ሲተኩ፣ ከፊሎቹ ደግሞ 'ኢትዮጵያኒዝም' የሚል ንቅናቄ ፈጥረው፣ ጥቁር የሚሰብክበት 'የኢትዮጵያ' የተባሉ ቤተ ክርስትያኖችን አቋቋሙ። ከዚያም የአድዋ ድል መከተሉ ለጥቁሮቹ ንቅናቄ ኃይል ስለሰጠው ከምዕራብ አገራት (በተለይም ከአሜሪካ) ወደ አፍሪካ፣ ከሰሀራ በታች ያሉ አገራት ኢትዮጵያኒዝም ተስፋፍቶና ተሟሙቆ በአፓርታይድ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ብቻ 37ሺሕ ገደማ 'ኢትዮጲያኒስት' ቤተ ክርስቲያኖች ተፈጥረው ነበር።

በአገራችን ግን 'ኢትዮጵያዊነት' የሚለው ቃል አጠቃቀም ከዚህ ሃይማኖታዊ-ፖለቲካዊ ይዘቱ ይልቅ ፖለቲካዊ ብቻ ሆኖ ከመውጣቱም በላይ፣ አጠቃቀሙም መላውን የጥቁር ዘር ወክሎ ሳይሆን በኢትዮጵያ ድንበር የታጠሩትን ብቻ ወክሎ ነው። በዚያ ላይ ቃሉ በይፋ መደመጥ የጀመረው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት በብዛት የውጭ ሠራተኞችን ቀጥረው ያሠሩ የነበሩ የመንግሥት ተቋማትን በኢትዮጵያውያን መተካት እና ተቋማቱም ኢትዮጵያዊ እሴቶች እንዲይዙ ማድረግ ሲጀመር ነበር። ለምሳሌ የኢትዮጵያ አየር መንገድን 'ኢትዮጵያናይዝ' የማድረግ ንቅናቄ ሲጀመር ኢትዮጵያዊ ሠራተኞችን (ከአብራሪ፣ እስከ በረራ አስተናጋጅ፣ እስከ ቢሮ ሠራተኞች) በፈረንጆቹ ምትክ የማሰማራት፣ የአማርኛ ቋንቋን መጠቀም፣ የባሕል ልብሶችን እንደ ዩኒፎርም መጠቀም የንቅናቄው አንድ አካል ሆነው ወጥተዋል።

ይሁን እንጂ በወቅቱ የነበረው የ'ኢትዮጵያዊነት' ግንዛቤ "የአማራ እና የትግሬ"ን እሴቶች ብቻ ያቀፈ ተብሎ ተተችቷል። በዘር የሚተላለፈው፣ የገባር ስርዓት ላይ ሕዝባዊ አብዮት ሲነሳ፣ ስርዓቱ ከደረሱበት ውግዘቶች አንዱ ይህ የ'ኢትዮጵያዊነት' ግንባታ ሁሉንም ያማከለ አይደለም የሚለው ነበር። 'ኢትዮጵያዊነት' የተባለው ለሁሉም ዕኩል ገላጭ አልነበረም የሚለው ትችት እስካሁንም ድረስ ይደመጣል።

ቀድሞ በንጉሣዊው ስርዓት እና በገባር ስርዓቱ የከፉ ብሶቶች ታፍኖ የነበረው የአለመወከል ቅሬታ፣ ከአብዮቱ ጋር ሲፈነዳ፣ 'ኢትዮጵያዊነት' (በነባሩ አረዳድ) ይስማማቸው የነበሩ ሁሉ አገሪቷ ትፈርሳለች ብለው ደንግጠው ነበር። ከነዚህ ድንጉጦች ውስጥ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚል መፈክር ይዘው የመጡት ደርጎች ይገኙበታል። ደርጎች ኦሮሞውን ተፈሪ በንቲን እና ኤርትራዊውን አማን አንዶምን ርዕሰ ብሔር አድርገው የመረጡት በነባሩ 'ኢትዮጵያዊነት' ውክልና ሳይሰማቸው የቀሩትን ሕዝቦች (አለመወከሉ በባሕልና እሴት ብቻ ሳይሆን በአገር አመራርም (ፖለቲካ ሥልጣንም) ጭምር ነበርና) ጥያቄያቸውን በከፊል ለመመለስ እንደነበር ጓድ መንግሥቱ ሳይቀሩ (ከገነት ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ) አምነዋል። ነገር ግን የሥልጣን ሽኩቻው ከኢትዮጵያ ቀደመና ሁለቱም ሲወገዱ 'ኢትዮጵያዊነት' ሳይቀድም ቀረ። ይሁን እንጂ ኢሕአዴግ ሥልጣን እስከጨበጠ ድረስ 'ኢትዮጵያዊነት' ቢያንስ በመፈክር ደረጃ ይቀድም ነበር። በወቅቱ በዘውግ ለእድር እንኳ በይፋ መደራጀት አይፈቀድም።

ኢሕአዴግ ሲመጣ ግን ነባሩን የ'ኢትዮጵያዊነት' ትርክት ተጠያፊ ሌላ የአደባባይ ትርክት ይዞ ነው። ትርክቱ ቀድሞም በተቃዋሚዎች ቢቀነቀንም፣ ገዢ ትርክት እንዲሆን አልተፈቀደለትም ነበር። ኢሕአዴግ በአጭሩ ኢትዮጵያውያን በጋራ የሚያስተሳስረን ነገር ካለ ኢኮኖሚ ነው የሚል እምነት አንፀባርቋል። ለዚህም ይመስላል፣ ሕገ መንግሥቱ በመግቢያው "የየራሳችን አኩሪ ባሕል ያለን፣ የየራሳችን መልክአ ምድር አሰፋፈር የነበረን እና ያለን..." በማለት የዘውግ ቡድኖች የተለያየን መሆናችንን ካስታወሰን በኋላ፣ የሚያስተሳስረን ቁሳዊ ጥቅም ብቻ መሆኑን ሲነግረን ደግሞ "አንድ የጋራ ኢኮኖሚ ለመገንባት" የሚል ቃልኪዳን በብሔር ብሔረሰቦች መሐል መደረጉን ይነግረናል።

ኢሕአዴግ ይህንን አቋሙን ሲያራምድ ፖለቲካው ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ትልቅ ተፅዕኖ ማሳረፍ ከሚችሉ ወገኖች ጋር ትልቅ ግጭት ውስጥ ገብቷል። ይሁን እንጂ ገና በዘውግ የመደራጀት መብት ከመፈቀዱ በርካታ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ድርጅቶች ተፈጥረዋል። ከግንባር ቀደሞቹ የዘውግ ድርጅቶች ውስጥ፣ በ'ኢትዮጵያዊነት' አይደራደርም የሚባለው የአማራ ሕዝብን የሚወክለው 'መአሕድ' ብዙ አባላትን ይዞ መነሳቱ ደግሞ ትንግርት ነበር። (በርግጥ ለዚህ የተሰጠው ዋነኛው ትንታኔ ሕወሓት ጣቱን አማራ ላይ ቀስሮ "ትግሉ የተደረገው የብሔር እና መደብ ጭቆናን ለማስወገድ ነው" እያለ ሲደሰኩር ስለነበር ነው የሚል ነው።) ይህ በእንዲህ እያለ፣ መጀመሪያ፣ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በ1989 ከሻዕቢያ ጋር ጦርነት ለመግጠም ሲገደድ ሥሙን እንኳ ይጠየፈው የነበረውን 'ኢትዮጵያዊነት'ን በራሱ ዜማ ለመዘመር ተገደደ። ከዚያም፣ በ1997ቱ ምርጫ ወቅት 'ቅንጅት'

በከተሞች፣ እንዲሁም በአማራ እና በደቡብ ክልሎች ከፍተኛ ተቀባይነት ማግኘቱ እና 'ኢትዮጵያዊነት'ን በውስጠ ታዋቂነት ማንገቡ ተቀባይነት አስገኝቶለታል የሚል ትምህርት በመቅሰም፣ 'በአዲስ አበባ የኢሕአዴግ አባላትን ብሔር ሳይጠይቁ ከመመልመል' ጀምሮ 'የባንዲራ ቀን' ከማክበር፣ ያስተሳስረናል ያለውን 'የኢትዮጵያ ሕዳሴ'ን እስከማወጅ ደረሰ።

ነገር ግን በዘውግ መደራጀት፣ በዘውግ መፈራረጅ፣ በዘውግ መወጋገን እያደገ መጣ እንጂ አልቀነሰም። ይልቁንም አስተሳሰቡ እንደቀድሞው በገጠር ከመወሰን ይልቅ የወትሮው የከተሜው ዘውግ-ጥዩፍነትን በማሸነፍ በከተማም ፖለቲካዊ ርዕዮትነቱ ጨመረ። ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ የገዢው ፓርቲ ፖለቲካውን በዘውግ ለመዘወር መምረጥ ሲሆን፣ በምላሹ የሚቀነቀነው የአንድነት ኃይሉ 'ኢትዮጵያዊነት' ንቅናቄ ደግሞ ራሱን ታሪክ ናፋቂ፣ የሚሰነዘሩበትን ትችቶች የማይቀበል፣ ዘመኑን ያልዋጀ መስሎ መታየት እሳቱ ላይ ነዳጅ ጨምሯል። በዚህም ምክንያት 'ኢትዮጵያዊነት' አሁን የሚታወሰው በዘፈን፣ በእግር ኳስ እና አትሌቲክስ ሜዳ ብቻ የሚመስልበት ጊዜ መጣ። የዘውግ ንቅናቄዎች የበለጠ ተቀባይነት ማግኘት እውነታ ጋር የተጋፈጠው ድኅረ-ዘውጌ (post-ethnic) ነኝ ባዩ የከተሜ ልኂቅ በዚህ ተደናገጠ። በዚህ ድንጋጤም ይመስላል ቀድሞ (በተለይ በደርግ ጊዜ) በመንግሥት አስገዳጅነት ይቀነቀን የነበረው 'ኢትዮጵያዊነት' አሁን በኪነት ሰዎች፣ በሬዲዮና ቲቪ አቅራቢዎች (ወይም በመገናኛ ብዙኃኑ) የለትተለት አጀንዳነት የተተካው። ዛሬ ዛሬ ከመቼውም ግዜ በበለጠ 'ኢትዮጵያዊነት' የሚለው መፈክር ብዙ ጠቃሽ አግኝቷል። አሁንም ቢሆን ግን፣ የ'ዘውጌ ይቅደም' ንቅናቄ ከገጠር ከተማ በዘለቀበት ፍጥነት፣ 'የኢትዮጵያዊነት' መፈክር ከከተሜዎች አልፎ ብዙኃን ገጠሬዎች ጋር ደርሷል ማለት አይቻልም።

ከዚህ ሒደት መረዳት የምንችለው እና መጠየቅ ያለብን ጉዳዮች፣

1) ብዙኃኑ እና ገጠሬው ኢትዮጵያዊ ቀድሞም ይሁን አሁን 'ዘውጌ ይቅደም' ባይ መሆኑን(?)
2) 'ኢትዮጵያዊነት' የሚለው አስተሳሰብ መጀመሪያ መንግሥታዊ ፕሮጀክት፣ ከዚያ በኋላ ከተሜው ጋር ተቀባይነት ያገኘ ንቅናቄ መሆኑን(?)
3) ምናልባትም ከከተሞች ዴሞግራፊ መቀየር (ገጠር-ከተማ ፍልሰት) ጋር ተያይዞ፣ ወይም በፖለቲካ ጨዋታው መቀየር ምክንያት፣ ከተሜውም ዘውጌኝነትን እያራመደ መምጣቱ፣
4) 'ኢትዮጵያዊነት' ይቅደም የሚለው ንቅናቄ የጨመረ ቢመስልም፣ ለ'ዘውጌ ይቅደም' ንቅናቄ የተሰጠ ግብረ መልስ መሆኑን ነው።

ይህ ግን ‘ኢትዮጵያዊነት’ ምንድን ነው የሚለውን ጥያቄ አይመልስልንም፡፡ “‘ኢትዮጵያዊነት’ በዜግነት የሚገኝ ነገር ነው” ማለት የንቅናቄውን መንፈስ አለመረዳት ነው፡፡ ‘ኢትዮጵያዊነት’ ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ነገር ነው፡፡ በተለይ በብዙኃኑ እና በልኂቁ መካከል የተለያየ ነገር ነው፡፡ በብዙኃኑ ዓይን ‘ኢትዮጵያዊነት’ ሲባል የሚመጣባቸው ቀደምት የሥልጣኔ ምንጭነት (ለምሳሌ አኵሱም)፣ አኩሪ የትውፊት ባለቤትነት (ለምሳሌ ገዳ)፣ የጀግንነት እና ነጻነት ምሳሌ (ለምሳሌ አድዋ)፣ ሃይማኖታዊ ባለታሪክነት (ለምሳሌ የክርስትና እና የእስልምና ወደአገር ቤት አገባብ እንዲሁም በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መከባበራቸው) እና የመሳሰሉት ናቸው ትዝ የሚሏቸው፡፡ ይህ ግን እያደገ የመጣውን እና ልኂቃኑን የሚወክለውን ‘ኢትዮጵያዊነት’ የተሰኘ የፖለቲካ ንቅናቄ አይወክልም፡፡ ሆኖም ልኂቃኑ እነዚህን አንድ ሕዝብ የወል ሥነ ልቦና እንዲኖረው የሚያስፈልጉትን የኩራት ምንጮች መጠቃቀሳቸው አይቀርም፡፡ ነገር ግን የወል የኩራት ምንጮችን መጠቃቀሳቸው ብቻውን አሁን የሚያራምዱትን የፖለቲካ ንቅናቄ ሐቀኛ እና ትክክለኛ አያደርገውም፡፡

የንቅናቄው አራማጅ ነን የሚሉት ልኂቃንም ቢሆኑ ራሳቸው የተለያዩ መሆናቸው በራሱ ብያኔውን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ ቢሆንም በአንድ ባሕሪ ሁሉንም መግለጽ ይቻላል፡፡ ይኸውም ሁሉም ‘ዘውጌ ይቅደም’ ሳይሆን ‘ኢትዮጵያዊነት ይቅደም’ መባል ነው ያለበት ብለው ያምናሉ፡፡ ለምሳሌ በማንኛውም ሁኔታ የመገንጠል ጥያቄ መነሳት የለበትም ብለው ያምናሉ፡፡ ስለዚህ በነርሱ ብያኔ ‘ኢትዮጵያዊነት’ በፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚገኝ ‘ማንነት’ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እንደነዚህ ልኂቃን ከሆነ፣ አንድ የኢትዮጵውያን ፖለቲካ ስብስብ ከአገረ-መንግሥቱ የምናገኘው ጥቅም ስለሌለ (ወይም እየመጡ በሔዱ ፖለቲካዊ ስርዓቶች እንጨቆናለን፣ በሀብታችን ፍትሐዊ ተጠቃሚ አይደለንም፣ ወዘተ…) ስለዚህ ተገንጥለን የራሳችንን ዕድል እንወክላለን የሚል አቋም ማራመድ ሲጀምሩ ገና የ‘ኢትዮጵያዊነት’ ንቅናቄ ልኂቃን ‘ኢትዮጵያዊነት’ን ከነዚህ የፖለቲካ ስብስብ አባላት ይነጥቃሉ፡፡ የ‘ኢትዮጵያዊነት’ ነጠቃው አንዳንዴ “በቀደሙት ስርዓተ መንግሥታት እኔ የምኮራበትን ያክል አልኮራችሁም” በሚል ሊሆንም ይችላል፡፡

‘ዘውጌኝነት’ ለ‘ኢትዮጵያዊነት’ ዘመዱ ወይስ ባዳ?

የዘውግ ንቅናቄ ሥር የሰደደ "ኢትዮጵያዊ" አስተሳሰብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ማመን ከምንፈልገው በላይ በታሪካችን ውስጥ በወንዝ እና በቀዬ መቧደን የተለመደ ነበር፡፡ እርግጥ በዋነኝነት አገሪቷ በሁለት ዐብይ ቡድኖች ተከፍላ ነበር - የገዢና የተገዢ መደብ በሚል፡፡ ገዢዎቹ በእያንዳንዱ አካባቢ የመንገሥ ዕድል ያለው ልዑል ለማፍራት ከየአካባቢው ገዢ ወይም ጦረኛ

ልጅ ጋር በጋብቻ ይዛመዱ ነበር። ምክንያቱም የአካባቢው ተወላጅ ጋር ሳይዋለዱ በአካባቢው ቅቡልነት ማግኘት እንደማይችሉ ያውቁ ነበር። በጦር ጀግንነት መኳንንትነት ቢገኝም፣ ምስፍንና በውልደት ብቻ ነበር የሚገኘው። የቀድሞ ነገሥታት የጦር ጀግና ሲያምፅባቸው በጋብቻ ይዛመዱታል። ይህም ዘር እንደመሸለም ስለሆነ አመፅ ያስታግሳል። ይህ በዘር ላይ የነበረ ጥገኝነት የሚያስረዳን የኢትዮጵያ አገረ መንግሥት የተፈጠረው በዘውጌኛ አስተሳሰብ መሆኑን ነው። ሌላው ቀርቶ የቀድሞ ጸሐፍት እና ሊቃውንት ከሥማቸው ቀጥሎ "…ዘ ብሔረ ቡልጋ (ዘጌ)(ወዘተ)…" በሚል የትውልድ ቀበሌያቸውን መጥቀስ የተለመደ ነበር። የድሮው ዘውጌኝነት ከዛሬው ስርዓት ልዩነቱ አንድም የዘውጎቹ አረዳድ እና ባሕሪ ከዛሬው የሚለይ በመሆኑ (ማለትም በፊት ሸዋ፣ ጎጃም፣ አርሲ ወዘተ የነበሩት ዛሬ አማራ፣ ኦሮሞ… መባላቸው) እና፣ አንድም ደግሞ የዛሬው ስርዓት የዘውጌኝነቱን ችግር (define and rule እንዲሉ) እየተቸ በተግባር ግን ራሱን ከቀድሞው በበለጠ ያውም በሕግ የተወሰነ የዘውገኛ አደረጃጀት እና በአፈፃፀም ደግሞ የሚባባስ የዘውግ መድልዖ ውስጥ መዝፈቁ ነው።

ከኢትዮጵያ እና ከ'ኢትዮጵያዊነት' የቱ ይቀድማል?

ነገሥታቱ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አልፎ አልፎም ቢሆን ይጠቀሙበት እንደነበር ይነገራል። ይሁን እንጂ እስከ ዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ድረስ ጠንካራ ፖለቲካዊ ኅልውና የነበራት አቢሲኒያ ነበረች። አቢሲኒያ መሠረቷ ክርስትና የሆነች አገረ መንግሥት ነበረች። ከዛሬይቱ የደቡብ፣ እና የምሥራቅ ኢትዮጵያ ጋር የነበራት ግንኙነትም የጠነከረ አልነበረም። ደቡቡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን ወደሰሜን በፍልሰት፣ ሰሜኑ (አቢሲኒያው) በ19ኛው ክፍለ ዘመን በጦር በማስገበር ሲቀላቀሉ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ተፈጠረች። የዚህ ኢትዮጵያን በዛሬ መልክና ቁመቷ የመፍጠር የመጨረሻ ርምጃ የወሰዱት ዳግማዊ ምኒልክ ቢሆኑም፣ አገሪቱ በአዋጅ ኢትዮጵያ ተብላ የተጠራችው በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግዜ ነው። (እርግጥ ነው ዳግማዊ ምኒልክ "ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ" የሚል ሐረግ ማኅተማቸው ላይ ስለነበር ያኔም ኦፊሴላዊ መጠሪያ ነበር ብሎ መከራከር ይቻላል።) የኢትዮጵያ አገረ መንግሥት ከተፈጠረ በኋላ፣ ኢትዮጵያም ኦፊሴላዊ ሥሟ ከሆነ በኋላ ነው 'ኢትዮጵያዊነት' የሚለው ሐሳብ የተፈጠረው እንጂ በተቃራኒው አይደለም።

የኢትዮጵያ አገረ መንግሥት መሥራቾች አቢሲኒያውያን እንደመሆናቸው፣ ኢትዮጵያን ከደቡቡ እና ምሥራቅ ኢትዮጵያዊው የበለጠ መውደዳቸው አይገርምም። አሰባሳቢ ነው ከመባሉ በቀር ገና አግባቢ ትርጉም እና ተግባር ያልተገኘለት 'ኢትዮጵያዊነት'ም ቢሆን አቢሲኒያውያን በራሳቸው ስሜት እና

ግንዛቤ የፈጠሩት ንቅናቄ እንደመሆኑ ለነርሱ የበለጠ ቢስማማቸው አይገርምም። በተቃራኒው፣ የደቡብ እና የምሥራቅ ሕዝቦች ከአቢሲኒያውያን ተቃራኒ ስሜት ቢያንፀባርቁ ሊገርም አይገባም። ምንም እንኳ ብዙዎቹ የ'ኢትዮጵያዊነት' አራማጆች ከዚህ ውጪ አማራጭ የለም የሚል አቋም ቢያራምዱም፣ "'ኢትዮጵያዊነት' የተባለው ማንነት ወይም ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ሁሉንም ካላስማማ፣ ኢትዮጵያ ያለኢትዮጵያዊነት መኖር ትችላለች ወይስ አትኖርም?" የሚለው ጥያቄ መከተል ይኖርበታል።

ከ'ኢትዮጵያዊነት' እና ከኢትዮጵያውያን የቱን እንምረጥ?

አሁን 'ኢትዮጵያዊነት' "በልካችን አልተሰፋም፤ ወይ እንደገና በልካችን ይሰፋልን አልያም አውልቀን እንጥለዋለን" የሚሉ ኢትዮጵያውያን መጥተዋል። በሕግ 'ኢትዮጵያዊ' የተባሉ በሙሉ ይህ በተለምዶ 'ኢትዮጵያዊነት' የሚባለው የተለያዩ ፖለቲካዊ ትርጉም የሚሰጠው ማንነት እንዲስማቸው የሚያስገድድ የሕግም፣ የሞራልም ግዴታ የለም። በሌላ በኩል 'ኢትዮጵያዊነት' ይቅደም የሚሉትን 'ዘውጌ ይቅደም' ከሚሉት የማበላለጡ መነባንባዊ እምነትም ውኃ የሚያነሳ አይደለም። ይልቁንም አማራጭ የፖለቲካ መፍትሔ ይዞ መቅረብ የተሻለ ይመስላል። ምክንያቱም ዘመኑ 21ኛው ክፍለዘመን ነው። መንግሥት ወይም ብዙኃን ወይም ልኂቃን የፈለጉትን ነገር ያገኙት ላይ ሁሉ በዘላቂነት መጫን አይችሉም። የአንድ ግለሰብም ቢሆን ልዩነቱ የሌሎችን መሠረታዊ መብት እስካልጣሰ ድረስ ይከበርለታል።

ኢትዮጵያ አሁን ፌዴራላዊ ሆናለች። የ'ኢትዮጵያዊነት' አራማጆች የሚጠቁሙት ሦስት ዋና-ዋና መፍትሔዎች (ሀ) ፌዴራሊዝሙን አፍርሶ ማዋሐድ፣ (ለ) የዘውግ ፌዴራሊዝሙን አፍርሶ በመልክአ ምድር ደግሞ ማዋቀር፣ (ሐ) ፌዴራሊዝሙን እንዳለ በማኖር የክልሎችን ሥልጣን (በተለይ የመገንጠል መብትን) መቀነስ ናቸው። የትኛውንም አማራጭ መፍትሔ መትከል ሕወሓት/ኢሕአዴግን ታግሎ ከመጣል በላይ ከባድ ነው። ምክንያቱም መፍትሔው የሕዝብ ይሁንታን ማግኘት አለበት። በኢትዮጵያ ታሪክ እንደተለመደው የ'ኢትዮጵያዊነት' ንቅናቄ አራማጆችም ይሁኑ የትኞቹም ከዚህ በፊት የታዩት ኃይሎች "ሁሉም ሕዝቦች ያቀረብነውን መፍትሔ ስለሚበጃቸው መቀበል አለባቸው" ባይ ቢሆኑም ሳይፈተኑ ተቀባይነት የሚያገኙበት ጀምበር ጠልቋል።

'ኢትዮጵያዊነት' ለሶማሌ ተወላጆች፣ ለጋምቤላ ተወላጆች፣ ለአዲስ አበቤዎች እና ለሁሉም ዕኩል ስሜት፣ ዕኩል ዕድል እና ዕኩል ጥቅም እንዲሰጥ የሚያስችለው ፖለቲካዊ መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል። በባሕል፣ በመልክአ

ምድር፣ በተፈጥሮ ሀብት፣ በታሪክ የተለያየ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከላይ የጠቀስነው ‘ኢትዮጵያዊነት’ አብረው እንዲዘልቁ አይጋብዛቸውም፡፡ ሁነኛው መፍትሔ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ምቾት ሲባል፣ ‘ኢትዮጵያዊነት’ የዜግነት መብቶችን በማክበር መርሕ ላይ እንዲመሠረት ማድረግ ነው፡፡ ይህ መርሕ መንግሥትና ሕዝብ፣ እንዲሁም አንዱ ወገን ከሌላው በጠመንጃ ቁራኛ በሚጠባበቁበት አፍሪካ ውስጥ ብቸኛው ልዩነትን አቻቻይ ተስፋ ሰጪ መርሕ ነው፡፡ የዜግነት መብቶችን ሙሉ በሙሉ ማክበር እና ማስከበር ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ማኅበራዊ ፍትሕን ያመጣል፡፡ ፍትሕ ካለ ነጻነት፣ ዕኩልነት እና ወዳጅነትም ይኖራሉ፡፡

"ዘውጌኝነት" እና "ዘውግ ዘለልነት"

(ሰኔ 21፣ 2009)

ለብዙዎቹ ችግሮቻችን ፍቱን መድኃኒት አድርጌ የምወስደው፣ ጉዳዩን በዘመን ቁመት እና በዓለም ሕዝቦች ታሪክ አግድም መመልከት ነው። ዓለም በበቂ ሁኔታ የምንማርባቸው ስኬቶች እና ውድቀቶች አሏት። ዘውጌኝነት፣ ብሔርተኝነት እና ዜግነት የመሳሰሉትም የብቻችን ጉዳዮች አይደሉም። ዓለም በየፈርጁ የዳከረችበት እና እየዳከረችበት ያለ ችግር ነው። ስለዚህ ጥያቄውን በቅጡ ለማበጃጀትም ይሁን፣ አዋጭ መልስ ለመፈለግ ከሰው ልጆች እንደአንድ የሚያደርገንን ታሪክ የምናውቀውን ያክል ማሰስ ያስፈልጋል። ይህን ከጠቆምኩ በኋላ ወደ የበኩሌን ለመሞከር ወደ አጀንዳዬ እዘልቃለሁ።

የዘውግ ብሔርተኝነት ምንድን ነው?

የዘውግ ብሔርተኝነት (ethnonationalism) የአንድ ዘውግ (ethnic) ቡድን ነጻ አገር እንዲመሠርት ወይም ከመገንጠል ወዲህ ያለውን የራሱን ዕድል በራሱ እንዲወስን ለማስቻል የሚደረግ ፖለቲካዊ ንቅናቄ ነው።

የዘውግ ማንነት በኢትዮጵያ ልማዳዊ አሠራር በወላጆች ማንነት ነው የሚወሰነው። እናትና አባታቸው ከተለያዩ ዘውጎች የተወለዱ ዜጎች በተለምዶ የአባታቸውን የዘውግ ሐረግ ነው የሚወርሱት። ዜጎች በአንድ ክልል ተወልደው፣ የአካባቢውን ቋንቋ፣ ባሕልና ወግ አውቀው ቢያድጉም ከአካባቢው ዘውግ የተለየ ዘውግ ካላቸው ወላጆች ከተወለዱ የአካባቢው ዘውግ አላቸው አይባልም። ማለትም፣ ለምሳሌ በኦሮሚያ ከአማራ ልጆች ተወልደው ያደጉ ልጆች በዘውግ ብሔርተኞች እንደኦሮሞ አይቆጠሩም። በሕግ የመምረጥ እና መመረጥ መብት ቢኖራቸውም በልማድ ተቀባይነት የማግኘት ዕድላቸው ግን አነስተኛ ነው። ነገሩን ይብስ ውስብስብ የሚያደርገው ደግሞ በሌሎች ማኅበረሰቦች መሐል የሚያድጉ ልጆች ከአደጉበት ማኅበረሰብ ይልቅ ዘውጋቸውን ከወላጆቻቸው በደም ለመውረስ የመፈለጋቸው ልምድ ነው።

የዘውግ ብሔርተኝነት ንቅናቄዎች ከዘር (race) ንቅናቄዎች ጋር በትይዩ ሊታዩ ይችላሉ። ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ያሉ ዘውጎች በፊት ቅርፅና የቆዳ ቀለም ሊገለጽ የሚችል ልዩነት ባይኖራቸውም (የዘር ልዩነት ባይኖርም)፣ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ግን ተቀራራቢነት አላቸው። ሁለቱም "በማንነታችን ምክንያት የመብት እና ዕድል አድልዎ ይደረግብናል" ይላሉ።

የሚገጥሟቸውም ተግዳሮቶችም ተቀራራቢነት አላቸው፤ ለምሳሌ ያክል 'Black Lives Matter' (የጥቁር ነፍስም ዋጋ አለው) በሚለው የጥቁሮች ንቅናቄ ላይ 'All Lives Matter' (የሁሉም ሰው ነፍስ ዋጋ አለው) ነው መባል ያለበት እንደሚሉት ሁሉ፣ በኛም አገር ለምሳሌ 'Because I am Oromo' (ኦሮሞ ስለሆንኩ) እንዲህ ደረሰብኝ በሚለው ፈንታ 'Because I am Ethiopian' (ኢትዮጵያዊ በመሆኔ) ነው መባል ያለበት የሚል ትችት ይቀርብባቸዋል።

አሁን 'ኢትዮጵያዊነት' ምንድን ነው?

'ኢትዮጵያዊነት' (‹ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት›) የሚባለው አሁን የወል፣ አስማሚ ትርጉም የለውም። ሆኖም 'ብሔር' የሚለው የግዕዝ ቃል 'አገር' የሚል ትርጉም አለው በሚል "ብሔሬ ኢትዮጵያ ነው" በማለት የዘውግ ማንነታቸው በኢትዮጵያዊነት መግለጽ የሚፈልጉ አሉ። በዚያ ላይ ቤተሰቦቻቸው ከሁለት ዘውግ የተወለዱ ሰዎች ራሳቸውን በኢትዮጵያዊነት ለመግለጽ መፈለጋቸው ኢትዮጵያዊነትን እንደ አቃፊ ወይም ደግሞ አማራጭ ማንነት መቀበላቸውን ያሳያል።

ይሁን እንጂ ከነዚህ ውጪ ኢትዮጵያዊነትን እንደዜግነት ሳይሆን ራሱን እንደቻለ ማንነት የሚመለከቱት በተለይ አዲስ አበቤዎች፣ በርካታ የአማራ እና በደቡብ ክልል የሚገኙ ብሔረሰቦች በተለይም ጉራጌዎች ናቸው። ከነዚህ ውጪ ያሉት ቀዳሚ ምርጫቸው አለመሆኑ የሚያሳየው 'ኢትዮጵያዊነት'ን እንደማንነት የማይቆጥሩት ዜጎች መኖራቸውን ነው።

ኢትዮጵያዊነት ከሉላዊነት (globalization) ባሕርያት ጋር የሚመሳሰልባቸውም ነገሮች አሉ። ሉላዊነት በኃያላን አገራት በተለይም በአሜሪካ የኢኮኖሚ መሪነት የተመሠረተ የዓለም አገራት ትስስር ነው። ኢትዮጵያዊነትም ከሰሜን ኢትዮጵያ በአቢሲኒያ ተመሥርቶ ወደደቡብ እና ምሥራቅ የተስፋፋ ፖለቲካዊ ንቅናቄ ነው። ሉላዊነት ኃያላኑ አገራት የኢኮኖሚ እና ቴክኖሎጂ የበላይነታቸውን ተጠቅመው የራሳቸውን ማንነት በአቅመ ደካሞቹ አገራት ላይ የሚጭኑበት (hegemonic) ግንኙነት ነው ይላሉ፤ ብዙዎች ሉላዊነትን ከአሜሪካዊነት ጋር ዕኩል ያደርጉታል። በተመሳሳይ፣ ቀላል የማይባሉ ኢትዮጵያውያንም ኢትዮጵያዊነትን ከአቢሲኒያዊነት ጋር ዕኩል ያደርጉታል። አቢሲኒያውያን የአገር መሥራችነት እና ቀዳሚ የመሣሪያ ማግኘት ዕድላቸውን ተጠቅመው የሰሜኑ ሕዝብ ከሌላው የተሻለ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ስርዓት ዘርግተዋል በማለት።

የዘውግ ብሔርተኝነት እና የአሁኑ 'ኢትዮጵያዊነት' - አንድነት እና ልዩነት

ሁለቱም ፖለቲካዊ ንቅናቄዎች ናቸው። ዘውገኝነት በቋንቋ፣ ባሕል እና ወግ መመሳሰል (አንድ ዓይነትነት /homogeneity/ አላልኩም) ወይም የማይመስሉትን በማግለል ላይ የተመሠረተ ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊነት ግን የወደዱትንም የጠሉትንም በጠቅላይነት ላይ የተመሠረተ ነው። የዘውግ ብሔርተኞች ለዘውግ ጥቅም የግዛት አንድነትን አሳልፈው ሊሰጡ ይችላሉ፤ የኢትዮጵያዊነት አራማጆች ደግሞ የግዛት አንድነትን ለማስጠበቅ የዘውጎች ቡድን ጥቅም አሳልፈው ሊሰጡ ይችላሉ።

በተቀባይነት ደረጃ የዘውግ ብሔርተኝነት ከኢትዮጵያዊነት ዕኩል ወዳጅም፣ ጠላትም አለው። ነገር ግን በተለይ ብዙኃን ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት ገጠር አካባቢ ዜጎች ራሳቸውን በወንዛቸው ወይም በዘውጋቸው መጥራት ይመርጣሉ። የዘውግ ብሔርተኝነትን አምርረው የሚቃወሙት የኢትዮጵያዊነት አራማጆችም ለዘውግ መወገንን የሚጠየፉት ምንጩ ከአቢሲኒያ ያልሆነ ወግ አጥባቂነት ሲመለከቱ ነው በሚል ይተቻሉ። በሌላ አነጋገር ‹ኢትዮጵያዊነት› የሚመርጠው (ወይም የሚጠየፈው) እና የማይመርጠው (ወይም የማይጠየፈው) ዓይነት የዘውግ ወገንተኝነት አለ ማለት ይቻላል።

እርግጥ ነው፣ የዘውግ ብሔርተኞች እና የኢትዮጵያዊነት አራማጆች የሚያመሳስላቸው አንድ ትልቅ ቋንቋ አለ፤ ይኸውም "ዘውጌኛነት" ራሱ ነው። ምንም እንኳን 'ኢትዮጵያዊነት'ን ብቻ የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ልሒቃን ኅብረብሔራዊነትን ነው የምንሰብከው ቢሉም ኢትዮጵያውያንን እንደዘውግ ስብስብ እንጂ ከዘውግ ፍልስፍና አፈንግጠው በተለየ ርዕዮተ ዓለም እንደ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ አይመለከቷቸውም። (ወይም በአንዳርጋቸው ፅጌ አጠራራር "ዘውግ ዘለል" አተያይ የላቸውም።) ለዚህም ይመስላል ሁሉንም የዘውግ ቡድኖች ማሸነፍ የሚችል "ከዘውጌኛነት" የተሻገረ ስኬታማ የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር ያልተቻለው። የገዢው ፓርቲ ግንባር በኅብረብሔራዊ ፓርቲነት በአዲስ አበባ ሲንቀሳቀስ፣ ከአዲስ አበባ ውጪ ግን የብሔር ፓርቲ ሆኖ ነው የሚንቀሳቀሰው። ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቢሆኑ የዘውጎቹ፣ በየአካባቢያቸው ተቀባይነት ሲያገኙ፤ ኅብረብሔራዊ ነን የሚሉት አብዛኛው ተቀባይነታቸው በከተማ እንዲሁም በአማራ እና በደቡብ ክልል ነው። ስለዚህ ሁሉንም የሚያስማማ ብሔራዊ ንቅናቄ ከዬት ይምጣ?

"ረዥሙ አብዮት"

ንዑስ ርዕሱን የተዋስኩት "The Long Revolution" ከሚለው የእንግሊዛዊው ሬይመንድ ዊሊያምስ መጽሐፍ ነው። ሐሳቡ ዓለማችን ረዥም እና

የማያቋርጥ የለውጥ ጉዞ ላይ መሆኗን የሚተርክ ነው። ኢትዮጵያም የዚሁ የሰው ልጅ ከድቅድቅ ድንቁርና ወደ ዕውቀት ብርሀን የሚያደርገው ጉዞ ውስጥ የራሷ ድርሻ አላት። ጥንታዊ ሥልጣኔዎቻችን እና ዕድሜ ጠገብ ትውፊቶቻችን የዚህ ረዥም ጉዞ አካል ናቸው። ይሁን እንጂ ፈጥነን፣ ከአሸናፊው የዓለም ክፍል ዕኩል መራመድ ባለመቻላችን እና ራሳችንን ባለማጣጣማችን ምክንያት ኋላ ቀር ሆነናል። በተለይም በዕድሜ ከኛ ዕኩል እና የዘገየ ሥልጣኔ ባለቤት የሆኑ አገራት ነገሥታቱ የሕዝቦቻቸውን ነጻነት ባከበሩበት ፍጥነት የኛዎቹ ባለማክበራቸው ምክንያት (እንግሊዝ በ1215 ነው ለመጀመሪያ ግዜ የንጉሦቿን ሥልጣን የሚገድበውን 'ማግና ካርታ' ያወጀችው።) እና አድሎአዊ አሠራሮችን በግዜ ባለመቅረፋቸው አገራችን የሚያፈቅሯት ብቻ ሳይሆን የሚጠሏትንም ዜጎቿን አቅፋ እንድትኖር አስገድዷታል።

የረዥሙ የሰው ዘር የነጻነት ጉዞ ዓላማ ደግሞ ዜጎች አገራቸውን እየጠሏትም ቢሆን መብትና ነጻነታቸውን እንድታከብርላቸው እና እንድታስከብርላቸው ማድረግ ነው። ይህ የሚሆንበት ሁለት ምክንያት አለ። አንደኛው፣ አገረ-መንግሥታት የተፈጠሩት በሕዝብና መንግሥት ውል ነው። የውሉ ሐተታ ደግሞ መንግሥታት የዜጎችን መብት፣ ነጻነትና ደኅንነት ይጠብቃሉ፤ በምላሹ ከዜጎች ምንዳ ይሰፈርላቸዋል። ይህ ውለታ የማይሻር ነው። ሁለተኛው ምክንያት፣ አገራት ለዜጎቻቸው ነጻነት ይኖራሉ እንጂ፣ ዜጎች ለአገሮቻቸው ሕልውና ነጻነታቸውን አይገብሩም። ነጻነት የሰው ዘር የመጨረሻ ግብ ነው።

የዓለምም ይሁን የአገራችን ታሪክ የሚያረጋግጥልን ፍጥነቱ ከቦታ ቦታ ይለያይ እንጂ የሰው ልጅ ወደነጻነቱ የሚያደርገው ጉዞ ስኬታማ ነው። በዓለማችን መንግሥታት በዜጎቻቸው ላይ የሚያደርሱት ጭቆና፣ በጦርነት የሚያልቁ ሕዝቦች ቁጥር፣ በማንነት የመገለል መጠን ከመቶ ዓመታት በፊት ካለው ዛሬ በጣም የተሻለ ነው። ይህ ተስፋ ሰጪ የሰው ልጅ የነጻነት ጉዞ ድል እያስመዘገበ እዚህ የደረሰው እያንዳንዱ (የዘውግም ይሁን ዘውግ ዘለል) ትግል ውጤት ስላመጣ ነው። አሁን በኢትዮጵያ የሚደረገው ትግል፣ ውጤቱ የሚወሰነው የኢትዮጵያ አገረ መንግሥት ለዜጎቿ ነጻነትን ለማቀናጀት ባላት ፈቃደኛነት ልክ ነው። ይህችን ለዜጎቿ ነጻነት የተመቸች አገር የፈጠርን እንደሁ የታሪክ ባለቤቶቹ (እና ተመስጋኞቹ) በኅብረብሔራዊነት የግዛት አንድነቷን ያስጠበቁት ብቻ ሳይሆኑ፣ አድሎና ማግለሏን የተቃወሙት እና ስርዓተ ፍልስፍናዋን የሚያስቀይሯትም ዘውገኞች ጭምርናቸው።

የነገ 'ኢትዮጵያዊነት' ምን ዓይነት ይሁን?

ቀደም ብለን በተመለከትናቸው የዘውጌኝነት እና የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት ንቅናቄዎች ውስጥ ያልተስተዋለው፣ ሁለቱም በተለያየ መንገድ የሰው ልጅ ረዥም የነጻነት ተልዕኮ አካል መሆናቸው ነው:: ስለዚህ፣ በገለልተኛ ዓይኖች፣ እንደተቀናቃኝ ሳይሆን ተመጋጋቢ ወይም ሚዛን ጠባቂ ንቅናቄዎች መቆጠር ይኖርባቸው ነበር:: እርግጥ ነው ሁለቱም ብሔርተኝነቶች "ዘውግ ዘለል" ባለመሆናቸው አንዳቸው ሌላኛቸውን ዒላማ በማድረግ ብቻ ነው ለማበብ የሚሞክሩት:: ይህ ተመጋጋቢ እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል:: የንቅናቄዎቹ መሪ ልኂቃን አንዱን የሌላኛው ጠላት በማድረግ የደጋፊና ተከታዮቻቸውን ቁጥር በመነጣጠቅ ስልተ አካሔድ በቁጥር ለመበርከት ይሞክራሉ::

በደጋግ ቃላት አሽሞንሙነን፣ ሁላችንም የምንስማማበት 'ኢትዮጵያዊነት' የምንለውን የምር መፍጠር ካስፈለገን ግን የእስከዛሬውን የሁለቱንም ወገን ዘውጌኛ ፍልስፍናችንን መከለስ ይኖርብናል:: 'ኢትዮጵያዊነት' እንደስከዛሬው በዘውግ/ብሔር ማንነት ሳይሆን በዜግነት ብሔርተኝነት (civic nationalism) መቃኘት አለበት::

'የዜግነት ብሔርተኝነት' የምንለው የሚፈጠረው የፓስፖርት ዜግነታችን ለወጉ ያክል 'ኢትዮጵያዊ' ስለሚል ብቻ አይደለም:: የዜግነት ብሔርተኝነት በዘር/ማንነት ላይ የተመሠረተ ማግለል የሌለበት ስርዓተ ማኅበር ነው:: "የብሔርተኝነቱ የመርሕ ዋልታዎችም ነጻነት፣ መቻቻል፣ ዕኩልነት እና ግለሰባዊ ነጻነት ናቸው::"

"'የዜግነት ብሔርተኝነት' በቋንቋ፣ ወይም በባሕል አይገለጽም:: ይልቁንም በፖለቲካዊ ተቋማቱ እና ዜጎች በተስማሙበት እንዲሁም ተቋማቱ በቆሙበት መርሖዎች ነው የሚገለጸው:: የዚህ ብሔርተኝነት አራማጆች እሴታቸውን ለመጋራት በራቸው ለሁሉም ክፍት ነው::" (Anna Stilz, 2009)

ይህ ዓይነቱ ብሔርተኝነት እንዴት ሊመጣ ይችላል?

የዜግነት ብሔርተኝነት ባሕርያት፦

- ☞ ዜጎቹን የሚያስማማ ሕገ መንግሥትና ሕግጋት እንዲሁም የሕግ የበላይነት ያለው፣
- ☞ ማንኛውም ሰው (የየትኛውም ዘውግ ተወላጅ) ሕግጋቱን በመቀበሉ ብቻ የስርዓተ ማኅበሩ አባል የመሆን ዕድል የሚሰጠው፣

- ☞ መንግሥቱ ብዝኃነትን በሚያስተናግድ መልኩ የተዋቀረ፣
- ☞ የስርዓተ ማኅበሩ አስኳል ግለሰቡ የሆነ ነው።

ይህን መሰል ስርዓተ ማኅበር ለመገንባት መንግሥትን መቀየር ብቻ ሳይሆን ዜጎችንም ማዘጋጀት፣ ማብቃት ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ በቤተ ዘመዳዊነት ስሜት በገዢ መደቦች በተፈፀሙ ታሪካዊ በደሎች እና መድሎዎች የተፈጠሩ ቁርሾዎችን እና ታሪካዊ አረዳዶችን ማስተካከል ያስፈልጋል። ለዚህም የሚከተሉት ላይ መሥራት ይገባል፦

1ኛ) ትምህርት

የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ መሐይምነት ነው - የግለሰብ እንዲሁም የማኅበረሰብ መሐይምነት። በተግባር የተደገፈ፣ ዓለምን በማወቅ ላይ የተመሠረተ ስርዓተ ትምህርት ዓይናችንን ይገልጥልናል። ነገር ግን ትምህርት በመደበኛው መሥመር ብቻ ሳይሆን በሲቪል ማኅበረሰቦች የማንቃት (awareness) ሥራ ወደ ማኅበረሰቦች የሚሰርፅ ነገር መሆኑም የማይታበል ሐቅ ነው። ከሲቪል ማኅበረሰቦች ጎን ለጎን መገናኛ ብዙኃንም የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ናቸው። መገናኛ ብዙኃን ዓላማቸው ለሕዝብ መረጃ መስጠት፣ ማስተማር እና ማዝናናት ነው።

ስለሆነም ዜጎችን በዜግነት ብሔርተኝነት ለማነጽ መደበኛ ትምህርት ቤቶች፣ ሲቪል ማኅበረሰቦች እና መገናኛ ብዙኃን በነጻነት እንዲያብቡ ማድረግ ያስፈልጋል።

2ኛ) ዴሞክራሲ

ዴሞክራሲን ከሌሎች ስርዓቶች ሁሉ የተሻለ የሚያደርገው "ሕዝባዊ ተሳትፎን" መፍቀዱ ነው። በተለይ በአፍሪካ እና በኢትዮጵያ በሥሙ ዜጎች እንደሚጭበረበሩበት ሳይሆን፣ በእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት፣ ሕዝቦች በምርጫ ብቻ ሳይሆን በምርጫዎች መካከል የሚሳተፉበት ዕድል ይሰጣቸዋል። በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሕግጋት እንዲወጡ፣ መንግሥት ከተለያዩ ማኅበረሰብ ክፍሎች በወጡ ተወካዮች እንዲመሠረት፣ የብዙኃን አመራር፣ የድሀጣን መብት እንዲከበር፣ ወዘተ… ዋስትና ይሰጣል። ስለሆነም፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባት ለሲቪክ ብሔርተኝነት ግንባታ ቁልፍ ሚና ይጫወታል።

3ኛ) ብልፅግና

የዓለማችንንም ይሁን የአገራችንን ነጻነትና ኅብረት በማፅናት በኩል የሀብት ማፍራት እና በፍትሐዊነት የማከፋፈል ጉዳይ እምብዛም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የሚገባውን ትኩረት የተሰጠው አይመስለኝም። የጉራጌ ማኅበረሰብን መመልከት ለዚህ ጉዳይ ጠቃሚ ነው። ጉራጌዎች በኢትዮጵያ ሁሉም አካባቢዎች በመሰራጨት ሀብት ያፈራሉ፣ ለዚህም ይመስላል ብዙ የጉራጌ ተወላጆች ራሳቸውን በዘውግ ከመግለጽ በተጨማሪ ከነባሩ የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት ጋር ብዙም ሲጋጩ የማይታዩት። ‹የዜግነት ብሔርተኝነት› ግለሰቡን የስርዓቱ ማዕከል ያደርጋል እንዳልነውም፣ ጉራጌዎች በሌሎች የዘውግ ስብስቦች መሐል ግለሰባዊነት በአኗኗር ዘዬአቸው ይከተላሉ። ይህ ግን ባሕላዊ እሴቶቻቸውን አላዳከመባቸውም። እንዲያውም ከቁጥራቸው ማነስ በተቃራኒ ባሕላዊ እሴቶቻቸው (ለምሳሌ ምግባቸው እና ጭፈራቸው) የኢትዮጵያ ታዋቂ እሴቶች ዝርዝር ውስጥ ተካቷል። ይህ ስኬት በዘውግ ቡድኖች መካከል ግጭት ሳይፈጥሩ የዜግነት ብሔርተኝነትን እንዴት ማምጣት እንደሚቻል ያሳያል።

የነጻ ገበያ እና የሀብት ማፍራት ነጻነቶች ለዜጎች በተረጋገጡ ቁጥር የአገራችን ሕልውና እየፀና እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ያለው የዘውግ አጥር በፈቃደኝነት እየተሰበረ እና በጋራ ተጠቃሚነት ስሜት መስተጋብራቸው - ቀደም ብለን በጠቃቀስናቸው ሕጋዊነት፣ መቻቻል፣ ዕኩልነት እና ግለሰባዊ ነጻነት - የተመሠረተ እና ጠንካራ (ጤናማ) ይሆናል።

«ለራሴ ነገርኩት»

"ጥላኝ" ብላኝ ጥላኝ በሔደች፥
ይኸው በስንት ዓመቴ፣
እሰይ ተሳካ ዛሬ፥ የእልፍ ዓመታት ጥረቴ።

በሌላ አመለ ሸጋ፥ ቆንጅዬ ለጋ ቀይሬ፣
ልጠላት ሞክሬ ነበር፥ ልተፋት ከልቤ አንቅሬ፤
ምትኮቿ ክፋታቸው፣
እሷን ማስናፈቃቸው።

ዓለም በቃችኝ በማለት፥ በልቤ ገዳም መን:ኜ፣
ልዘነጋት ሞክሬያለሁ፥ ለራሴ ዋጋ ተምኜ፤
የልቤ ገዳም ግድግዳ፥ በምስሏ አሸብርቆ፣
አስረሳኝ ብዬ ብጠጋው፥ አባረረኝ አስናፍቆ።

ልክ ልኳን ነግሬ፥ ሰድቤ ልሰናበታት፣
መጥላት ቢከብደኝ እንኳ፥ የጠላሁኝ ልምሰላት፤
ብዬ ሞክሬም ነበር፥ የስድብ ቃላት ቋጥሬ፣
"እንኳንም ተውኩህ በዘዴ፣
አንተ 'ማትረባ መደዴ"
ብትለኝ አፈርኩ በራሴ፥ ቤቴ ተመለስኩ አቀርቅሬ፣
ስሔድ ከነበረኝ ቁመት፣ ግማሽ ክንድ ያክል አጥሬ።

ጥላኝ በሔደች ማግስት፥ የተካችብኝ ተራ ሰው፣
ለጊዜው ቢረታት'ንጂ፥
ለኔ ያላትን ቦታ'ንደሁ፣ መቼም ቢሆን አታወርሰው፣
የሷ ምትኮች ሁሉ፥ እሷን እንዳስናፈቁ
የኔዎቹም የኔን ዙፋን፥ በተአምር አይነቀንቁ፣
ብዬ በማለም ልፅናና፥ ያደረግኩትን ሙከራ፣
ቅናት አፍርሶ ጣለው፥ ያን የደካማ ፉከራ።

ለሌላው ዓለም በሙሉ፥ ሳድል በብላሽ ጥላቻ፣
ላንቺ የሚሆን አንድ አጥቼ፥ እንዳልሆንኩኝ መዛበቻ፣
አሁን ግን ተሳካ ዛሬ፥ ይኸው የምሥራቼ፣
እንደጠላሽኝ ሳላምን፥ ልጠላሽ መጣሬን ትቼ፣
"ጠላችኝ" ብለው ለልቤ፥ ከራሴ ጋር ተሟግቼ፣
"ጠላሁሽ" ብዬ ግጥም ጻፍኩ፥
"ናፈቅሽኝ" ማለቴን ትቼ።
(ሰኔ 10፣ 2009)

Is OLF Dead or Alive?

(Friday, October 4, 2013)

Based on a facebook status update I wrote on October 1, 2013 on which I mentioned OLF (Oromo Liberation Front) was dead, I had an interesting discussion on twitter. I thought, though boring, it would also be helpful in provoking discussion on the Oromo-Ethiopia politics and future, if you get a few lines of the discussion. Enjoy! Below is the status update I published:

> ***They give a term their own meaning; then, they condemn it.***
>
> *For me, Ethiopianism is one of these purposely made confusing terms. It is used by OLFites to refer to Abyssinianism (which is dominated by Amhara, Tigre and a few southerners esp. the Guraghe people culture). Ethiopia is a country that's wider than that Abyssinia now. Yes, Abbyssinians have used force, abused rights, marginalized some cultures and languages but that don't make wrong the fact that they created a bigger sovereign State. Bigger is better in either political power or economical strength. That State - Ethiopia - is home of all regardless of differences in language, cultural values and religious beliefs. The only thing that makes it look like a comfortable home for few is its political setting. Its political setting has always been different to its societal setting.*
>
> *Political leaders of Ethiopia, unfortunately, couldn't successfully create regimes that favor every member of the society equally and impartially. Ethiopia is a sovereign State. Any Ethiopian has the right and the obligation to struggle to make Ethiopia an inclusive one for all because it is meant to be like that. Therefore, Ethiopianism can be defined and redefined as a State that accommodates all varieties of social values, language and cultural differences. Be it in Federalism or whatever you have, Ethiopiaism can be defined as an accommodating one to be in the future; but not as the discriminatory one as in the past.*
>
> *I am not in delusion about the presence of politicians or activists who work to profit from defaming or faking common values. For me, they will eventually perish.*
>
> *I have a good example how political entrepreneurship perishes the good cause. OLF, especially for introducing Oromummaa, was a great party. Oromumma is a movement to create pride in and promote the*

Oromo language, the Oromo Culture and the Oromo indigenous Religion. The Oromo people loved it and accepted OLF as redeemer of the people. But, OLF couldn't be in the place when needed. Dirty political games and interests have washed their cause away from the OLFites mind. And, only if they think that will make them look like more Oromo than the other (there is no such thing though) they do anything. That's how they created lines between societies who are living together to profit from the split. Now, the only benefit OLF do is used to TPLF as a means to jail Oromo youth dissidents.

By the way, it has been so long since OLF has died; but, its ghost - like Meles' ghost does - is leading many. I suggest it is time to wake up and listen to the pain of the people you are claiming struggling for. Stand by it and help solving its challenges. Don't confuse it.

Here is part of the twitter discussion provoked by the above note:

Bira'anuu Biyo (@BiraanuuBiyo): @befeqe, you can feed your followers and yourself momentarily happiness by declaring #OLF is dead. We know, you can't fool the Quubee generation.

Me (@befeqe): You don't know the people; not even its pain.

Oromo Network (@Oromo_NT): @befeqe, why do you think people believe in a party supposedly long dead? OLF may die, but what it stands or stood for will never die.

Me: People believe in OLF because it was the first genuine party for the people. Not anymore. Sooner or later people distinguish between the people and the party. Oromummaa was its only legacy.

@Oromo_NT: Even in a democratic Ethiopia, if she ever becomes one, there will be a political party that will advocate for Oromo Self Determination.

Me: In democratic Ethiopia oneness may not really means one being. It will be united-ness.

@Oromo_NT: I can assure you that I and my likes will form a political party that will seek independence from Ethiopia even if Ethiopia democratizes.

Me: You'll have the right but I doubt your success.

@Oromo_NT: Fair enough! But you guys assume that Oromos love being Ethiopian without even doing a single empirical research on their attitude.

Me: don't you guys me. Who am I? Anyway, I believe the self-determination narration is an insult or niqet to the Oromo people.

@Oromo_NT: You guys are those of you who think you can speak for Oromos without even studying what Oromos want.

Me: Emmm... I can't argue with your take of who I am. Let's proceed the important discussion.

@Oromo_NT: You cannot build oneness on the foundations of conquest and annexation. That legacy must be undone first through self determination.

Me: It is the definitions you have given to unity that forces you draw this conclusion. Unity isn't oneness. It's united-ness for the better.

@Ze_Alem: @Oromo_NT, It obvious that EPRDF fear every Oromo as OLF member not the people of Ethiopia. Why separation if we bring equality?

@Oromo_NT: @Ze_Alem, one may want Oromia as a country just for the sake of it alone.

Me: The Oromo people paid a lot to the present Ethiopia. They can't just leave it all.

@Oromo_NT: When they leave they will take what is their own. There is really nothing to miss. Why would I want to be united with people I cannot trust with my liberty and freedom? What has my community gotten since Adowa? .... Oromos paid not for Ethiopia but because Italy also came to enslave them too.

Mesfin Meshesha (@kobele): @Oromo_NT, can you cite a book or any historical evidence on that?

@Oromo_NT: @kobele, western Oromos had wanted to establish an independent Oromo confederation when Italy came but when that failed they fought. If Britain hadn't refused to act on their request, western Oromia would have parted ways with Ethiopia.

@kobele: Who do you mean by Oromo in this case? It needs an organization to make such a claim, right?

Me: You can't just runaway though. Besides, if there is democracy majority rules. Why bother about trust? Others should.

@Oromo_NT: Why is it a niqet if Oromos do not want to run or be part of Ethiopia? It is true Oromos should not beg for their independence.

Me: No! The narrations undermine the people of Oromo.

@Oromo_NT: In that case change the name of the country to Oromia & ditch Ethiopia. That would be a good start.

Me: That's a better narration but still there are lots of questions.

@Oromo_NT: What are those questions?

Me: For e.g. Oromo is major ethnic group not majority as in 50%+1 but Ethiopia isn't an ethnic group.

@Oromo_NT: Why then should Oromos bear a name of country that subjugated them for a century when they can have their own country? Ethiopia is a Trojan horse hiding in her belly an ethnic group that defined what it means being an Ethiopian. A fatal blow to brand. The name Ethiopia does not resonate with me, I do not relate to it.

Me: Do the majority of the people worry about that? Should that be the question? It's beyond my response but OLF too has no real answer for that.

@Oromo_NT: Since you are with Zone9 , why don't you conduct a survey in Oromia to find out the prevailing attitude?

Me: We would if we could. (Money?) We will think about it though. It would be nice but the survey may not get true attitudes. People may doubt our intention. They might think of us as cadres of TPLF.

@Oromo_NT: There are ways of conducting anonymous surveys or even use other means to ensure confidentiality. It is better than nothing if done correctly. Otherwise, how else would you know public attitude on issues like this?

Me: Sure. detailed studies should be done but until then investigating all ways & discussing them would help from making fatal mistakes

@Oromo_NT: haha, some farmers may not even know the name Ethiopia or who the prime minister is. But ask those who deal with Ethiopia.

[ከሰማይ ቤት የተላከ]

ከቅርብ ርቀት በቆሙ፥ ትልልቅ ፎቆች ትይዩ፣
የቆሻሻ ተራራ ላይ፥ ተደፍቶ ሲያድር ሰማዩ፣
ውዳቂ ሕይወት ስንኖር፥ ከትራፊያችሁ ተራራ ሥር፣
የተጣለውን በልተን፣ ቀዳዳ ለብሰን ስናድር፣
መፈጠራችን በራሱ፥
ትዝ የሚለው ሰው ማን ነበር?

እግዜር ይመስገን ዛሬስ፣ ሞት እሚሳነው የለ፣
ከኑሯችን ተሽሎ፥ ሞታችን "የሰው" ተባለ።

ለሞት እግዜር ሞት ይስጠው፥...
ለኛ ማዕረግ እንደሰጠ፣
ሰው የናቀውን አክብሮ፥ ከሰው ዕኩል ላስቀመጠ።
(መጋቢት 4፣ 2009)

(ይህ ጽሑፍ የተጻፈው በአዲስ አበባ - ቆሼ በሚባለው አካባቢ ቆሻሻ ተደርምሶባቸው ለሞቱ ሰዎች መታሰቢያ ነው።)

የተዘለለው ምዕራፍ

(ጥቅምት 2፣ 2008)

የሰለሞን ስዩምን *‹‹የኦሮሞ ጉዳይ እና የኢትዮጵያ ብያኔ››* የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ (ሁለተኛ እትም) አነበብኩት፡፡ በጥቅሉ ወድጄዋለሁ፡፡ ጥቂት ቅሬታዎች ግን አሉኝ፡፡ ሰለሞን በአማርኛ የኦሮሞ ጉዳይን ከጻፉ (እና እኔ ካነበብኩላቸው) ጸሐፍት ሁሉ በተሻለ ልለው በምደፍረው ደረጃ ምሁራዊ ታማኝነት (intellectual honesty) ተስተውሎበታል፡፡ አልፎ፣ አልፎ ግን ምሁራዊ ታማኝነቱ ከሚጎድላቸው ምሁራን ማጣቀሱ ሚዛን አስቶ ያንገዳገደው ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ የታቦር ዋሚ ‹‹የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች››ን ማንሳት ይቻላል፡፡ ታቦር ትልቅ ርዕስ ይዞ ትንንሽ ክርክር የተከራከረባቸው ቦታዎች አሉ፡፡ አንዱ የቋንቋ ተናጋሪዎች ብዛትን በተመለከተ የሚሰጠው ምንጭ አልባ ድምዳሜ ነው፡፡ ሰለሞን ያንን በኦሮሞ ጉዳይ ላይ ያንፀባርቀዋል፡፡ "...መረጃዎች አሉ" በሚል ብቻ፡፡ በተጨማሪም አጠራጣሪ (አከራካሪ) ሁኔታዎች ላይ እምነቱን ለዘውግ ብሄርተኞቹ ትርክት ወደመስጠቱ አዘንብሎብኛል፡፡

ይህ በእንዲህ አያለ፣ መጽሐፉን አንብቤ ስጨርስ የጎደለ ነገር ያለ-ያለ ተሰማኝ፡፡ ታዲያ የጎደለ የመሰለኝን ምዕራፍ ለምን አልጽፈውም አልኩና ተነሳሁ፡፡ ጽሑፉን የምጽፈው የሰለሞንን ሐሳብ እየተዋስኩ፣ የኔን እየጨመርኩበት ነው፡፡ እሱም ይጭንብኛል፤ እኔም እጭንበታለሁ፡፡ ስለዚህ ከታች የማሰፍረው ጽሑፍ ላይ ‹እኔ›› እኔ አይደለሁም፡፡ ሰለሞን ስዩም ነው፡፡ እኔ ሁን እንዳልኩት፡፡

የተጣመመው የብሔርተኝነት ቅርንጫፍ

በኢትዮጵያ ቀኝ ዘመሞች አና ግራ ዘመሞች ሁሌም እርስ በርስ እንደተዋቀሱ ነው፡፡ እነዚህ ‹‹ትምክህተኛ ብሔርተኞች ፍፁም አሀዳዊ አገር ለመፍጠር ሊፍጨረጨሩ አገሪቱን ይበታትኗታል፡፡ ሲሉ፣ እነዚያ ‹‹ጠባብ ብሔርተኞች ሁሉንም ነገር በዘውግ ዓይን እያዩ አገሪቱን ሊበጣጥሷት ነው›› ይላሉ፡፡ መጽሐፉ በኦሮሞ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን ነው፡፡ ስለሆነም አሁን ማተኮር የምፈልገው የዘውግ ብሔርተኞች የሚከሰሱባቸው ችግሮች እና መፍትሔዎች ላይ ነው፡፡

አማራ-ሰግነት (AmharaPhobia)

ኦሮሞ ብሔርተኝነት ከገጠሙት ፈተናዎች መካከል አንዱ የኦሮሞ-ሰግነት እንደሆነ የሆነ ቦታ ገልጫለሁ፡፡ የአማራ ልሒቃን ያለውን ስርዓት ለማንበር ከመፈለግ ይሁን የኦሮሞ ልሒቃን ወደ ሥልጣን ከመጡ የቀድሞ የአማራ ገዢዎች በአባቶቻችን ላይ አድርሰውታል ለሚሉት በደል ‹ይበቀሉናል› በሚል ፍራቻ ኦሮሞ-ሰግነት ልንለው የምንችለው የኦሮሞ ብሔርተኝነትን የመፍራት ሥነ ልቦና አዳብረዋል፡፡ የይስሃቅ ኒውተን ሦስተኛ ሕግ በዚህም ይፈፀም ዘንድ፣ የአማራ ልሒቃን የአፀፋ ፍራቻ በኦሮሞ ልሒቃንም ዘንድ እየተንፀባረቀ ነው፡፡ ቀኝ እና ግራ ጠርዝ ላይ ቆመው በፍራቻ መተያየታቸው በመሐል ቤት የጠቀመው ሕወሓት መራሹን ቡድን ነው፡፡ የሁለቱንም ወደመሐል መምጣት መፍትሔ የሚያደርገውም አንዱ የዚህ ችግር መኖር ነው፡፡ ነገር ግን የተጣመመው እያልኩ የምጠቅሰው የኦሮሞ ብሔርተኝነት አራማጅ ልሒቃን የፈጠሩት የፖለቲካ ትርክት ከአማራ-ሰግነትም አልፎ ወደ አማራ-ጠልነት እያመዘነ ነው፡፡ የኦሮሞን ብሔራዊ ማንነትን ለመገንባት አስተዋፅዖ አድርጓል ያልኩት ‹የጋራ የመበደል ታሪክ ወለድ ሥነ ልቦና› በልሒቃኑ የተሳለበት መንገድ ‹ከታሪክ እንደምንረዳው ከአማራዎች ጋር መተማመን አንችልም፡፡ ስለዚህ አብረን አንኖርም› ዓይነት መደምደሚያ አዝሎ ነው፡፡ ድምዳሜው በአሜሪካ የባሪያ አሳዳሪ ወይም በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ስርዓት የተበደሉ ጥቁሮች ከደረሱበትም የከፋ ድምዳሜ ነው፡፡ በጣም አሳሳቢው ጉዳይ ደግሞ በኦሮሞ ሕዝብ የዕኩልነት፣ የፍትሕ እና ርትዕ ተጋድሎ ውስጥ ከጊዜ ወደ ጊዜ ብዙ ቅጠል እያፈራ የመጣው ቅርንጫፍ ይህንኛው ጠማማ ቅርንጫፍ መሆኑ ነው፡፡

አማርኛ-ሰግነት

የአማራ ጠልነት ጦስ የአማርኛ ቋንቋንም ሰለባው አድርጎታል፡፡ "ሊንጓፍራንኳ" (ባሕሩ ዘውዴ(ፕ/ር) እንዳለው) በመሆን የክልል መንግሥትን (ሕዝቦቹን) አንዱን ካንዱ እንዲያግባባ የፌደራል መንግሥት የሥራ ቋንቋነት ማዕረግ ቢቸረውም፣ የተጣመመው የኦሮሞ ብሔርተኝነት ቅርንጫፍ አራማጅ ልሒቃን ግን የአማርኛ ትምህርት ክፍለጊዜን እንዳይታደሙ (አቋርጠው እንዲወጡ) ተማሪዎቹን ያነሳሷቸዋል፡፡ የፌደራል ቋንቋው በኦሮሚያ ክልል ከ5ተኛ ክፍል መጀመሩ (ቀድሞ አለመጀመሩ) በፌደራል መንግስቱ ውስጥ ኦሮሚያን "ሐሳባቸውን እና አቋማቸውን መግለጽ በማይችሉ፣ ነገር ግን፣ በኮታ ብቻ የሚወከሉ፣ ግዑዝ ፖለቲከኞች ይሞሏታል ማለት ነው" ያልኩት ላይ ተጨማሪ ችግር አከሉበት ማለት ነው፡፡ እነዚህ ልሒቃን ይህንን የሚያደርጉት ‹አማርኛን ከኦሮሚያ ክልል ውስጥ በ2020 ለማጥፋት› ካላቸው ምሥጢር መሆን ያልቻለ ምሥጢራዊ

ዕቅዳቸው በመነሳት ነው፡፡ ኦሮምኛ ሁለተኛ የፌደራል መንግሥቱ የሥራ ቋንቋ እንዲሆን መሥራት ሌላ፣ አማርኛን ለማጥፋት መሥራት ሌላ፡፡ አንድ ግለሰብ (ወይም ማኅበረሰብ) ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ቢሆን ተጠቃሚው ራሱ መሆኑን የዘነጋ አካሄድ ነው፡፡ ክርክሩ ምን ያህል ውኃ እንደሚያነሳ ለአንባቢ በመተው የአማራ ልሒቃንን ከዚህ የተገናኘ ሙግት ላንሳ፡- ‹አማርኛ የፌደራል ቋንቋ በመሆኑ የተጎዳ ካለ ዋነኛው አማራ ነው፡፡ በሌሎች ክልሎች ያሉ ዜጎች ከአፍ መፍቻቸው ውጪ አማርኛን ሲማሩ፣ የአማራ ክልል ሰዎች ግን ተጨማሪ የአገር ውስጥ ቋንቋ አይማሩም፡፡ ይህም የአማራ ልጆችን ሌላ ክልል ተዘዋውሮ የመሥራት ዕድል አጥብቦታል› ይላሉ፡፡

ወደ መነሻችን ስንመለስ፣ አማርኛን ኢትዮጵያ ውስጥ ከሁሉም የበለጠ የበለፀገ እንዲሆን ያደረገው “ዕድል” ነው፡፡ (በነገራችን ላይ በኢሕአዴግ ዘመንም የተናጋሪዎቹ ቁጥር በፍጥነት እያደገ ነው፡፡) ባሕሩ ዘውዴ “The Changing Fortunes of the Amharic Language” በሚለው ድርሳኑ “አማርኛ መበልፀጉን የቀጠለው ታሪካዊ ክስተቶች ቀድሞውኑ እንዲበለፅግ ስላደረጉት ነው” ይላል፡፡ እውነት ይመስለኛል፡፡ መርጌታ ግሩም ተፈራ የተባለ ፀሐፊ (‹የደብተራ ታሪክ› ነው ካላላችሁብኝ) የአማርኛን ታሪክ ሲያነብር ‹የአክሱም መግባቢያ የነበረው ግዕዝ ነው፡፡ ደብተራዎች አሁንም ድረስ “ነገረ-ደብተራ” የሚባል የምሥጢር መግባቢያ በየጊዜው ይፈጥራሉ፡፡ [በከተማ ‹የአራዳ› ወይም ‹የዱርዬ› /እንደሰሚው/ የሚባለው ዓይነት ቋንቋ ማለት ነው፡፡] ኋላ ዮዲት [አስቴር ይሁዲት] ባመፀች ጊዜ፣ አክሱማውያን መኳንንት ሸሽተው ሰሜን ሸዋ አንኮበር ተሸሸጉ፡፡ እዚያም ለሚስጥራዊነት ሲባል መኳንንቱ “ነገረ-ደብተራን” ይጠቀሙ ጀመር፡፡ ሌላው ሰፋሪም የመኳንንት ቋንቋ አገኘሁ ብሎ ይናገረው ጀመር፡፡ በዚህ መንገድ የተወለደው አማርኛ ዕድል ቀንቶት ዕድገቱ ተፋጠነ› ይላል፡፡ (ወሬሳው ካሳ፣ 2005፡230 ላይ) የባሕሩ ዘውዴ ድርሳንም አማርኛ የተወለደው በዚሁ የ13ኛው ክ/ዘመን ገደማ እንደሆነ ይናገራል፡፡ በሌላ በኩል ዶናልድ ሌቨን (ዶ/ር) ‹Greater Ethiopia Reconsidered› በሚል በሠራው አንድ ጥናቱ ‹አማርኛ የተፈጠረው የኦሮሞ ተወላጆች ግዕዝ ለመናገር ሲሞክሩ ነው› በማለት ያትታል፡፡ የመርጌታ ግሩም ተፈራን ትርክት ማመን ከቻልን ይህ እውነት ሊሆን ይችላል፡፡ ዶናልድ ሌቪን የአማርኛ ቋንቋ ቅርፅ (Synatax) የኩሽ ቋንቋዎች ባሕሪ ያለው መሆኑን ጠቅሶ ነው እንዲያ ያለው፡፡ ባሕሩ ዘውዴም “[አማርኛ] ተገንጥሎ ወጥቷል ተብሎ በጥቅሉ ከሚታመንበት ሴማዊው ግዕዝ ይልቅ ከኩሻዊው ኦሮምኛ ጋር ብዙ የሚጋራው ጠባይ አለው” ብሎ ጽፏል፡፡

በዚህ ትርክት መሠረት የተጣመመው ብሔርተኝነት ቅርንጫፍ አራማጅ ልሒቃን የሚጠሉት አማርኛ፣ ምናልባትም የኦሮሞ ሕዝብ ራሱ የፈጠረው

ወይም በፈጠረው ወቅት አስተዋፅዖ ያደረገለትን ቋንቋ ነው ማለት ነው። ከዚያም በላይ ኋላ የአማርኛ ተናጋሪ በመሆናቸው “አማራ” የሚል የዘውግ ብሔር ስያሜ የሰጠናቸው ሰዎች የጥንት ዘራቸው ኩሻዊ እና አክሱማዊ (አክሱማውያን /አግኣዚኣዊያን/ ራሳቸው ኩሻውያን ነበሩ የሚባል ትርክት አሁን፣ አሁን እየገነነ ነው) የነበሩ ናቸው ማለት ነው። ፀቡ ዞሮ፣ ዞሮ ወደ ኋላ መለስ ባልን ቁጥር ከራስ የዘር ግንድ ጋር መሆኑ የተረጋገጠ እውነታ ቢሆንም የዚህን ያህል በቅርብ የሚታይ (Traceable) መሆኑ ግን የራሱ የሆነ የከንቱ ጥላቻ ፖለቲካን አስተዛዛቢ ማጋለጫ ነው።

የአማራ እና የአማርኛ ጥላቻው በጥቅሉ አማራ ብለን በአሁኑ የብሔር ብያኔ መሠረት የምንጠራው ሕዝብ የሚጠቀምበትን ነገር በሙሉ በጋራ አለመጠቀም የጠማማው ቅርንጫፍ አራማጆች የላቲን ፊደሎች* ለኦሮምኛ የተመረጡት እንደ እውነቱ ከአማርኛ-ጠልነት በመነጨ ምክንያት ቢሆንም፣ ኋላ ላይ ለማስተባበል ከተጻፉ ጥናቶች የጥላሁን ጎምታን ጠቅሻለሁ። እዚያ ላይ ምናልባት አሳማኙ ‹‹ለኦሮሞ ሕዝብ የሥነ-ልቦና ነጻነት ወሳኝ ነው›› የሚለው ብቻ ሳይሆን አይቀርም። ጥረቱ የቴክኒክ ጉድለቶቹን የመቅረፍ ጉዳይ ብቻ ቢሆን ኖሮ የሼክ በክሪን የአፋን የኦሮሞ ፊደል ገበታ ለመጠቀም የተደረገ ጥቂት እንኳን ሙከራ (consideration) እናይ ነበር። (*በነገራችን ላይ መጽሐፌ ውስጥ የ‹ላቲን ፊደሎች› ምንጭ ነው ብዬ “የኩሽ ፊደል” እያልኩ የጠራሁበት ቦታ አለ። ያንን ያክል ምንጭ ፍለጋ መሄዴ፣ ከሌሎች ሙግቶቼ አንፃር ምን ያክል አመክኖአዊ እንደሚያደርገኝ ራሴን በራሴ ያጠራጥረኛል። የፊደሉ ምንጭ የኔ ነው ለማለት ያንን ያክል ርቄ መሄዴ ካልቀረ ‹‹ጨቋኝ፣ ተጨቋኝ›› የምላቸውን ዘውጎችንም የሩቅ ምንጭ ቀድቼ ‹የአቤል እና ቃዬል› መጠፋፋት ዓይነት መሆኑን መግለጽ ነበረብኝ።)

በነገራችን ላይ በጥላሁን ጎምታ ጥናት ላይ የተጠቀሰው በግዕዝ ፊደላት ሊቀረፍ አይችልም ከተባሉት ችግሮች አንዱ የሚጠብቁና የሚላሉ ፊደሎችን መለየት አለመቻሉ ነው። ሲጠብቁ እና ሲላሉ እንዲሁም ሲጎተቱ የተለየ ትርጉም የሚሰጡት የአፋን ኦሮሞ ቃላቶች ብዛት ምን ያህል እንደሆነ አላውቅም። ነገር ግን ችግሩ አማርኛንም የገጠመው ችግር ነው። ቁቤን በመጠቀም ይህን ችግር ለመፍታት የተደረገው ሙከራም ራሱን የቻለ ሌላ ችግር ማስከተሉ አልቀረም። በግዕዝ ፊደላት አንድ ገጽ የሚጻፈው ጽሑፍ በቁቤ (ከአናባቢዎቹ መብዛት የተነሳ) ሁለት ገጽ ገደማ ይሆናል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተለያዩ ቦታዎች ላይ በግዕዝ ሆሄያት ፈንታ “dha,dhi…” እያልኩ ጽፌያለሁ። ለምሳሌ ‹ይላማ dheeሬሳ› የሚለውን መጥቀስ ይቻላል። ይህንን ድምፅ የሚገልጽ የግዕዝ ሆሄ የሌለ መስሎኝ የተፈጠረ ስህተት ነው እንጂ፣ ምንም እንኳ ድምፁ በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ባይኖርም፣ በፊደል ገበታው ላይ ግን አለ። በነጋሶ ጊዳዳ (ዶ/ር) ታሪክ ‹ዳንዲ› ላይም ‹ዺ›ን

ለመፃፍ ‹ዲ› ከጻፉ በኋላ በእስክርቢቶ አናቷ ላይ ጭረት አድርገውባታል። ነገር ግን ፊደሉ የኮምፒውተር የፓወር ግዕዝ የፊደል ሰሌዳ ላይ ‹shift key + d› ስንጫን ይገኛል። ፊደሉ ከ‹ጰ› ጋር ይመሳሰላል፤ ነገር ግን በ‹ደ› እና ‹ጰ› መካከል ያለውን ልዩነት ከተረዳን በሁለቱ ፊደሎች መካከል ያለውም ልዩነት ግልጽ ይሆንልናል። መጽሐፉ ላይ ያሉትን መሰል ግድፈቶች፣ ምናልባትም ቀጣዩ እትም ላይ አርመዋለሁ። . . . (የኦሮምኛ የግዕዝ ፊደላትን የመጠቀም ጉዳይ መሐል ሰፍረን ለምናቀነቅነው አንድነት ወይም ኅብረት ራሱን የቻለ /የአንድነት የጋራ መገለጫ/ ቅመምመሆን ስለሚችል ነው የምንቆጨው እንጂ ይህንን የምለው ወደኋላ እንመለስ ለማለት አይደለም። አንዳንዴ በአማርኛ ሆሄያት ኦሮምኛን መጻፍ ሲያስፈልገን፣ አንዳንድ የአማርኛ-ኦሮምኛ መዝገበ ቃላቶች ላይ ‹ፊፅሞ አይቻልም› እንደሚሉት ብዙም እንደማንቸገር ለማስታወስ ያክል ነው።)
በአሁኒቷ ኢትዮጵያ ብያኔ አማራ የሚባለው ክልል ሕዝቦች ራሳቸውን በወንዛቸው (የኦሮሞ ሕዝብ በአብዛኛው ራሱን በብሔሩ ሥር ባለው ጎሳው መጥቀስ ነው የሚወደው)፣ አሊያም በኢትዮጵያዊነታቸው ለይተው መጥቀስ ይወዳሉ። ይህንን ግን ‹በኢትዮጵያዊነት ውስጥ የተደበቀ (pseudoEthiopian) አማራነትን› ለማራመጃነት እንደሚጠቀሙበት መሣሪያ የሚመለከቱባቸው ብዙዎች ናቸው። መጽሐፌ ውስጥ የአማራ ሕዝብ ራሱን በአንድ የዘውግ ብሔር ማንነት ለምን እንደማይጠራ ጠቅሻለሁ። በተጨማሪም ቀድሞ ‹አማራ› ይባል የነበረው ‹አማራ ሳይንት› የሚባለው አካባቢ ብቻ እንደሆነና የአማርኛ ቋንቋ መስፋፋት ነገሩን ቀይሮ አማርኛ ተናጋሪው በሙሉ አማራ መባል እንደጀመረ› ብዙ ድርሳናት ይተርካሉ። እስከቅርብ ግዜ ድረስም ‹ማነው አማራ?› በሚለው ላይ መግባቢያ ላይ መድረስ አይቻልም ነበር (አሁንም ተችሎ መሆኑን እርግጠኛ አይደለሁም)። ለምሳሌ በፊታውራሪ ተ/ሐዋርያት ‹አውቶባዮግራፊ› ላይ ‹አማራ› የሚለው ቃል ‹ክርስቲያን› ለማለት (ገጽ 278፣ 292)፣ ‹መልካም ሰው› ለማለት (ገጽ 306) ላይ ተጠቅሷል፤ ‹የጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀ/ወልድ ማስታወሻ› ደግሞ “…የአማራ የሚባለው” ይልና በቅንፍ “ጎጃም፣ ጎንደር” ብሎ “ትግራይ”ን ይጨምራታል (ገጽ 10)፤ ጆን ስፔንሰር ትርሚንግሃም እ.ኤ.አ. በ1952 ባሳተመው ‘Islam in Ethiopia’ በሚለው መጽሐፉ ላይ ስለአገው ሕዝቦች ሲያወራ “አሁን ትግራይ፣ ቤጌምድር፣ ደምቢያ፣ ጎጃም፣ አገው-ምድር፣ ዳሞት እና አማራ የሚባሉት አካባቢዎች ላይ የሰፈሩ ሕዝቦች ነበሩ” (ገጽ 48) በማለት ጎጃምና ጎንደርን (ቤጌምድርን) ሳይቀር ‹አማራ› እንዳልሆኑ ይጠቅሳል። ዛሬ ላይ ‹አማራ› ማለት በአሁኑ ብያኔ መሠረት የአማራ ክልል ሕዝብ ማለት ነው። ሒደቱ የብሔርተኝነት ብያኔን ተለዋዋጭነት ያስረዳናል ብዬ እገምታለሁ። ‹የጋራ ተበዳይነት ስሜት ለኦሮሞ ብሔራዊ ማንነት እንደሰጠው› በተደጋጋሚ ተናግሬያለሁ። በተመሳሳይ፣ የኦሮሞ ልሒቃን አማራ-ጠልነት አዝማሚያ አማራን (በተሠመረለት ድንበር ላይ ተመሥርቶ)

ቀድሞ ከነበረበት እና ምናልባትም የዘመናዊ ሰውነት መጀመሪያ ነው ከሚባልለት የግለሰባዊነት (individualism) ስሜት ወጥቶ የብሔራዊ ስሜት እንዲያዳብር እያስገደደው ነው። ይህ የምሥራች አይደለም።

ደም አዳኝነት

"ኦሮሞነትን በደም የሚገልጽ ካለ ለኔ ሞኝ ነው" ብያለሁ። ሞኝ ብቻም አይደለም፤ አደገኛም ነው። የተጣመመው የብሔርተኝነት ቅርንጫፍ አንዱ አደገኛ መገለጫ ይኸው ኦሮሞነትን በደም ለመግለጽ መሞከር ነው።

ኦሮሞ ማነው?

ሀ) ኦሮሞ ማኅበረሰብ ውስጥ ከኦሮሞ ወላጆች ተወልዶ ያደገ፣ ቋንቋውን የሚችል፣ ባሕሉን የሚረዳ፤
ለ) ኦሮሞ ማኅበረሰብ ውስጥ ኦሮሞ ካልሆኑ ወላጆች ተወልዶ ያደገ፣ ቋንቋውን የሚችል፣ ባሕሉን የሚረዳ፤
ሐ) ከኦሮሞ ማኅበረሰብ ውጪ ከኦሮሞ ወላጆች ተወልዶ፣ ቋንቋውን የማይችል፣ ባሕሉን የማይረዳ፤
መ) አፋን ኦሮሞ የሚናገር፣ ባሕሉን የሚረዳ ማንኛውም ሰው፤
ሠ) ኦሮምያ ክልል ውስጥ የሚኖር ማንኛውም ሰው፤
ረ) . . .

በጣም አደገኛ የሚባለው መልስ ማንነትን በደም ለመግለጽ መሞከር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሙከራ ንፁህ ዘር፣ ድቅል ዘር… ወደሚል መደምደሚያ ያመራል። ቀድሞ በነበረው ጅምላ ፍረጃ (stereotyping) ላይ ተመስርቶ፣ በክፉ ቀን፣ ውጤቱ ዘር ማጥራት ነው። Genocide! ማንነትን በደም ለመግለጽ መሞከር ማንነት በአንድ በኩል የቋንቋ፣ የባሕል እና የሙያ ውኅድ ውጤት፣ በሌላም በኩል በትምህርት፣ በጉብኝትና ልምምድ የሚለዋወጥ (ተፈጥሯዊ ያልሆነ ሥሪት) መሆኑን ሰርዞ ‹በዘር ሐረግ የሚመዘዝ ነገር ነው› እንደማለት ነው። ‹ሰውዬው፣ ለምሳሌ ኦሮሞነትን በደሙ፣ ከወላጆቹ ካልወረሰ አፍ መፍቻ ቋንቋውም ሆነ የሚያውቀው ባሕል የኦሮሞ ብቻ የሆነ ሌላ ቋንቋ የማያውቅ ሰው ኦሮሞ አይደለም ሊባል ነው› እንደማለት ነው። በርካታ የኦሮሞ ብሔርተኝነት አራማጅ ድረ-ገፆች ላይ የሚታየው ግን ይህ ነው። አንድ የኦሮምያ ክልል ባለሥልጣን በተሾመ ቁጥር ድረ-ገፆቹ የሰውዬውን ወላጆች ማንነት ጎልጉለው በማውጣት ‹‹ኦሮሞ አይደለም›› ብለው ይጮሃሉ። ሰውዬው "ኦሮሞ ነኝ" ካለ፣ ‹ኦሮሞ ነው› ያለው የኦነጉ በያን አሶባ (ፒ.ኤች.ዲ) አባባል፣ አባባል ብቻ ሆነ ማለት ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥም እንደተገለጸው ሙክታር "የም" ነው ይባላል። እሱ "ኦሮሞ ነኝ" ማለቱ የጠማማው ቅርንጫፍ አራማጆች እንዲቀበሉለት አላደረጋቸውም። መረራ ጉዲና የአምቦ ሰዎች "ኦሕዴድ አልጋችን ላይ

የተወለደ ዲቃላ ነው" አሉኝ ሲል፣ ‹በደም ኦሮሞ አይደሉም› በሚል ኦሮሞነት እየተነፈጉ ነው ማለቱ መሆን አለበት፡፡ ይህ በራሱ በጉዲፈቻ እና ሞጋሳ፣ የደም ውርስ ሳያስፈልግ ኦሮሞነትን ለሚያጎናጽፈው ጥንታዊ ባሕል ዲቃላ አስተሳሰብ ነው፡፡ የደም ቆጠራ አደገኛ አዝማሚያ የሚንፀባረቀው ራሱን የኦሮሞ ብሔርተኝነትን በሚጎዳ መልኩ ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ የሙክታር ከድር እና የአስቴር ማሞ አመራር "የጅማ መንግሥት" መባሉ፣ ቀድሞ ደግሞ ኤርሚያስ ለገሰ እንደነገረን "አርሰናሎች" (የአርሲ ሰዎች) አመራር በዛ መባሉ የዘር ቆጠራው፣ ብሎም የሥልጣን ክፍፍሉ ወደ ወንዝ ቆጠራ እንደሚወርድ አመላካች መርዶ ነው፡፡ (እንደጉዳይ የተነሳው የሥልጣን ክፍፍሉ አለመማከል ሳይሆን የሰዎቹ የትውልድ ቀዬ ጉዳይ በመሆኑ!) ዞሮ፣ ዞሮ የዘር ቆጠራው ዓላማ የቡድን መብትን ማስከበር ሳይሆን "ብሔርተኞች" የሚፈልጉት አካል ሥልጣን እስኪቆጣጠር የሚመዙት ካርድ ሆኖ እንደሚቀጥልም ማመላከቻ ይሆናል፡፡

ዘውገኝነትን ወይም ብሔርተኝነትን (ጥቂት ነው ልዩነታቸው) ምሁራን በሁለት ሊከፍሉት ይሞክራሉ፣ በመልካምነቱ እና በክፋቱ፤ ዘውጌኝነት /ዘውጌ እኝኝነት/ (ethnocentricism) እና ዘውጌኛነት /ዘውጌ እኛነት/ (Nationalism) - ሁለቱም ትርጉሞች ለዚሁ ጽሑፍ ሲባል፣ መጽሐፉ ላይ የበፍቃዱ ሞረዳ ‹ማነው ዘረኛ?› ግጥም በመዋስ ፈጥሬ የተጠቀምኩባቸው ናቸው፡፡ ዘውጌኝነት ‹እኔ የምወክልበት ዘውግ ከሌሎች ዘውጎች ሁሉ ምርጡ ነው› በማለት ከሌሎች ጋር በዘር ላለመቀየጥ መሞከር፣ ሌሎችን ማግለል እና መጠየፍ እንደመፍትሔ የሚወስዱትን የሚወክል ሲሆን፤ ዘውጌኛነት ግን ለዚህ ጽሑፍ ሲባል ‹እኔም ሆንን ሌሎች ዕኩል የሰው ዘሮች ነን፤ ሆኖም እኔ ይወክለኛል የምለውን ዘውግ መምሰል ነው የምፈልገው› በሚል የዘውጉን ቋንቋ፣ ባሕላዊ አለባበስ እና አኗኗር ዘዬ የሚያዘወትሩትን የሚወክል ነው፡፡ በዘመነ ሉላዊነት (globalization) ግን ይህ የሚቻል ዓይሆንም፤ ሰዎች እንደኩሬ ውኃ በአንድ ቦታ ረግተው በሚኖሩበት ዘመን፣ ከሌሎች ጋር አለመቀየጥ ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ነበር፡፡ ለሰዎች ዓለማቸው አካባቢያቸው ነበር፡፡ አሁን ግን ሰዎች፣ ግለሰዎች እየሆኑ ነው፡፡ ይንቀሳቀሳሉ፤ ይቀየጣሉ፤ ባሕል፣ ቋንቋ፣ ወግና ሥልጣኔ ይወራረሳሉ፤ ያሻቸውን ካላሻቸው ይመርጣሉ፡፡ እንደየዘመኑ አንዱ ባሕል፣ ቋንቋ ወይም ሥልጣኔ ከሌላው የበለጠ የገነነ እና ተቀባይነት ያለው ይሆናል፡፡ የዘመኑ ሰዎችም (ትውልዶችም) የበለጠ የገነነውን እና ተቀባይነት ያለውን በመምረጥ የበለጠ ተጠቃሚ ሆነው ያልፋሉ፡፡

መጽሐፉ ውስጥ የሆነ ቦታ የገለጽኩላችሁ የባስክ ፖለቲከኞች አባዜ (የተጣመመው ቅርንጫፍ) ብሔርተኞችም አባዜ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ የአፍሪካ ኅብረት (ወይም የምሥራቅ አፍሪካ አካባቢያዊ ትብብር) መጠናከርን እየፈለጉ

ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ግን አብረን አንኖርም የሚል እርስበርስ የሚጋጭ አስተሳሰብ ነው፡፡ የአፍሪካ ኅብረት 50ኛ ዓመትን አስመልክቶ የታተመው “Unite or Perish” የሚል የጥናቶች መድብል ላይ ‹‹Separatist Movements, Insurgencies, and Integeration in Africa›› በሚል ርዕስ በHanji A. Diyal የተሠራ ጥናት እንዲህ ይላል፡-

> *“በመላው አፍሪካ ልኂቃን የመንግሥት ሥልጣን ለመቆጣጠር በማለም በግጭቶች ተጠምደዋል፡፡ የመንግሥትን ሥልጣን የመያዝ ግልጽ ዓላማው የገዛ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነታቸውን ማሻሻል ነው፡፡ በአፍሪካ የመንግሥት ሥልጣን ለልኂቃኑ እውነተኛ የሀብት ማፍሪያ እና ማስጠበቂያ ሰርተፍኬት ሆኗል፡፡ በርግጥ፣ የፖለቲካ ሥልጣን መያዝ ማለት የዘውግን ጥቅም ማስተማመን ከሚለው ጋር ትርጉሙ አንድ ሆኗል፡፡” (የኔ ትርጉም፣ ገጽ 322)*

መራር እውነት ነው፡፡ ስለዚህ በስመ ብሔርተኝነት (ወይም ዘውገኛነት) የሚቀነቀኑ “የደም” ማጣራቶች አላማ ለግል ጥቅም የመንግሥትን ሥልጣን መሆኑ መጋለጥ ይኖርበታል፡፡ ብሔርተኝነት ፍትሕ እና ርትዕን ለማረጋገጥ እንጂ በማኅበረሰቦች መካከል ሐሳባዊ መለያ መሥመር ለማኖር መዋል የለበትም፡፡

በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በግልፍተኝነት እና በግልብነት በተደረሱ ድምዳሜዎች ተነሳስቶ አንዱ ዘውገኛ፣ ሌላውን ሲገፋ - ዛሬ፣ ዛሬ መሠረታዊ የሰው ልጅነት በአገራችን ዋጋ አጥቶ በብሔርተኝነት እና ተጠቃሚነቱ የኀደለ የሚሉት ዘውግን ጥቅም በማስከበር ሥም የራስን ጥቅም ማሳደድ የተለመደ ሆኗል፡፡ ልብበሉ! ችግሩ የኦሮሞ ልሒቃን ብቻ አይደለም፤ በተለይ ከበፊቱ በከፋ አሁን፣ አሁን እያቆጠቆጡ ያሉት የአማራ ብሔርተኛ ልሒቃንም (አቀራረቡ ቢለይ እንጂ)፣ የሌሎችም ጭምር ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ የሚባሉትም ሳይቀሩ የዘውግ ብሔርተኞቹን እሴት የኢትዮጵያውያን አድርጎ የመቀበል የተሳሳተ ዕይታ እየተጋረጠባቸው ማየት የተለመደ ነው፡፡ የተጣመመው የብሔርተኝነት ቅርንጫፍ ወረርሽኝ እያጠቃ ያለው ሁሉንም ነው፡፡ …በአገራችን ሁሉም ኀጡን ሲያሳድድ እንደፖለቲካው ሁሉ ተራው የሸቀጥ ግብይት በዘውገኝነት እንዲመራ እያደረገ ያለው የተጣመመ ብሔርተኝነት ነው፡፡ በአገራችን የሰውዬውን ስም ሰምቶ ብቻ የፖለቲካ አመለካከቱን ብቻ ሳይሆን ገንዘብ የሚያስቀምጥበትን ባንክ፣ የሚጠጣውን የቢራ ዓይነት፣ የሚደግፈውን የአገር ውስጥ የእግር ኳስ ቡድን ሳይቀር መገመት እየተቻለ ነው፡፡

ለራሳችን ከእንግሊዝ፣ ስፔን፣ ላቲን አሜሪካ ድረስ የሚካሄዱ የእግርኳስ ሊጎችን እየተከታተልን፤ የቻይናና ሕንድ ጅንሶችን እየለበስን፤ የሆሊውድ፣ ቦሊውድ እና ኖሊውድ ፊልሞችን እየኮመኮምን፤ ከሶቅራጠስ እስከ ዘርዐያቆብ እያጣቀስን እንኳን የዘውግ ብሔርተኝነት፣ ዘውጎቹን ያቀፋቸው ኢትዮጵያዊነትም ይጠበናል። ዓለማዊ፣ ሰብኣዊ ነን። የተጣመመ ብሔርተኝነት ያመጣብን አባዜ፣ መፍትሔው ወደኋላ በመጓዝ ከታሪክ አይቀዳም። ጥላቻም ተረኛ ጨቋኝ ይፈጥር እንደሆን እንጂ መልስ አይሆነንም። ዶ/ር ሌቪን ‹ትልቋ ኢትዮጵያ› በሚለው መጽሐፉ ‹‹በልዩ ልዩ ቀለማት አሸብርቃ እንደተጠለፈች የጥልፍ ሥራ ሁሉ ኢትዮጵያም ፈፅሞ የተለያዩ ሕዝቦች ጥልፍ ትመስላለች ብሎ ማሰብ ሕዝቦቿ ለዘመናት እርስ በርሳቸው የነበሯቸውን በርካታ ግንኙነቶች፣ በጋርዮሽ የተካፈሉትን መከራና ደስታ መዘንጋት ነው›› ይላል። ...ኢትዮጵያ ለተበደሉት ሕዝቦቿም፣ ለጨቋኝ ልኂቃኖቿም ከተራ ጥልፍ በላይ የማይተረተር የብሔረሰቦች የርስበርስ ትስስር ነች ነው ነገሩ። ሼክ በክሪ ሳጳሎ ደግሞ ‹‹የወደፊቷ ኢትዮጵያ ሕልውና የሚወሰነው በኦሮሞ ሕዝብና በሌሎች ኢትዮጵያ ሕዝቦች ዕኩልነት እና አንድነት ነው›› ብለው ነበር። ልብ በሉ! ‹‹በሕዝቦቹ ዕኩልነት እና አንድነት ነው›› ያሉት። ሁለት በአንድ! ይህ እውን የሚሆነው ጠማማው ቅርንጫፍ ዛፉን ከማጉበጡ በፊት እንዲቃና ማድረግ (righting the wrong) ከቻልን ነው።

ማስገንዘቢያ፤ በጽሑፉ የተጠቀሱት ምሁራን አንቱ ያልተባሉት ጽሑፉ ‹የኦሮሞ ጉዳይ› ለተሰኘው መጽሐፍ ምላሽ - መካተት የነበረበት ምዕራፍ - በሚል እሳቤ የሚታረመውንም፣ የጎደለውንም ለመጠቆም እንደመሆኑ የመጽሐፉ ደራሲ በተጠቀመት መንገድ ለመጻፍ ሲባል ነው።

(ለዚያ ለጀግና ሕዝብ)

ከባርነት ሕይወት፥ ሞቱን ለመረጠ፣
ቂጤማ ጨብጦ፥ ደረቱን በድፍረት
ለጥይት ለሰጠ፣
ለነጻነት ትግሉ፥ የምሰጠው ባጣ፣
የፈሪ በትሬን፣ እንባዬን ላዋጣ።
...
(ለከንቱ እኔነቴ)
ቢዘገይም እንኳ፥ ለማይቀረው ሞቴ፣
እንዲህ በመፍራቴ፣
አላዝንም ለራሴ፥ አላለቅስም ለኔ፣
ፈቅዶ ለሚረገጥ፥ ሲያንሰው ነው ጭካኔ፣
በኔ መግደርደር ነው፣
ከወዲያኛው ሰፈር፥ የሚያልቀው ወገኔ።
ወይኔ!
(መስከረም 24፣ 2007)

“ጉንዳን እንኳ ሲሔድ ተሰልፎ ነው”

የኦሮምኛ ተረት

(ነሐሴ 2007፤ ከቂሊንጦ ወኅኒ ቤት)

በ19ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ አውሮጳውያን አፍሪካን ለመቀራመት ተሰብስበው ወሰኑ። ኃያላኑ መንግሥታት የየድርሻቸውን ሲወስዱ የኢትዮጵያን አካባቢዎች ለመውረር የሞከረው የጣሊያን መንግሥት ነበር። አውሮጳውያን ወራሪዎች “ዓላማችን አፍሪቃውያንን ከእንቅልፋቸው ቀስቅሶ ማሠልጠን ነው” ቢሉም እየዋሹ ነበር። ዋነኛ ዓላማቸው የአፍሪቃን ሀብት ለፋብሪካዎቻቸው ጥሬ ዕቃ ማድረግ ነበር። ሆኖም እግረ መንገዳቸውን አፍሪቃውያንን ሃይማኖታቸውን እያስለወጡ ከራሳቸው ጋር ያመሳስሉታል። ቋንቋ፣ ወግ እና ልማዶችን በማጥናት ዘመናዊ በሚሉት በራሳቸው ቋንቋ፣ ወግ እና ልማድ ይተኩታል። አፍሪቃውያንን ማሠልጠን የሚሉት ይህንን ነው። በዚህም ምክንያት ከቅኝ ግዛት በኋላ ብዙ አፍሪካውያን የራሳቸውን ቋንቋ፣ ባሕል እና ስርዓት ሙሉ ለሙሉ አጥተው በአውሮጳውያን ገዥዎቻቸው ባሕል እና ስርዓት እየተዳደሩ ነው። ኢትዮጵያ ግን በአንፃሩ ይህንን ወረራ በኅብረት መመከት በመቻሏ ምንም እንኳን ከአውሮጳ ተፅዕኖ ባትተርፍም የተለየ (የራሷን) ባሕል እና ወጎችን እንደያዘች አለች።

ኢትዮጵያ የአውሮጳ ወራሪዎችን መመከት የቻለችው ሕዝቦቿ በመተባበራቸው ነው። የጣልያን ሠራዊት አድዋ ላይ ድል ካደረጉት የጦር መሪዎች መካከል ባልቻ ሳፎ (በፈረስ ስማቸው አባ ነፍሶ) ሳይጠቀሱ የማይታለፉ የኦሮሞ ልጅ ናቸው። ከምንም ተነስተው የጦር ሚንስትር እስከመሆን የደረሱት ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (አባ መላ) ለዚህ ደረጃ የበቁት በአድዋ ባሳዩት ጀግንነት እና መለኛነት ነበር። እርሳቸውም የኦሮሞ ልጅ ናቸው። ጣልያን ድል ሆኖ መመለሱ ቆጭቶት ከ40 ዓመታት በኋላ ሲመለስም ወረራውን በመመከት ረገድ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ኦሮሞዎች ተሰልፈው ነበር። ከነዚህም መካከል የማይዘነጉት እነ ገረሱ ዱኪ እና ጃጋማ ኬሎ ይገኙበታል። ጀግናው ጃጋማ ኬሎ ፍቅረማርቆስ ደስታ በጻፈላቸው ታሪካቸው ውስጥ “ኦሮሞ የኢትዮጵያ ግንድ ነው” ሲሉ ነግረውታል። እውነታቸውን ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ በብዛት ትልቁ ኢትዮጵያዊ ብሔረሰብ ነው። የኦሮሞ ታሪክ ከተጻፈው በላይ ትልቅ ነው። የኦሮሞ ጎሳዎች ይተዳደሩበት የነበረው የገዳ

ስርዓት ዴሞክራሲ ለኦሮሞ ሕዝብ ባህሉ ነው ያስብላል። በኦሮሞ ባሕል የሰዎች አደረጃጀት የበላይና የበታች የሚለው ብዙም ተቀባይነት የለውም። በየትኛውም የገዳ ስርዓት የሥልጣን እርከን ላይ ያለን ሰው፣ የትኛውም ተራ ሰው መተቸት እንዲችል የኦሮሞ ባሕል ይፈቅድለታል። ይህ ዓይነቱ ባሕል የሕዝብ መሪዎች ከሕዝብ ትችት እንዳያመልጡ የሚያደርግ ስለሆነ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ያስፈልገናል።

የኦሮሞ ሕዝብ፣ ምንም እንኳን የብዛቱን ያህል ተጠቃሚ ባይሆንም የኦሮሞ ልጆች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሥልጣን ተቀናቃኝ ሆነው አልፈዋል። አንዳንድ ባለታሪኮች ‹ዘመነ መሳፍንት› የሚሉት የኢትዮጵያ ክፍለ ታሪክ በየጁ ኦሮሞዎች ኢትዮጵያ የተመራችበት ዘመን ነው ይላሉ። ያኔ መናገሻ የነበረችው ጎንደር ከተማ የሥራ ቋንቋዋ ኦሮምኛ ሆኖ ነበር። በሌላ ጊዜ ደግሞ ንግሥናውን ያገኙት የአማራ እና የትግሬ ገዢዎች ከኦሮሞ ጦረኞች ጋር ተስማምቶ ለማደር በጋብቻ መተሳሰርን መርጠዋል። ለምሳሌ ቴዎድሮስ ልባቸው እስኪጠፋ ያፈቅሯት የነበረችው ሚስታቸው የወሎው ኦሮሞ ራስ አሊ ልጅ ተዋበች ነበረች። አጤ ምኒልክ ያገቡት “የኢትዮጵያ ብርሃን” የምትባለውን ዘዴኛ የየጁ ኦሮሞ ሴት ጣይቱ ብጡልን ነበር። …ኦሮሞዎች ኢትዮጵያን በቀጥታ ባልገዙበት ዘመን በተዘዋዋሪ አዝዘውባታል።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንዳለመታደል ሆኖ ሕዝቡ ተመችቶት አልኖረም። የኦሮሞ ሕዝብም የዚሁ ገፈት ቀማሽ ነበር። መሪዎች በተገላበጡ ቁጥር ለራሳቸው ሲሉ ድሃውን ገበሬ ሲያንገላቱ ኖረዋል። ነገሥታቱ ለግል ጥቅማቸው ሲሉ ከጎናቸው ያልተሰለፈውን ሁሉ በኃይል ያጠቁ ነበር። ገበሬው ያመረተውን ቀርሶ የማካፈል ግዴታ ነበረበት። ግብር የበዛባቸው ገበሬዎች ከመማረራቸው የተነሳ የእህል ክምራቸውን የንጉሥ ወታደሮች ሊወስዱባቸው ሲመጡ እህሉ ላይ እሳት ለኩሰውበት ይሸሹ ነበር። ነገሥታት በመጡ፣ ነገሥታት በሄዱ ቁጥር ድሃው ሕዝብ እረፍት ሳያገኝ ኖሯል። የኦሮሞ ሕዝብ ከጥቂቶቹ የሥልጣን ተቀናቃኞች በስተቀር ቀሪው ያሳለፈው ታሪክ የፈተና ነበር። ሆኖም ግን ጭቆናው ዴሞክራሲያዊ (ሕዝባዊ) ያልሆኑ መንግሥታት ባሉበት ቦታ ሁሉ ብዙኃኑ ላይ የሚጫን ቀንበር ነው።

የኦሮሞ ሕዝብ በታሪኩ ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ከደቡብ ወደ ሰሜን በመስፋፋት ያልሰፈረበት የኢትዮጵያ ግዛት የለም። ከሁሉም ሕዝብ ጋር ተቀላቅሏል። በአንዳንድ ቦታዎች የራሱን ባሕልና ቋንቋ ሲያወርስ በሌሎች

ቦታዎች ደግሞ ከተስፋፋባቸው አካባቢዎቹ የቀድሞዎችን ነዋሪዎች ባሕልና ቋንቋ እንዲሁም ሃይማኖት ወርሷል፡፡ "ግማሽ ሲዳማ"፣ "ግማሽ ጉራጌ" የሲዳማንና የጉራጌን ባሕል የወረሱ ኦሮሞዎች ናቸው፡፡ የወሎ ኦሮሞዎች አማርኛ ቋንቋ እና እስልምና ሃይማኖትን ወርሰዋል፡፡ ራያ እና አዘቦዎች ትግርኛ ቋንቋና ክርስትናን ወርሰዋል፡፡ ...በዚህ መንገድ ኦሮሞዎች ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር ተሳስረዋል፡፡ ሶሾሎጂስቱ ዶናልድ ሌቪን የኦሮሞዎች እንዲህ ከሌሎች የመዋሐድ ችሎታ ትልቋን ኢትዮጵያ ፈጥሯል ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች አሁንም ከገኘው ጭቆና አልተላቀቁም፡፡ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ልክ እንደ ትላንቷ ኢትዮጵያ የመብት ጥያቄ ያነሱ ልጆች በኃይል ይጨፈለቃሉ፡፡ ይህንን ጭቆና ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆች በየራሳቸው መንገድ እየታገሉት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተባበረ ክንድ መታገል ባለመቻላቸው ጭቆናው ሊቆም አልቻለም፡፡ ብዙ የኦሮሞ ልጆች መፍትሔው የኦሮሚያ መገንጠል እንደሆነ ሊያምኑ ይችላሉ፡፡ ኦነግ በቀድሞው ብርታቱ ባይኖርም መንፈሱ አለ፡፡ ብዙዎች የኦነግ መንፈስ የሚሉት ይህንን "እንገነጠላለን" የሚለውን ጥያቄ ነው፡፡ ብዙዎች የተሰዉለት፣ ብዙዎች የታሰሩለት፣ ብዙዎች የተሰደዱለት ጥያቄ ይሄው ቢሆንም እስካሁን ለውጥ አላመጣም፡፡ በእኔ እምነት ጥያቄው ለውጥ ያላመጣው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ ትልቋን ኢትዮጵያ የመሠረተው የኢትዮጵያ ግንድ (የኦሮሞ ሕዝብ) እንደቅርንጫፍ እገነጠላለሁ ማለቱ ነበር፡፡ ሁለተኛ ጠላታችን የሆነውን ጭቆና ማሸነፍ የምንችለው በመተባበር እንጂ በመለያየት ባለመሆኑ ነው፡፡

የጣልያን ወረራን ያሸነፍነው በተባበረ ክንዳችን እንጂ በተነጣጠለ ኃይል አይደለም፡፡ አሜሪካ ዓለምን የምትመራው ክፍለ ሀገሮቿ ተባብረው በአንድነት ስለቆሙ ነው፡፡ አውሮጳውያን የአውሮጳ ኅብረትን የመሠረቱት የአሜሪካን ኃያልነት በኅብረት ለመቋቋም ነው፡፡ አፍሪካም ወደ ኅብረት እየሔደች ነው፡፡ በኅብረታችን ታሪካዊ ጠላታችን ጭቆናን ማሸነፍ ይቻላል፡፡ መገነጣጠል ግን ይብሱን ያደክመን ይሆናል እንጂ አይበጀንም፡፡ የኤርትራ መገንጠል ለኤርትራ ሕዝብ ነጻነት አላስገኘም፡፡ የደቡብ ሱዳን መገንጠል ለደቡብ ሱዳናውያን ሠላም አላመጣላቸውም፡፡ የሶማሊያ አንድ ብሔር መሆንና አንድ ሃይማኖት መከተል ከመበጣበጥ አላዳናቸውም፡፡ መዋጋት ያለብን ጭቆናን እንጂ ኅብረታችንን አይደለም፡፡

ኦሮሚያን እንገነጥላለን የሚለው ጥያቄ ታላቋ ኢትዮጵያን ለመሠረተው የኦሮሞ ሕዝብ ስድብ ነው፡፡ ሽንፈት ነው፡፡ ትግሉ መሆን ያለበት ጠንካራና

ነጻ ኢትዮጵያን ለማረጋገጥ ነው። የኦሮሞ ፖለቲከኞች ለዚህ ዓላማ (ሌሎች ፖለቲከኞች ባይመቿቸው እንኳ) የዴሞክራሲ ባሕላቸውን ተጠቅመው ሊታገሉት ይገባል እንጂ የገነቧትን ትልቋን ኢትዮጵያ ጥለው እንገነጠላለን ማለት የለባቸውም እላለሁ። የታላቅነት ምሥጢሩ ኅብረት እንጂ ነጠላነት አይደለም። በኅብረት እናሸንፋለን!

(Trickle-down)
እላይ ቤት ዘነበ፥ ዶፉን አረገፈ፣
ለሰፈሩ ሰዎች፥ ካፊያ አርከፈከፈ፣
እታች ሰፈር ያሉ፣
እያዩ ያዝናሉ፣
«ደመናው የኛ ነው፤ ዝናቡ የነርሱ፣
እኛን ጎርፉ በላን፥ እነሱ ሲርሱ፤»
እያሉ።

(ሰኔ 4፣ 2008)

«ወርቃማ እግሮችህ፥ ጭቃ እንዳይነካቸው፣
እሽኮኮ ሳድርግህ፥ ወለል ልሁናቸው፤…
ከመላ አካላቴ፥ ከከንቱ ልፋቱ፣
ይሻለኛል ለኔ፥ ለአንተ መሰ፡ጠቱ፤…

ወይም፣ ጫማዎችህ፥
እንዳይቆረቁሩህ፣
ቆዳዬ ተገፎ፥ ካልሲ ይሠራልህ፤

እንዲያውም፣
ከሥጦታ ሁሉ፥ የላቀ ሥጦታ፣
የኔን ድርሻ ጭምር፥ በሕይወት ገበታ፣
እንድትኖር ውሰደው፥ ቀሪ ዕድሜዬን ሁሉ፣
እንዳንተ ካልሆነ፣
ምን ይሠራልኛል፥ ኖሮ መንዛለሉ?»
ብዬ እንዳልደልልህ፣ ነጻነት ገብቶሃል፣
ጭቆና ጠልተሃል፤…
ከስኬትህና ከምኞትህ ጋራ፣
የወገንህ ብሶት፥ ብሶ አለያይቶሃል።

እንዳንተ ላለው ሰው፣
አንጀት የሚያርሰው፣
የራስ ምኞት ሳይሆን፣
የወገን ነጻነት መሆኑን ባወቀ፣
ከንቱ ልቦናዬ በቅናት አለቀ።

ስለዚህ ፈይሳ፣
ከራስ በላይ ንፋስ፥ ብዬ ለምተርት፣
ለከንቱው ሰው ለኔ፣
ወገን በሌለበት፣
ራስ እንደሌለ እንዳስተውልበት፣
ዓይንህ ይሁን ዓይኔ፣
ይህን አስተውዬ፥ አቤት እንድልለት፣
ወኔህ ይሁን የኔ።
መቀበል ነው እንጂ፣
መስጠት እንደሁ አላውቅ፣
ከንቱ አድናቂህ እኔ።
(መስከረም 4፣ 2009)

የመሐል አገር ሰው መልዕክት ለትግራይ ሰው!

(ነሐሴ 2007፤ ከቂሊንጦ ወኅኒ ቤት)

ትግራይ የኢትዮጵያ ገናና ታሪክ መሬቷ ላይ የተጻፈባት ክልል ናት። ብዙዎች "የኢትዮጵያ ራስ ናት" የሚሉት ለዚህ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ ወደኋላ 3000 ዓመት የሚያደርሰው የአክሱም ሥልጣኔ አሻራውን ትቶ የሔደው በትግራይ ክልል፣ አክሱም ከተማ ነው። ከአረቦች ተቀድቷል የሚባለውን የንግሥተ ሳባ ታሪክ "ክብረ ነገሥት" በሚባለው መጽሐፍ ተርጉመው ለዚህ ትውልድ ያኖሩልን የትግራይ ሊቃውንት ናቸው።

ሌላው ቀርቶ ኅብረ-ብሔራዊ ቅርስ የሆነንን የሳባ ፊደል ለመላው ኢትዮጵያዊ ያወረሱት የትግራይ ሊቃውንት ናቸው። ከኢትዮጵያዊነት ቀለሞች አንዱ የሆነው ያሬዳዊው ዜማ የተቀዳው ከትግራይ ምድር ነው። እነዚህና ሌሎች ያልጠቀስኳቸው እውነታዎች ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሚኮራባቸው ናቸው።

ኢትዮጵያዊነት በትግራይና በሌሎችም ሕዝቦች አኩሪ ታሪክ፣ ባሕልና ስርዓት ተገምዶ የተፈጠረ ማንነት ነው። ይሁን እንጂ ነገሥታት በመጡና በሔዱ ቁጥር ለራሳቸው ጥቅም አንዱን ወገን ከጎናቸው በማሰለፍ ሌላውን ወገን ያጠቁ ነበር። የአሁኑ የአገራችን ገዢዎችም፣ ይህንን ስልት እየተጠቀሙ በስጋና መንፈስ የተገነባውን ኅብረታችንን ሊያፈርሱብን ከጫፍ ደርሰዋል። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ለዚህ እኩይ ተግባር ትግራዋዮች ተባባሪ እንዳይሆኑ መጠየቅ ነው።

እንደሚታወቀው አምባገነኑን ደርግ ለመጣል በተደረገው ትግል የትግራይ ሕዝብ የከፈለው መስዋዕትነት ቀላል አይደለም። ይሁን እንጂ ደርግን ተክቶ ሥልጣን የያዘው ሕወሓት ቃል የገባውን ዴሞክራሲ እና ነጻነት ማምጣት ከብዶታል። እንዲያውም መልሶ ከደርግ ያልተናነሰ አምባገነን ሊሆን ተቃርቧል። ይህ አልበቃ ብሎት በትግራይ ሕዝብ ሥም የጥቂት ግለሰቦችን ጥቅም እያካበተ ነው። በዚህም የከፋፍለህ ግዛ ስልቱ በትግራይ ሕዝብ እና በሌሎቻችን መካከል የቅራኔ ግንብ እየገነባ ነው።

እኔ የመሐል አገር ሰው ነኝ። የመሐል አገር ሰው በሕወሓት ከፋፍለህ ግዛ ስልት ምን ያክል እንደተሸወደ አይቻለሁ። እኔም የችግሩ ሰለባ ነኝ። የመሐል አገር ሰው ትግራዋይ ሁሉ የሕወሓት አባል ይመስለዋል ቢባል የተጋነነ

ውሸት አይደለም። የፖለቲካ ቅሬታ ያለው የመሐል አገር ሰው ትግራዋዮች ፊት ችግሩን አያወራም። ሁሉም አንድ ናቸው ብሎ ይፈራል። ታዲያ በዚህ የመሐል አገር ሰው ሊወቀስ አይገባም። ምክንያቱም የሕወሓት ፖሮፖጋንዳ ሰለባ አድርጎታል። ሕወሓት ራሱን የትግራይ ሕዝብ ወኪል አስመስሎ ያቀርባል። በደል እና ጭቆና የበዛበት የመሐል አገር ሕዝብ፣ ሕወሓት የጨቆነው የትግራይ ሕዝብ የጨቆነው ይመስለዋል።

በዚህ ጉዳይ ከብዙ የትግራይ ልጆች ጋር ካወራሁ በኋላ ሌላ ነገር ተገለጸልኝ። ለካስ ትንሽ የማይባሉ የትግራይ ልጆች የመሐል አገር ሰው ይጠላናል ብለው ያስባሉ። የመሐል አገር ሰው በሕወሓት እና በትግራይ ሕዝብ መሐል ያለውን ልዩነት መረዳት ባለመቻሉ፣ የትግራይ ሰው በፍራቻ ከሕወሓት ሌላ አማራጭ እንዳይዝ አድርጎታል። ሕወሓት የጨቋኞች ቡድን ነው። አንድ ጨቋኝ ቡድን ደግሞ እየመረጠ አይበድልም። ለስልጣኑ እና ለጥቅሙ ያልተመቸውን ሁሉ ይበድላል። ስለዚህ የህወሓት ጨቋኝነት ለትግራይ ሕዝብም የሚቀር አይደለም። እኔ (የመሐል አገር ሰው) የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት የተባበረ የሚመስለኝ በስርዓቱ ተጠቃሚ ስለሆነ ይመስለኝ ነበር። ተሳስቻለሁ። ለካስ የእኛ ጥርጣሬ የፈጠረው ፍራቻ ነው።

ከትግራይ ልጆች ጋር በግልጽ ስንነጋገር የተረዳሁት ይህንን ነው። የትግራይ ሰዎች ሕወሓትን የሚመርጡ የሚመስሉት ሌላ የሚያምኑት ባለማግኘታቸው ነው። እርግጥ ነው፣ ጭቆናም ሆነ ነጻነት ለአንዱ ተሰጥቶ ለሌላው የሚነፈግ አይደለም። ኢትዮጵያ ሁላችንም በኅብረት የምንኖርባት አገር እስከሆነች ድረስ፣ የትግራይ ሕዝብ ነጻ ወጥቶ ሌላው ሳይወጣ አይቀርም። ሌላው እየተጨቆነ ከሆነ ደግሞ የትግራይም ሕዝብ እየተጨቆነ ነው ማለት ነው። እንደተረዳሁት ግን፣ ይህንን ሐቅ የሕወሓት ፕሮፖጋንዳ ሸፍኖታል።

ልክ የመሐል አገር ሰዎች የትግራይ ሰዎችን ሁሉ በሕወሓት አባልነትና ደጋፊነት እንደሚጠረጥሯቸውና እንደሚፈሯቸው ሁሉ፣ የትግራይ ሰዎችም የመሐል አገር ሰዎች ከሕወሓት ጋር ቀይጠው ያጠቁናል ብለው ይጠረጥራሉ፤ ወይም ይፈራሉ። ይህ በመካከላችን ትልቅ የፍርሐት ግድግዳ ፈጥሯል። ግድግዳውን በመተማመን ማፍረስ ደግሞ የእኔና የእናንተ ኃላፊነት ነው።

ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ ሽፍቶቹ፣ ወያኔዎች እና የትግራይ ሕዝብ የተለያዩ ናቸው ይላል። ወያኔዎቹ የነጻነት ታጋዮች ናቸው። ሽፍቶቹ ደግሞ በነጻነት ታጋዮቹ ሥም የሚነግዱት የአሁኖቹ ጨቋኞች (ሕወሓቶች) ናቸው። ዮናስ በላይ የትግራይ ሕዝብ የሽፍቶቹ ተባባሪ እንዳልሆነ የጻፈውን ከልቤ ተቀብየዋለሁ። የትግራይ ሕዝብ የሽፍቶቹ ተባባሪ ካልሆነ አሁን ብዙዎቻችን እያደረግን ያለነውን የነጻነትና የዴሞክራሲ ጥረት (ትግል) ይቀላቀላል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በእርግጥም ብዙ ትግራዋይ የነጻነት ታጋዮች ዛሬም አሉ። ነገር ግን ትግላቸው ከመሐል፣ ከምዕራብ፣ ከምሥራቅና ደቡብ አገር ሰዎች ጋር መቀናጀት አልቻለም።

እዚህ ጋር ከብዙ በእስር ከሚሰቃዩ የትግራይ ልጆች መሀከል አብርሃ ደስታን መጥቀስ ይኖርብኛል። አብርሃ የትም ቦታ የሚደረግ ጭቆና ይሰማኛል ብሎ የሚታገል ታጋይ፣ ምሁርና ምክንያታዊ የሐውዜን ልጅ ነው። አብርሃ ከማንም በላይ በትግራይ እና በመሐል ሀገር ሰው መካከል ያለውን አለመተማመን የሰበረ ሰው ነው። አብርሃ በኃይለኛ ብዕሩ ሕወሓትን ሲተች የተመለከቱ የመሐል አገር ሰዎች "ለካስ ትግራዋዮችም ሕወሓትን ይቃወማሉ" አስብሏቸዋል። ይህንን ሰው ግን ለነጻነት ታግያለሁ የሚለው ሕወሓት በመቃወሙ አስሮታል። አሁን በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ጠያቂ ተከልክሎ፣ በጥብቅ ክትትል እንደወንጀለኛ ታስሯል። በትግራይ ልጆች መስዋዕትነት ሥልጣን ላይ የወጣው ሕወሓት በሥልጣኑ ከመጡበት ለትግራይ ልጆችም እንደማይመለስ አብርሃ ደስታ ማሳያ ነው።

ሕወሓት በትግራይ ሥም እየነገደ ነው። የትግራይ ሕዝብ በሕወሓት ሥም መልካም ገጽታው እየጎደፈ ነው። ይህ ግን መቀጠል የሌለበት ታሪክ ነው። የትግራይ ሕዝብ፣ በተለይ የትግራይ ወጣቶች ይህንን ታሪክ ከሌላው ሕዝብ ጎን ቆመው ማስቆም አለባቸው። የትግራይ ሕዝብ ለጭቆና እምቢ ባይነት ሕወሓት በሚል ሥም ራሳቸውን ለሚጠሩት ሽፍቶችም መዋል አለበት።

ኑ! እምቢ አልጨቆንም እንበል።

"ወያኔ" vs "ሕወሓት" vs "ኢሕአዴግ"

(ግንቦት 14፣ 2008)

ወዳጄ ሶሊያና ሽመልስ [ውይይት መጽሔት ላይ ባሰፈረችው] "ትዝብቷ" እንዳጫወተችን "ወያኔ" በባሕር ማዶ የኢትዮጵያ መንግሥት ኦፊሻል ሥሙ ነው። እኔም ቆም ብዬ አሰብኩት። እዚህ ጋዜጣ እና ቴሌቪዥን ላይ አልወጣም እንጂ በተለይ በተቃዋሚዎች ንግግር ላይ መንግሥት "ወያኔ" ነው።

አንድ ነገሮችን ያለምክንያት ማድረግ እንደማይወድ የምከራከርለት ወዳጄ፣ በቀደም'ለት "ኢሕአዴግ ማለት አቁሜያለሁ" አለኝ። "ለምን?" አልኩት። "ኢሕአዴግ ብሎ ነገር የለም። ያለ፡ው ወያኔ ነው።" ወዳጄ የሕወሓትን በኢሕአዴግ ግንባር ውስጥም ይሁን በመንግሥት ውስጥ ተፎካካሪ የሌለውን ፈላጭ ቆራጭነት እያመላከተኝ ነበር።

'ወያኔ' የሚለው ቃል ለብዙዎቻችን 'ወንበዴ' ከሚለው ቃል ተለይቶ አይታየንም። ነገር ግን ትግራዋዮች 'ወያነ' ማለት 'የነጻነት ታጋይ' የሚል ትርጉም እንደሚሰጥ ይናገራሉ። እኔ በጽሑፎቼ ወያኔ የሚለውን ቃል መጠቀም የማልፈልግበት አንዱ ምክንያት ይሄው ነው፤ ለምን ለተወሰነው የማኅበረሰባችን ክፍል የማይመስል ትርጉም የሚሰጥ ቃል እጠቀማለሁ? ለምንስ በአንዲት ቃል ብቻ የተወሰኑ አንባቢዎች እገፋለሁ? ቃሉን ተጠቅሜስ ምን አተርፋለሁ?

አንዳንድ ቃላት የፈለገውን ያሕል ቀና ትርጉም ቢኖራቸው፣ ቃላቱ ዝነኛ የሆኑበት ዐውድ አስቀያሚ ከሆነ ዋጋ የለውም። ለምሳሌ "ኢትዮጵያ ትቅደም" የሚለውን ሐረግ ውሰዱ። ሐረጉ ምንም አሉታዊ ትርጉም የለውም፤ ነገር ግን ከደርግ ጋር ተሳስሮ ስለሚታሰበን ብቻ መልካም ትርጉም አይሰጠንም። ልክ እንደዛው 'ወያነ' የሚለው ቃል ሥሙ ጠፍቷል (derogatory ሆኗል)፤ ስድብ ሆኗል።

በዚህ በኩል፣ አሁን በግንቦት 20, 25ኛ ዓመት ዋዜማ ላይ ቆሜ ሳስበው ሕወሓት የታገለለት ዓላማ የምቀበለው ሆኖ አላገኘሁትም (በፊት የማስበው ሥልጣን እንዳባለጋቸው ብቻ ነበር)። ሕወሓት ደርግን ለመጣል ታግሏል አትበሉኝ። ሕወሓቶች የሸፈተቱት ጠላቴ ብለው በሠየሙት ሕዝብ ላይ ነው። ትግላቸውን ከትምህርት ቤት ሙግቶች እየመዘዙ ሥም ስለሰጡት ብቻ ለሕዝብ ታግለዋል የሚለውን ለመቀበል ታግዬ አልተሳካልኝም። The end

justified the means. ስለዚህ 'ወያነ' የምትለዋን ቃል የሚወዷትን እና 'በመጥፎ ስትተረጎም' ደስ የማይላቸውን ሰዎች ሳይ፣ የንዴታቸው ምንጭ 'ትግሉ ትክክል ነበር፣ ውጤቱ ነው ስህተት የምትል' ዓ/ነገር ውስጣቸው እንዳለች ይሰማኛል።

በሌላ በኩል፣ 'ወያኔ' የሚለውን ቃል በማነብነብ ብቻ የተቃዋሚነት ማዕረግ (ከሆነ) የሚያገኙ የሚመስላቸው ሰዎች መኖራቸው ያናድደኛል። ፖለቲካችን ከቃላት ጠረባ እንኳ ፈቀቅ አለማለቱ ያሳዝነኛል። 'ወያኔ' የሚለውን ቃል አልጠቀምም ስለው 'አካፋን አካፋ በማለት ራስህን ነጻ አውጣ' ያለኝ ወዳጄን አባባልንም የምወስደው እንደዚያ ነው። 'ወያኔ' የሚለውን ቃል እዚህ ጽሑፍ ላይ ደጋግሜ በመጠቀሜ ነጻነቴ በስንት ዲግሪ እንደጨመረ መረዳት ይከብደኛል።

ሌላኛው 'ወያኔ' የሚለውን ቃል የማልጠቀምበት ምክንያት እነዛን ወስላቶች (ኦሕዴድ፣ ብአዴን እና ደኢሕዴንን) አምባገነን ለመሆን ባይመቻቸው የአምባገነን ጉልቻ በመሆን ያደረጉትን አስተዋፅኦ ዕውቅና ላለመንፈግ ነው። ሕወሓት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግሥት ውስጥ እንዲህ ተፎካካሪ የሌላት ጡንቸኛ እንድትሆን ያደረጓት እነሱ ናቸው። ቤቱን እሳት የለኮሰው ብቻ ሳይሆን፣ ነዳጅ ያቀበለውም ዕኩል ጥፋተኛ ናቸው። 'ወያኔ' የሚለው ቃል - ለኔ - ይሄንን አይገልጽልኝም።

\- - -

እረግጦኝ ቆይቶ፥
ከፍ ብሎ ሲታይ፥
አናቴ ላይ ወጥቶ፣
ሰልችቶኝ ቀና ብል፥
ቢወድቅ ተንኮታኩቶ፣
ምንድን ነው 'ሚሆነው፥
የኔ ጥፋት ከቶ?
(ነሐሴ 5፣ 2008)

"የትግራይ ሕዝብ እና ሕወሓት
አንድ ናቸው/አይደሉም"!?

(ነሐሴ 27፣ 2008)

ጥያቄውም መልሱም ያናድደኛል። ነገር ግን ብሸሸውም አምልጬው አላውቅም። ዛሬም ከሁለቱም ወገን ሆነው ስህተትን በስህተት ለማረም እየተረባረቡ ያሉ ጓደኞች ስላሉኝ፤ ይሄ ጥረታቸውም በመሐላቸው ያለውን ልዩነት እያሰፋው እና እያከረረው ስለሆነ የበኩሌን ሳልል ማለፍ እንዳይቆጨኝ ነው መጻፌ።

የትግራይ ሕዝብ ሕወሓትን ይደግፋል፤ so what?

በኦሮሚያ እና በአማራ ኦሕዴድ እና ብአዴን ካላቸው ቅቡልነት ወይም ደኢሕዴን በደቡብ ካለው ተወዳጅነት ይልቅ ሕወሓት በትግራይ ያለው ቅቡልነት/ተወዳጅነት ይበልጣል። ሌላው ቀርቶ በትግራይ የሕወሓት ተቃዋሚዎች (ሁሉም ባይሆኑ እንኳ በጣም ብዙዎቹ) የሚያፀድቁለት/የሚያደንቁለት ገድል አለ። ለዚህ የሕወሓት በትግራይ ሰፊ ተወዳጅነት ማግኘት ደግሞ በቂ (?) ምክንያቶች አሉ፤ ፩ኛ) ሕወሓት እንደሌሎቹ ‹ፎርጂድ› አይደለም፤ ፪ኛ) በሌሎች ወገኖች ትግራዋዮችን ሁሉ በጥቅሉ በሕወሓት ዓይን እያዩ የመፍራት፣ የመጠርጠርና የመጥላት ገፊ ምክንያቶች አሉ፤ ፫ኛ) ሕወሓት በፌዴራል መንግሥቱ ውስጥ ያለውን የበላይነት ተጠቅሞ ለልኂቃኑ በረከት እያዘነበ ስለሆነ ብዙኃኑም ባይዘንብ ያካፋልኛል ብሎ የሚያስብበት ኅታች ምክንያት አለው፤ ፬ኛ) የኛው ናቸው በሚል የገዢነት ሥነ ልቦናን (entitlement) በነሱ በኩል መውረስ አለ።

በነዚህ ምክንያቶች ብዙኃኑ ትግራዋይ ሕወሓትን ይደግፋል (ብዬ አምናለሁ)። ጥያቄው ሲነሳ የትግራይ የዴሞክራሲ አራማጆች የሚሰጡት መልስ "የትግራይ ሕዝብ ሕወሓትን አይደግፍም" የሚል ነው። እርግጥ ያንን ማስረጃ መረጃ ይኖራቸው ይሆናል። እኔን የሚያሳምነኝ ግን እስከዛሬ አላገኘሁም። በኔ ግምት ግን መልሳቸው መሆን የነበረበት “እና ምን ይሁን?” የሚል ነበር። ከደገፈ በቃ፣ ምንም ማድረግ አይቻልም፤ የራሳችን ሕዝብ ነውና ድጋፉን መቀበል አልያም ከዚያ የተሻለ የሚደግፈው አማራጭ መስጠት ነው።

በተቃራኒው ግን ተቃዋሚው ለትግራይ ሕዝብ ምን ቃል ገባለት? ምንም። እንዲያውም ጥቂት የማይባለው የተቃዋሚው ወገን የትግራይ ልኂቃንን ከትግራይ ሕዝብ ጋር ጨፍልቆ ሲዝትባቸው መስማት አሁን-አሁን መብት

መስሏል። ስለዚህ፣ የትግራይ የዴሞክራሲ አራማጆች በአሁኑ ሰዐት በተከላካይነት ቦታ ራሳቸውን ማስቀመጣቸው የሚገርም አይደለም። የሚያዋጣ ባይሆንም።

በሌላ በኩል የሕወሓት ደጋፊ አንጋሾች ደግሞ አጋጣሚዋን በመጠቀም የተፈጠረውን ካልተፈጠረው ጋር በማራገብ (ሁሉም ሠላማዊ ሰው ላይ የሚሰነዘር ጥቃት ካለ ማውገዝ ሲችሉና ሲገ፡ባቸው) የትግራይ ተወላጆች ላይ ብቻ የደረሰውን ጥቃት እየነቀሱ በማውጣት እና የግጭቱን መልክ በመቀየር ቀዳዳውን ያሰፋሉ (ላልቶ ይነበብ)። ሕወሓቶች በአጋጣሚው የትግራይ ሕዝብ ጠባቂ በመምሰል ወትሮም ያላቸውን "ከነሱ ውጪ አማራጭ የለንም" የትግራዋዮች ብሒል የሚያገኙት ከራሳቸው ከተቃሚዎቹ ስህተት እና ስህተቱን እጥፍ ድርብ አጋንነው እና ቀጣጥለው ከሚነግሯቸው የሕወሓት አንጋሾች ነው።

"ሁሉም ፍረጃዎች (stereotyping) በጥቅሉ ትክክል ናቸው"

ትግራዋዮች ሕወሓትን ይደግፋሉ የሚለው አባባል የሚያበሳጫቸው ብዙ ትግራዋዮች አሉ። በሌላ ወገን "የትግሬ አኩራፊ እንጂ ተቃዋሚ የለም" የሚል ተረት ተፈጥሯል። ለኔ፣ እነዚህ በፍረጃው የሚበሳጩት ሰዎች ጥቂቶች እንጂ ብዙኃንን አይወክሉም (they are exceptions, not the norm)። ከዚህ በፊት ኦሮሞ ሁሉ ሲፋቅ ኦነግ ነው፤ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይ በሙሉ ሲፋቅ አማራ ወይም አማራናይዝድ ነው ተብሏል። እነዚህ አባባሎች ከባዶ ሜዳ የፈለቁ አይደሉም። የብዙኃን እውነታዎች ናቸው። በዚህ ግዜ 'ጥቂቶቹን' (exceptional) መሆን ፈታኝ ነው። ቢሆንም ግን የብዙኃኑን እውነታ የጥቂቶቹ ዲስኩር አይለውጠውም።

"ቤት የእግዚአብሔር ነው" የሚለው ብሒል ላይ "ኮንዶሚኒየም የገብረእግዚአብሔር" የሚል ተጨምሮበት ተረት ሆኗል። ያለ ምክንያት የሆነ ነገር አይደለም። በተለይ በአዲስ አበባ አዳዲሶቹ የኢኮኖሚ ዘዋ፡ሪዎች እና የንብረት ባለቤቶች ትግራዋይ መሆናቸውን ሕዝብ አይቶ የደረሰበት ጥቅል ፍረጃ ነው፤ (ለሁሉም ላይሠራ እንደሚችልም መረዳት ቀላል ነው)።

የትግራይ ተወላጆች በፌዴራል መንግሥቱ ውስጥ ያላቸው ያልተመጣጠነ ጉልህ ድርሻ፣ በመከላከያ እና ደኅንነቱ ውስጥ ያላቸው ፍፁም የበላይነት፣ በቢዝነሱ በጥቂት ግዜ የሚከብሩ ልኂቃኖቻቸው፣ ወዘተ… ከዚያም በላይ በኢሕአዴግ ሥር ያሉ ሦስቱ ፓርቲዎች የሕወሓትን ፍልስፍና እና ኢትዮጵያን የመግዛት ዓላማ እንዲደግፉ ተደርገው እንደተፈጠሩ ይታወቃል። ይሄ ሁሉ የትግራይን አንፃራዊ እና የትግራይ ልኂቃንን ፍፁማዊ ኢፍትሓዊ

ተጠቃሚነት ያረጋግጣል። እነዚህን ሐቆች ንቆ “ሕወሓት የሚያስተዳድረው ትግራይን ብቻ ነው፣ የጨቆነው የትግራይን ሕዝብ ብቻ ነው፣ የሚጠየቀውም ትግራይ ውስጥ ለፈፀመው ብቻ ነው..." የሚሉ መከራከሪያዎች ልዩነታችንን ያሰፉ እንደሆን እንጂ አያጠብቡትም።

"ትግራይ ለምን አታምፅም?"

ሸገር ለምን አታምፅም? የሚደርስበት በደል እና ግፍ ተሰፍሮ የማያልቀው እና በቁጥር ከትግራይ ሕዝብ የሚበልጠው የሶማሊ ሕዝብ ለምን አያምፅም? የአኙዋ ሕዝብ፣ የቤኒን ሕዝብ፣ የአፋር ሕዝብ ለምን አያምፅም? ለነዚህ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል እንጂ እርግጡን መናገር አይቻልም። ግን ሕዝብን የሚያሳምፅ አንድ ነገር አለ፤ ተስፋ አስቆራጭ ሲደመር ተስፋ ሰጪ ሁኔታ። ሁለቱም አብረው ካልታዩት የቱም ሕዝብ አያምፅም።

ለመዝጊያ መንደርደሪያ ከሦስት ዓመት በፊት ከአብርሃ ደስታ ጋር የተጨዋወትነውን ልንገራችሁ። አብርሃን የትግራይ የበላይነት ስለሚባለው ጠየቅኩት። እንዲህ አለኝ፤ “በፊት በትግራይ በየዞኑ ያሉ ኃላፊዎች የአድዋ ተወላጆች ነበሩ። ይሄ ለምን ሆነ ብዬ መጠየቅ ጀመርኩ። ብዙ በጠየቅኩ ቁጥር በኢትዮጵያ ባሉ የመንግሥት ኃላፊነቶች ለምን ትግራዋዮች ብቻ ኖሩ ይባላል። ሳየው እነዛ በሚኒስትርነት የተቀመጡ ሰዎች እኔና ወዳጅ ዘመዶቼን አይወክሉም። በየዞኑ ኃላፊ የሆኑትም የአድዋ ልጆች የአድዋ አካባቢ ሕዝብን አይወክሉም ማለት ነው አልኩ” እንዳለኝ አስታውሳለሁ።

አዎ። ሕወሓት መጀመሪያ "ትግል ላይ" ሳለ ሲሰነጠቅ በአድዋ፣ አክሱም እና ሽረ ሰዎች በተነሳ የሥልጣን ፉክክር ነው። ኋላ ላይም እነስየ ሲባረሩ ለሻዕቢያ ሰዎች ስሱ ልብ ባላቸው እና የትግራይ ብሔርተኝነትን በሚያስበልጡ ሰዎች መካከል በተነሳ ፉክክር ነው። የትግራይ ሕዝብ እና ሕወሓት አንድ ቢሆኑ እንኳ ሕወሓቶች (የጋራ ጠላት ካላዋደዳቸው በቀር) አንድ አይሆኑም።

የትግራይ ሕዝብ ከሕወሓት
የተሻለ “ወዳጅ" አለው?
(መጋቢት 6፣ 2006)

ከዚህ በፊት ’የትግራይ ሕዝብና ሕወሓት ምንና ምን ናቸው?’ ብዬ በጠየቅኩበት ጽሑፌ፤ እጅና ጓንት ናቸው ብዬ ነበር። ስለብዙኃኑ ትግራዋዮች እያወራን ከሆነ አሁንም ያው ነው መልሴ። በዚያ ጽሑፍ እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረስኩት ሕወሓት በሚያገኘው ሙሉ ድምፅ አይደለም፤ ያንን የሚያክል ድምፅ አዲስ አበባ ውስጥም የትም ፈጭቶ የትም አግኝቶታል። ሕወሓትን የሚወዱት አማራጭ አጥተው ነው ብዬ ነበር የተከራከርኩት። ምክንያቱም ደግሞ ትግራዋይ ያልሆነው ሰው ሁሉ ትግራዋዩን በሕወሓት መነፅር ስለሚመለከተው ተገፍቶ ነው ባይ ነበርኩ በዚያ ጽሑፍ (በዚህ ጽሑፍ ደግሞ ’ምን ዓይነት አማራጭ አጥቶ ነው?’ የሚለውን ነው የምጠይቀው)።

እርግጥ ይሄ ብቻ በቂ ምክንያት አይደለም። ሕወሓት ለሁለት ዐሥርት ዓመታት የዘራው የጥርጣሬ ፕሮፓጋንዳ ትግራዋዮች ሕወሓትን ባይወዱት እንኳ ለሌሎች የሚኖራቸው ጥርጣሬ ከሱ ጉያ እንዳይወጡ ያስገድዳቸዋል። (ፀረ-ቅኝግዛት ተንታኞች የጥገኝነት አባዜ የሚሉት ዓይነት።)
ይህንን ድምዳሜ የእነአብርሃ ደስታን የግለሰብ እና አረና ፓርቲን የቡድን ቁርጠኛ ትግል አጣቅሶ ፉርሽ ለማድረግ የሚሞክር አይጠፋም ብዬ እገምታለሁ። ችግሩ፣ የአረና ተቀባይነት ከጥቂት የልኂቃን ትግራዋዮች አልፎ ብዙኃኑ ውስጥ ሰርጿል ወይ የሚለው ጥያቄ ሲመጣ ነው።

ወደ ጽሑፌ ርዕስ ስመለስ ’ወዳጅ’ የሚለውን ቃል የተጠቀምኩበት ሕዝቡ የሚወደው ለማለት እንጂ ድርጅቱ የሚወደው ለማለት አይደለም። የአንድ ወገን ፍቅር ነው። አዎ፣ ሕዝብ ሆነን ስናስበው ሕዝቡ የሚወደው "የተሻለ" አማራጭ የለውም።

ሕዝብ ማለት (ቢያንስ ለዚህ ጽሑፍ) በደረሰበት የማኅበረሰባዊ ዕድገት (social evolution) ደረጃ ብቻ የሚያስብ፣ ስሜታዊ፣ ማኅበራዊ እንስሳ ማለት ነው። ሕዝብ ደምበጫ ውስጥ የኦሮሞ ሥም ይዞ የመጣ ሰው አይመርጥም፣ ሰላሌ ውስጥ የትግራዋይ ሥም ይዞ የመጣ ሰው አይመርጥም፣ አዲግራት ውስጥም እንደዚያው ነው። ይህ የወገን ፍለጋ እሳቤ የሠለጠኑት ዓለማትም ውስጥ የተቀረፈ ነገር አይደለም። አሜሪካ ውስጥ የሳኡዲ አረቢያ ሥም የያዘ ፕሬዚደንት ቢያንስ በቅርቡ አይመረጥም። ስለዚህ ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ ይህን የሕዝብ ፍላጎት ያሟላል። ያውም ነፍጥ አንስቶ ሕዝቤን ነጻ አወጣለሁ ብሎ ለመታገል እስከሚደርስ ጀብደኛ

ታሪክ (legend) በማሚላት። ስለዚህ ለአረና እና ሌሎችም አማራጭ ፖለቲካ ይዘው የትግራይን ሕዝብ ልብ ለመግዛት የሚታገሉ ፖለቲከኞች ዐብይ ፈተናቸው ይህንን የትግራዋዮች እና ሕወሓት የልብ ለልብ ግንኙነት የሚያሻክር ማስረጃ አሳይቶ፣ ከዚያ የተሻለ ነገር እንደሚያቀርቡ ማሳመን መቻል ነው። ይህንን ማድረግ ለጊዜው ከባድ ይመስላል።

ሕዝብ ጥቅሙን ወዳድ ነው። ፖለቲከኞችም የሚሚገቱት የሕዝብ ጥቅም በሚሚላት ሥም ነው። ስለዚህ የሕዝብ ጥቅም በማሚላትም ረገድ ቢሆን የሕወሓት ተፎካካሪዎች ቀላል ፈተና አይኖራቸውም። ሕዝብ ቅቡልነት (legitimacy) የሰጠው መንግሥት የሚያደርገውን ሁሉ ለጥቅሜ ነው ብሎ ያምናል። ሕወሓት ደግሞ በትግራይ ውስጥ የብዙኃኑ ቅቡልነት ይጎልበታል ብሎ ለመከራከር የሚያስችል በቂ መረጃ የለንም። ስለዚህ ተቃዋሚዎች ለሕዝቡ ጥቅም የሚበጅ የተሻለ አማራጭ ይዘው ከመወትወታቸው በፊት በሕዝቡ ውስጥ ቅቡልነት ለማግኘት መድከም አለባቸው። ቅቡልነት ደግሞ ሕዝቡ ቀድሞ የተቀበለውን ቡድን ሥም አፈር ድሜ በማስበላት ብቻ አይገኝም፤ እንዲያውም ይህንኛው ወደኋላ ሊባርቅ (backfire) ይችላል። ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ ሕዝባዊ ወካይነታቸውን እና ሕወሓት ከሕዝቡ ጉያ ወጥቶ ርቆ መሄዱን የሚያስመሰክሩባቸው ብዙ መንገዶችን መፍጠር አለባቸው።

ሌላውና የማይናቀው ሕወሓትን የተሻለ አማራጭነት በትግራይ ውስጥ የሚያጎላው ደግሞ ጉልቤነቱ ነው። የሕወሓት በኢሕአዴግ ውስጥም ሆነ በፌዴራል መንግሥት ውስጥ ከዕኩልነት የበለጠ ኃይል ሌላውን ሕዝብ፣ አራማጆችን ወይም የሕግ የበላይነት የሚያሳስባቸውን ሰዎች ያሳስብ እንደሆነ እንጂ ብዙኃኑ ትግራዋዮችን አያሳስብም። ሕዝብ ይወክለኛል የሚለው ቡድን የበላይ ኃይል ሲኖረው አይጠላም። የአረና ፈተናም ይኸው ነው። የትግራይ ሕዝብ አረና ከሕወሓት የተሻለ ፖለቲካዊ አማራጭ ይዞ መጥቷል ቢሎ ቢያስብ እንኳ ሕዝቡ በሌሎች ሕዝቦች ላይ የሚኖረውን [የጦር] ኃይል የበላይነት ያስነጥቀኛል ብሎ ካሰበ ለመምረጥ ይቸገራል። ይህ የትግራይ ሕዝብ የተለየ ባሕርይ አይደለም፣ የሁሉም ሕዝቦች ባሕርይ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ በአገራት መካከል ያሉ ሽኩቻዎችም ባብዛኛው በዚሁ የበላይነት ጥያቄ እንጂ የዕኩልነት ጥያቄዎች የተነሱ አይደለም።

ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ የሕዝብን የጋራ የአስተሳሰብ ፍሰት እንጂ የሕወሓትን እውነተኛ ወካይነት ያረጋግጣሉ ብሎ መደምደምም አይቻልም። ሕወሓት የሚደነቀው የሕዝቡን ሥነ ልቦና በመረዳት መጠቀሚያ ማድረጉ ነው። በዚህ መሐል ግን በርካታ ለማረም የሚቸግሩ ስህተቶችን ሠርቷል። ከስህተቶቹ ሁሉ የከፋው በፌደራሊቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ሌሎች

ሕዝቦች የትግራይን ሕዝብ በሕወሓት ዕዳ እንዲጠመድ (በጥርጣሬ ዓይን እንዲታይ) ማድረጉ ነው፣ በምላሹም የትግራይ ሕዝም ሌላውን የማያምን የሕወሓት ጥገኛ አድርጎታል። እነአረናም ይህንን ክፍተት በመሙላት እና የሁሉም ወገን ሕዝቦች ለዘመናት የነበራቸውን ትስስር ባለበትና በተሻለ የዕኩልነትና ወዳጅነት ስሜት ለማስቀጠል የሚያስችል ፕሮግራም መቅረፅ ይጠበቅባቸዋል። እስከዚያው ድረስ ግን ሕወሓት የትግራይ ሕዝብ የቅርብ ወዳጅ መስሎ መኖሩን ይቀጥልበታል።

“ቻው” ብዬሽ፣ “ቻው” ብለሽ፥
ስትሔጂ ከፍቶኛል፣
ጀርባዬን እያሰብኩ፥
ስሔድ ት’ዝዝ ይለኛል፣
እርምጃ ወደፊት፣ ሐሳብ ወደኋላ፣
ባስታወሱት ቁጥር፥ አንጀት የሚበላ፡፡

…ስን’ባክን ከርመን፥ በሕይወት መንገድ ላይ፣
ባለፈው ቀን ድንገት፥ ባካል ብንተያይ፣
እንዲህ ነው የተሰማኝ፣…
ውበትሽ ረግፎ፥ ክፉ ዓመልሽ ቀርቷል፤
ሳመልከው የኖርኩት፥ ‹አንቺ›ነትሽ ነጉዷል፤
እርጅና ክፉ ነው፥…
ያፈቀሩትን ሰው ‘ማንነት’ ይነጥቃል፡፡

‹እንዲያ የሚያኮራት፥ ያ ማማሯ የታል?
ክፉ ዓመሏን ችዬ አፍቅሬላታለሁ፥…
ብዬ ብል ማን፡ያምናል?›…

እንዲህም ብያለሁ…
‹ምን ነበር በወደድኩ፥ ያንኑ ዓመሏን፣
ውበት ሲኮበልል፥ ታማኝ አገልጋይዋን፤›
…ግን እንደ እውነቱ
የፍቅር ክፋቱ፣
በዓመል አሳ’ቦ፥ መልክ አምላኪነቱ፤
ውበትና መምሰል፥ ‘ማንነት’ ባይሆኑ፣
አያልፍም ነበረ፥ የፍቅር ዘመኑ፡፡
(ያልፋል)

(ሰኔ 2፣ 2006)

፱ - የትግል ስልት

"ጨዋ" ነዎት "ባለጌ"?

(ነሐሴ 2007፤ ከቂሊንጦ ወኅኒ ቤት)

ሐምሌ 27/2007 ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች እና ቀናኢ-ፍትሕ ለሆኑ ሰዎች በሙሉ የመርዶ ቀን ነበር፡፡ ስለ ሠላማዊነታቸው የተመለከታቸው በሙሉ የፈረደላቸው፣ ባንድ ወቅት መንግሥትም በወኪሉ በኩል ሲደራደራቸው የነበሩ፣ ለሦስት ዓመታት ያክል በሕግ የበላይነት አምነው ችሎት ፊት የሠላማዊነታቸውን ማስረጃ ሲደረድሩ የቆዩት (በተለምዶ በሚጠሩበት ሥማቸው) የሙስሊሞች ጉዳይ መፍትሔ አፈላላጊ "ኮሚቴዎች" እስከ 22 ዓመት የሚደርስ የፅኑ እስራት ፍርድ ተጣለባቸው፡፡ ይህንን ዜና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን (ኢብኮ) ከ7፡30 የቀን ዜና እወጃው ጀምሮ ሲለፍፈው ነበር፡፡ ከዜናው ጋር በማነፃፀሪያነት የቀረበው ሌላ ዜና ግን ግቡን ስላልመታ ይመስላል ማታ አልተደገመም፡፡ ያልተደገመው ዜና በተመሳሳይ አንቀፅ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ስለተፈረደባቸው ሰዎች ነው፡፡ እነዚህኞቹ መሣሪያ ታጥቀው የተወሰኑ ሰዎችን ገድለዋል፡፡ ሆኖም እንደ ኢ.ብ.ኮ. ዘገባ "የቅጣት ማቅለያ በማስገባታቸው" 14 ዓመት ተፈርዶባቸዋል፡፡ ዜናዎቹን ያዳመጡ ሰዎች ግን ማነፃፀር የቻሉት የሠላማዊነት ቅጣት መክበዱን ነበር፡፡

ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ "Military and militarism in Africa: the case of Ethiopia" ባሰኙት ጥናታቸው ላይ እንዲህ ይላሉ፡-

> *"በመካከለኛውዘመን እንዳየነው [ጨዋ] ማለት መሣሪያ ታጣቂ ማለት ነበር፡፡ ኋላ ላይ ግን ትርጉሙ ተለውጦ መልካም ፀባይ ያለው ማለት ሆነ፡፡ በተመሳሳይ፣ የቃሉ ተቃራኒ የሆነው "ባለጌ" የሚለው ቃልም የሚወክለው ጭሰኛውን (ማለትም መሣሪያ የማይታጠቀውን) ነበር፡፡ አሁን የዚህም ቃል ትርጉም ተለውጦ መጥፎ ፀባይ ያለው ማለት ሆኗል፡፡" (እራሴው እንደተረጎምኩት)*

እንግዲህ ኢሕአዴግም የሚያስበው በቀደመው ዘመን የ‹ጨዋ› እና ‹ባለጌ› ትርጉም ነው ማለት ነው፤ ለእርሱ መሣሪያ ከታጠቀ ይልቅ ሠላማዊ

ይባልግበታል። (‹ይባልግበታል› በአሁኑ ትርጉም!) ስለዚህ አቀጣጡም በዚያው መሠረት መሆኑን መግቢያ አንቀፁ ያመለክታል።

የአሁኒቱ ኢትዮጵያ ገዢዎች (‹አመራሮች› አላልኩም፤ አይመጥናቸውም) የመንግሥትን ሥልጣን ከተቆጣጠሩበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁን (ለሁለት ዐሥርት ዓመታት) ሠላማዊ ትግሎችን በፅኑ ተቃውመዋል። እንዲያውም "የሚችለን ካለ በትጥቅ ትግል ይሞክረን" የሚል መፈክር በተደጋጋሚ አስደምጠዋል። ዓላማቸው ግልጽ ነው። ያዋጣናል፣ እናሸንፍበታለን የሚሉትን የትግል ሜዳ እየመረጡ ነው። የኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችስ? ገዢው በመረጠላቸው ሜዳ (battlefield) ቢገጠሙት ይሻላል ወይስ ሠላማዊነትን የሙጥኝ ቢሉ? የትኛው ያዋጣል? የትኛው ይቀላል? ከሕወሓት ምን መማር ይቻላል? አምባገነኖች እንዴት ሥልጣን ላይ ይሰነብታሉ?

ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ከመፈለጌ በፊት ነገሩ ሁሉ ለለውጥ ነው እና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ‹ለውጥ› የሚባለውን ነገር ልበይን። ‹ለውጥ› ማለት በዚህ አገባቡ ‹ወደ ሕዝባዊት፣ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ የሚደረገው ሽግግር› ነው።

አመፃዊ የትግል ስልት ያዋጣል?

ሠላማዊ ያልሆነ ትግል በሙሉ የትጥቅ ትግል አይደለም። አመፃዊ የሚለውን ቃል የተጠቀምኩት ከትጥቅ ትግል ወዲያ ሠላማዊ የማይባሉ ስልቶችንም እንዲያካትትልኝ ስለፈለግኩ ነው። በዚህ መስፈርት አመፃዊ ትግል በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ፣ ከአገሪቱ ታሪካዊ ሁነትም፣ ከዓለምዐቀፍ ተሞክሮዎችም በመነሳት ያዋጣል ወይ የሚለውን እንጠይቃለን። ለዚህ ጥያቄ በዚህ ጽሑፍ ሰጥቼ የማልፈው ጉዳይ በተነሳ ቁጥር የሚመጡልኝን መልሶች ነው።

1ኛ - የዴሞክራሲ መንገድነት

ዴሞክራሲ በየትኛውም መመዘኛ መንገድ እንጂ መድረሻ አይደለም። ይህም ማለት አንድ አገር የሆነ የጊዜ ነጥብ ላይ ‹ዴሞክራሲያዊ ሆነ፤ በቃ አበቃ! › የሚባልበት ፊሊጥ የለም። ዴሞክራሲያዊነት ማለት ሁሉንም ሕዝባዊ ጥያቄዎች በዴሞክራሲያዊ መንገድ (በብዙኃን አመራርና ሕዳጣን መብት ጥበቃ፣ በሕግ የበላይነት፣ በወቅታዊ እና ነጻ ምርጫ…) መፍታት መቻል ነው። ይህ የማይቆም፣ መድረሻ የሌለው ጉዞ ነው። የአመፃ ትግል ዴሞክራሲን ማምጣት አልሞ ሲደረግ ከመነሻው ዴሞክራሲን እንደመድረሻ

ስለሚቆጥረው ስህተት ይሆናል። በአካሄድም ቢሆን አመፃዊ ዴሞክራሲያዊነት ስለማይኖር ምናልባት ነባሪውን ፍፁማዊ አምባገነን በለዘብተኛ አምባገነን (Benevolent dictatorship) መተካት ካልቻለ በቀር አመፃ ለዴሞክራሲ መንገዱን እንደሚከፍት ዋስትና አይሰጥም።

2ኛ - "ውሻ ወደትፋቱ ይመለሳል"

ምንም እንኳን "ነጻ አውጪዎች" በብረት ነጻነትን፣ በእኛ ጉዳይ ዴሞክራሲን እናመጣለን ብለው ቢሸፍቱም - የሚያውቁትም፣ የሚለምዱትም የብረት (አፈሙዝ) ሕግን ነውና - በዓለም እንደታየው መጀመሪያ ላይ ዴሞክራሲያዊነትን ለማስመሰል ቢሞክሩም ቆይተው ግን በብረት ሥልጣናቸውን ማቆማቸው የተለመደ እውነት ነው። ቀደም ሲል የጠቀስነው የባሕሩ ዘውዴ ጥናት እንዲህ ይላል፦

> *"...ሥልጣን የራሱ የሆነ የማይሻር አመክንዮ አለው፤ ለአብዮታዊ ዲስኩር አያጎበድድም። ስለዚህ በሕዝባዊ ድጋፍ ተመርኩዞ በአፍሪካ ግዙፍ ከሆኑት ወታደራዊ ሠራዊቶች አንዱን የደመሰሰው ኢሕአዴግ የራሱን ሥልጣን ለማስጠበቅ መልሶ ወታደራዊ ኃይል ላይ መንጠላጠሉ የሚያስገርም አይደለም።..."*

በዚህ ረገድም ስናስበው አመፃዊ ትግል እኛ ‹ለውጥ› የምንለውን እንደሚያመጣልን ዋስትና መስጠት አይቻልም።

3ኛ- "እኛ" እና "እነርሱ" እንሆናለን

አመፃዊ ትግል (በተለይ የትጥቅ ትግል) አንድን ሕዝብ ቢያንስ ለሁለት ይከፍለዋል። (እንደ ሶሪያ ዓይነቶቹ ከዚያም በላይ ከፋፍለውት አሳይተውናል።) ስለዚህ በትግሉ ወቅት የወገን እና የጠላት እየተባሉ የሚፈረጁ የአንድ ሕዝብ ሁለት ክፍሎች፣ ከትግሉ በኋላም በዚያው ዓይን መተያየታቸው አይቀሬ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው አሁንም በገዢዎቹ የሕወሓት ልኂቃንና ደጋፊዎቹ መካከልና በሌሎች ኢትዮጵውያን መካከል ያለው ልዩነት (ያውም ከ25 ዓመት በኋላ) የሁለትዮሽ ነው። ቂም የያዘ እና ያስያዘ ሁለት ወገን ካለ፣ ቂመኛው መልሶ ስለሚሸፍት እንደመጀመሪያው ሁሉ ‹ንጉሥ ያለ ለውጥ› እንደትልቻ እያቀያየረ ይሔዳል። ዴሞክራሲ መሠረታዊ ሕዝባዊ ስምምነት (consensus) ስለሚጠይቅ አመፃዊ ትግል ዴሞክራሲን እንደማያስገኝ ይህም አንድ ማሳያ ነው።

4ኛ- ለፍቶ መና

ሕወሓት የዱር ትግሉን ጨርሶ ቤተ መንግሥት ሲገባ ከገጠሙት ፈተናዎች አንዱ "ታጋዮቹን ምን ላድርጋቸው?" የሚለው ነው። 17 ዓመት ሙሉ በዱር በገደሉ ሲዋደቁ ከርመው የሥልጣን በትሩን ሲጨብጡ፣ የተለያዩ የመንግሥት ኃላፊነት ቦታዎችን በሙያ ብቃት ብቻ ለመሸም (አላሰቡም እንጂ) ቢያስቡም ለትግሉ ስኬት የመማርና የሙያ ልምድ የማካበት ዕድላቸውን ያባከኑትን ሰዎች "አፍንጫችሁን ላሱ" ሊሏቸው አይችሉም። ምንም እንኳን ታጋዮቹ የሚታገሉት ለዓላማ (cause) ነው ቢባልም፣ ድል ሲቀናቸው የዓላማው ፍሬ የመጀመሪያው ተቋዳሽ ለመሆን ከመጓጓት አይተርፉም። ሰው ናቸውና። ስለሆነም በወታደራዊ አስተዳደር (ማለትም በማዕከላዊነት እና ከላይ ወደታች የትዕዛዝ መሥመር በሚሠራ የአስተዳደር ዘዬ) የሠለጠኑ ሰዎች ከወረዳ እስከ ጠቅላይ ሚንስትር ቢሮ ሲገቡ ዴሞክራሲን (ከታች ወደላይ የሚወሰንበትን አሠራር) ያመጣሉ ብሎ መጠበቅ አይቻልም። ያውም ደግሞ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የኃላፊነት ቦታዎችን እንዲይዙ ለምርጫ ቢቀርቡ በዕውቀትና ልምድ ማነስ ስለማይመረጡ ከታገሉለት ስርዓት ጋር ቅራኔ ውስጥ በመግባት እንደማያጨናግፉት ምንም ዋስትና የለም። ይህም አመፃዊ ትግልን ለዴሞክራሲ እንዳይመች ያደርገዋል።

5ኛ - ዴሞክራሲን ይኖሩለታል እንጂ አይሞቱለትም!

ሕውሓቶች ለ17 ዓመት ሲታገሉ፣ 60ሺ ነፍስ መስዋዕት ሲያደርጉና ከዚያ በላይ ሲገድሉ፣ ተስፋ ያደርጉ የነበሩት እንደ ሃይማኖት ያመልኩት የነበረውን ማርክሳዊ-ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም ነበር። ትግሉ ድል ሲቀናው ግን የታገሉለት ርዕዮተዓለም "አለፈበት"። በዓለም እንደ መንግሥት ፀንቶ ለመኖር "ነጭ ካፒታሊዝም"ን መቀበል ነበረባቸው። እንደ ገብሩ አሥራት ንግግር ‹አልባንያ፣ አልባንያ እየተባለች እንደ ሞዴል የተጠራችው አገር ትግሉ ሳይጠናቀቅ ብትንትኗ ወጣ›። ሕወሓትም የሞተለትን እና የገደለለትን ስርዓት ንቆ "የዘመኑን" ያዘ። እንግዲህ የአመፃ ትግልን ከሚያስፈሩ ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው። ምናልባት ለሚለወጥ ርዕዮተ ዓለም መልሶ የማይገኝ የሰው ልጅ ነፍስ መስዋዕት ማድረግ ይጠይቃል። ለሰዎች አንፃራዊ ሠላም እና ደኅንነት ሲባል መሞት ያውም በገፍ - ምክንያታዊ አይደለም።

በለውጥ የትግል ዓለሞች ሁሌም (እንደየተመልካቹ) ጠርዘኛ (radical) እና መሐከለኛ (moderate) አቋሞችን ይዘው የሚንቀሳቀሱ ሰዎች አሉ። አመፃዊውንም ሆነ ሠላማዊውን ትግል የሚመርጡትን ሰዎች እንደ ጠርዘኛ የሚቆጥሯቸው አሉ። ራሳቸውን አማካይ ብለው ይጠራሉ። የሚሰጡትም ምክንያት ሠላማዊውም ሆነ አመፃዊው ትግል ለየብቻ መቆም አይችልም

የሚል ነው። በኃይል ሥልጣኑን የያዙ ሰዎች ከሠላማዊዎች ጋር መደራደር እና ለለውጥ ፈቃደኞች የሚሆኑት አማፂዎቹን በመፍራት ነው ይላሉ። ይህንን እንስማማበት ቢባል የአማፂዎችን ሚና ወስዶ የሚጫወተው ማን ነው? በግሌ እኔ የምኖርለት እንጂ የምሞትለት ግብ የለኝም። አመፃዊ ትግል ደግሞ ለመግደልም ብቻ ሳይሆን ለመሞትም መዘጋጀትን ይጠይቃል። በበኩሌ እኔ የማልገባበትን የትግል መሥመር ሌሎች እንዲገቡበት የምመክርበትም ሞራል የለኝም። እንዲያውም እስከ መሞት በሚደርስ ወኔ የሚታገሉ ሰዎች ካሉ ለሠላማዊ ሜዳ ይበልጥ ውጤታማ መሆን ይችላሉ ብዬ አምናለሁ።

በሠላማዊ እና በአመፃዊ ትግሎች መካከል ያለው ልዩነት የሕይወትና የሞት ያክል ነው። በሠላማዊ ትግል ትልቁ ፈተና እስር ነው። አልፎ፣ አልፎ ሞት የሚከሰትባቸው ሠላማዊ ትግሎች ቢኖሩም የአመፃዊ ትግሎችን ያክል እልቂት የሚያስከትሉ አይደሉም። ጌታቸው ማሩ ‹ደርግን ለአመፃ ትግል መጋበዙ ይብስ አረመኔ ያደርገዋል› የሚል ስጋት እንደነበረው ሕይወት ተፈራ “Tower in the sky” ላይ ገልፃዋለች። ስጋቱ አልቀረም፤ ለኢሕአፓ የ‹ነጭ ሽብር› ምላሽ ደርግ በ‹ቀይ ሽብር› አገሩን በደም አጠበው። ትግሉ በሁለት ገዳዮች መካከል ስለነበር ኃያሉ ገዳይ አሸንፎ ወጣ። በድኅረ ምርጫ 97ም የቅንጅት መሪዎች (በተለይ እነ ልደቱ) ስለ ጆርጂያና ዩክሬን የቀለም አብዮት የቀሰቀሱትን ሕዝብ እንዴት ሠላማዊ መሆን እንዳለበት ስላልነገሩት፣ በድንጋይ ውርወራ እና ጎማ በማቃጠል ብሶቱን ገለጸ፤ አጋጣሚው ግን ለኢሕአዴግ ሕዝባዊ ብሶቱን ለማፈን ብቻ ሳይሆን ለዘለቄታውም እንዳይደገም ዕድሉን እንዲዘጋ መንገድ ጠረገለት። አሁንም የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴች አሉ። በተለይ በኦነግ፣ ኦብነግ እና ግንቦት ሰባት ሥም የተጨፈለቁ ሠላማዊ ታጋዮችን ቁጥር ወኅኒ ቤቱ ይቁጠረው። እንግዲህ መደራደሪያ ይሆናል የተባለው የአመፃ ትግልም ሠላማዊውን ለማደናቀፊያ እያዋለ ነው ማለት ነው።

አመፃዊው ትግል ውስጥ (በተለይ በትጥቅ ትግሉ) ሌላም ፈታኝ ጉዳይ አለ። ሕዋሓት ለድል የበቃው “የሻቢያ የትሮይ ፈረስ ሆኖ ነው” የሚሉ አሉ። ሕወሓት ጫካ እያለ የማይደራደርባቸው ከነበሩ አቋሞቹ ውስጥ “የኤርትራ ጉዳይ የቅኝ ግዛት ነው፤ እና የሚፈታው በነፃነት [መገንጠል] ነው” የሚለው አንዱ ነበር። ሻቢያ ያን ሕልሙን በሕወሓት አሳክቷል፤ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ አማፂዎች ወዳጅ ሆኗል። ሻቢያን እንደ ኢትዮጵያ ወዳጅ መቁጠር የሚቻልበት መሥፈርት አይታየኝም። አዲሶቹ አማፂዎችም እንደ ሕወሓት የሻቢያ የሌላ አጀንዳ የትሮይ ፈረስ እንዳይሆኑ እሰጋለሁ።

ሠላማዊ ትግል ስንል?

ሠላማዊ ትግል ደርዘ ብዙ ትንቅንቅ ነው፡፡ አንዳንዶች ‹ሕጋዊ መንገዶችን ብቻ መጠቀም ነው› ብለው ያምናሉ፤ ነገር ግን በዚህ የማይወሰንበት ጊዜ አለ፡፡ ሠላማዊ ትግል ከነፍስ ማጥፋት፣ አካላዊ ጉዳት ከማድረስ እና ንብረት ከማውደም መቆጠብን ብቻ የሚጠይቅ በመሆኑ ነው ‹ሠላማዊ› የተባለው፡፡ ለምሳሌ ሕዝባዊ እምቢተኝነት (Civil disobedience) አንድ የሠላማዊ ትግል ዘርፍ ነው፡፡ ማርቲን ሉተር ኪንግ (ትንሹ) "ኢ- ፍትሐዊ ሕጎች፤ ሕጎች አይደሉም" ይል ነበር፡፡ በዚህ ፍልስፍና ነው ለሕግ አለመታዘዝ የሚወለደው፡፡ ለምሳሌ በአፓርታይድ ስርዓት ውስጥ ያሉትን አግላይ ሕጎች በሠላማዊ ትግል ለመቃወም የአፍሪካ ብሔራዊ ኮንግረስ ከነደፋቸው ስልቶች አንዱ ለአግላይ ሕጎች የማይታዘዙ (እና በዚያ ሳቢያ ለመታሰር ፈቃደኞች የሆኑ /እስር እንደትግል/ የሚቆጥሩ) ሰዎችን መልምሎ ማሰማራት ይገኝበታል፡፡ ተግባሩ ሠላማዊ ነው፤ ግን ሕጋዊ አይደለም፡፡ ሕጉ ኢ-ፍትሐዊ ነውና፡፡

በኢትዮጵያ፣ በአብዛኛው የሚስተዋሉ ከኢ-ፍትሓዊ ሕጎች ይልቅ የሕግ የበላይነት ማጣት ነው፡፡ የማበላለጥ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ኢ-ፍትሓዊ ሕጎች የሉም ማለትም አይደለም፡፡ ሕዝብን ለማደንቆር (እንዳይነቃ) የወጣው የመያድ ሕግ እና ሁሉን ነገር ሽብር ያሰኘው የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግጋት በዚህ ረገድ ሳይጠቀሱ አይታለፉም፡፡

ሆኖም የሕግ የበላይነትን ባለማክበር የሚፈፀሙ ጥፋቶች ይህንን አምባገነን ስርዓት የበለጠ ይገልጹታል፡፡ ለምሳሌ መደራጀት ይፈቀዳል (በሕግ)፣ በተግባር ግን ይደናቀፋል፡፡ ይህንን በሠላማዊ መንገድ መታገል የሚቻለው ከስርዓቱ ጆሮ ጠቢዎች በላይ የሆነ (ነገር ግን በሕግ ያልታወቀ) ሠላማዊ ድርጅት በመፍጠር ነው፡፡ የፕሬስ ነጻነት በሕግ ተፈቅዷል፤ በተግባር ግን አይቻልም፡፡ ከቴክኒካዊ ማደናቀፊያ እስከ ጋዜጠኛ ማሰር በሚደርሱ ሕገወጥ ተግባሮች ነው ይህ የሚሆነው፡፡ ዘመኑ ይህን ለማሸነፍ ምቹ ነው፡፡ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ከአፈናውም ከእስሩም በላይ የሆነ (በእነዚህ እርምጃዎች የማይደናቀፍ) የመረጃ ማቅረብ ወይም ሕዝባዊ ንቃት የመፍጠር ሥራ መሥራት ድርጅታዊ መረብ መፍጠር ይቻላል፡፡ የአገራችን የሠላማዊ ትግል ፈቀቅ አለማለት አማራጭ መንገድ ከማጣት ይልቅ ያለመፈለግ የፈጠረው ይመስላል፡፡ ኢሕአዴግ "ሠላማዊ ትግል አልፈልግም" እያለ ቢሆንም እየሔዱ ፊት ለፊት መላተም ብቻ (አስፈላጊ ቢሆንም) በቂ አይደለም፡፡ አስፈላጊነቱ የስርዓቱን ሕገ-ወጥነት ለማሳየት ሲሆን በቂ የማይሆነው በዚህ የኢሕአዴግ ባሕሪ ፊት ለፊት መላተም ለውጥ ማምጣት ስለማይችል ነው፡፡ ፊት ለፊት መላተም ሲበዛ፣ መጠቃት ስለሚበዛ ሰዎች

ትግሉን ከመቀላቀል ይልቅ በፍርሓት እንዲርቁት ያደርጋል፡፡ ይህን ችግር፣ በትጥቅ ትግል ቋንቋም ቢሆን ሲያስረዱ አቶ ገብሩ አሥራት (‹ሉአላዊነትና ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ› ላይ) እንዲህ ብለዋል፦

> *“አንድ አባት ገበሬ ‹ልጆቼ እንታረዳለን፣ መሬት ቀውጢ ትሆናለች እያላችሁ አትቀስቅሱ፡፡ የዚህ ዓይነት ቅስቀሳ ሰው ወኔው እንዲሞት፣ ተስፋ እንዲቆርጥና አንገቱን እንዲደፋ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ እናቸንፋለን፣ ተቃርበናል፣ አይዟችሁ፣ በርቱ፣ ብላችሁ ብትቀሰቅሱ ይሻላል› ብለው መክረውን ነበር፡፡”*

ቢያንስ በእኔ እምነት፣ ያውም ለቆረጠ እና ዓላማውን በቅጡ ለሚያውቅ ሰው ሠላማዊ ትግል ከአመፃዊ ይልቃል፡፡ እርግጥ የፍትሕ እጦት ትውልድ እየበላ የምንታገስበት አንጀት አይኖረን ይሆናል፡፡ ሆኖም አመፃዊ ትግል ፍትሕ የምናገኝበትን መንገድ ማሳጠር አይችልም፡፡ የካርል ማርክስ “There is no short cut to history” (‹ለታሪክ አቋራጭ መንገድ የለውም› ብሒል) እዚህ ይሠራል፡፡ ሚስተር ኪንግ በሠላማዊ ትግል ጎዳና ሦስት ደረጃዎች አሉ ይላል፡፡ *መንቃት* (Awareness)፣ *መደራጀት* (Organize) እና *መተግበር* (Action) በቅደም ተከተል የሚመጡ የሠላማዊ ትግል ሒደቶች መሆናቸውን ይናገራል፡፡ አሁን ችግር የሆነብን ተግባሩ እየቀደመ ነው፡፡ ጥቂት የነቁ እና የተደራጁ (ሁለቱንም ያሟሉ) አደባባይ ሲወጡ ወይም በሆነ የትግል ተግባር ሲጠመዱ ገዢው በቀላሉ ይጨፈልቃቸዋል፡፡ ለተመልካችም ሕዳጣን ያስመስላቸዋል፡፡ በሠላማዊ ትግል ሕዝብ ኃይል የጨበጠውን ገዢ የሚያሸንፈው በብዛት ነው፡፡ ብዙዎችን በኃይል መጨፍለቅ አይቻልም፡፡ እንግዲህ ስለመደራጀት ቀደም ሲል ለመጥቀስ ሞክሬያለሁ፤ አስፍቶ ማሰብ የእያንዳንዳችን ቀጣይ ድርሻ ይሆናል፡፡

መንቃት ለምንና ለማን?

‹ለውጥ› የሚፈልጉ ለውጥ አማጪዎች (Activists) ሕልማቸውን ብቻቸውን ይዘውት ምንም ማድረግ አይችሉም፡፡ ለሌሎች ማጋራት አለባቸው፡፡ በዚህ መንገድ ነው ተከታይ ማፍራትም ሆነ፣ ያፈሩት ተከታይ ሕልማቸውን ማስቀጠል የሚቻላቸው፡፡ ሕልማቸው ከራሳቸው አልፎ ሌሎች ላይ መጋባት ከቻለ ነው ከራስ-ሥዩምነት ወደ ሕዝበ-ሥዩምነት መሸጋገር የሚችሉት፡፡ ብዙኃን የሚመሩት/የሚሳተፉበት ትግል የመክሸፍ ዕድሉ አነስተኛ ነው፡፡ የ1953ቱን ስዒረ መንግሥት እንደምሳሌ እናስታውሰው፡፡ በወቅቱ የንጉሡ ደጋፊዎች እና የስዒረ መንግሥቱ ደጋፊዎች ያደረጉትን ውጊያ ጣልያናዊው አንጄሎ ዴል ቦካ (la negus ባሰኙት መጽሐፋቸው ላይ) እንዲህ ተርከውታል፦

"ለሰዐታት የዘለቀ ውጊያ መንገዱ ላይ ተካሒዶ ነበር፣ ሕዝቡ ግን በወታደሮቹ መካከል የነበረውን ጦርነት ያለውንና (indifference) ይመለከተው ነበር።" (እንግሊዘኛው ትርጉም ገጽ 260)

በዚህ ታሪክ የምናስታውሰው ብዙኃኑ ለአመፃ የሚኖረውን ምላሽ ብቻ ሳይሆን ውጊያው ለምን እየተካሔደ እንደሆነ እንኳን ግንዛቤ እንዳልነበረው ነው። ደራሲው ሲቀጥል፦

"...ግርማሜ ንዋይና ወርቅነህ ገበየሁ [የወቅቱ የደኅንነት ሹም]፣ ሁለቱም በአሮጌው መንግሥት መውደቅ ብዙ ነገር ማግኘት እንደሚችል በቂ ግንዛቤ አለው ብለው የአዲስ አበባን ሕዝብ በመገመታቸው የምር ስህተት ፈፅመዋል።"

ይሁን እንጂ የንጉሡ መንግሥት ከዚያ በኋላ የቆየው 13 ዓመታት ብቻ ነው። ያ በኢትዮጵያ ታሪክ በአግባቡ የተደራጀ እና ዘመናዊ ሠራዊት እና የደኅንነት ተቋም የመሠረተው የመጀመሪያው መንግሥት የወደቀው ያለመሣሪያ ጩኸት ነው። በሕዝቡ መንቃት እና በሐሳብ መበለጥ። ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ ‹ሕዝቡ/ተማሪዎች "መሬት ላራሹ" ሲሉ በወቅቱ መሬት የባላባቶች በመሆኑ መንግሥት በሐሳብ ተበለጠ... ወደቀ› ይላል። አንጄሎ ዴል ቦካ ለዚህ ለውጥ የስዒረ መንግሥቱ ሙከራ አስተዋፅዖ እንደነበረው አልሸሸገም። ከሙከራው በኋላ ሕዝቡ ነቃ ይላል፦

"[ከዚያ በፊት የነበሩት] ሌሎች አማፂዎች፣ እነባልቻ፣ ጉግሳ ወሌ፣ እና ኃይሉ ተ/ሃይማኖት በማዕከላዊው ኃይል ላይ ያመፁት በጥላቻ፣ በቀል ወይም ምኞት ብቻ ተነድተው ነበር። ለአገሪቱ ያቀረቡት አማራጭ ራዕይ አልነበራቸውም።" (ገጽ 264)

የስዒረ መንግሥቱ ሞካሪዎች ግን ነበራቸው። የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ያንን ራዕይ ከአፈሙዝ ፋክክሩ ነጥለው መመልከት ችለዋል። በወቅቱ አመፁን የደገፉ 200 ተማሪዎች ሰልፍ ወጡ እና ከትምህርታቸው ታገዱ። ቆይተው ግን ይቅርታ ጠየቁና ወደ ትምህርት ገበታቸው ተመለሱ።

እኔ (የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ) የቅድመ እና ድኅረ ምርጫ 97ን ጉዳይ እንደዚህኛው ስዒረ መንግሥት ሙከራ ነው የምመለከተው። ያኔ ተማሪዎቹ ይቅርታ ጠይቀው ትምህርት ቤት ሲመለሱ የተከሰተው ዝምታ የተቀረፈው የአብዮቱ ሰሞን ነው። ዝምታቸው የተገፈፈው ሕዝባዊ ንቃቱን ተከትሎ ነው። ሕዝብ የነቃ'ለታ ምንም እንኳን ወታደራዊው ጁንታ (ደርግ)

ቢነጥቃቸውም ለውጥ መጥቶ ነበር፡፡ አሁንም ሕዝብ መንቃት ያለበትን ያህል ሲነቃ ለውጥ ይመጣል፡፡ እኛ ዘብ ሆነን መጠበቅ የሚኖርብን የደርግ ዓይነቱ የለውጥ ሌባ እንዳይዘርፈን ነው፡፡

እስከዚያው ከሕወሓት መማር

የሚቀናቀኑትን አካል በቅጡ መረዳት ግማሹን መንገድ መምጣት ነው፡፡ የሕወሓትን ታሪክ፣ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና ወዘተርፈ መለየት ለሠላማዊ ትግላችን ሰፊ አስተዋፅዖ ይኖረዋል፡፡

ትምህርት አንድ፤ ዛፉ እንዳይነብጥ፥ ችግኙን ማረቅ

ሕወሓት መራሹ የኢሕአዴግ መንግሥት በአውራ ፓርቲ ሥም፣ አሀዳዊ ፓርቲ ስርዓት እየዘረጋ ነው፡፡ መላ አገሪቱ ከቀበሌ እስከ ፓርላማ በአንድ ዓይነት አስተሳሰብ የተቃኙ፣ የአንድ ፓርቲ ሰዎች እንዲሞሉት አድርጓል፡፡ ይህ አመል ኢሕአዴግ የመንግሥት ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የመጣ ይመስላል፡፡ ግን አይደለም፡፡ ሕወሓት ከቀድሞ ወዳጁ ሻዕቢያ የተማረው "በአንድ ሜዳ ሁለት ኃይል አይኖርም" የሚል አባባል አለው፡፡ በዚህ ፍልስፍና ሻዕቢያ ጀብሃን አጠፋ፡፡ ሕወሓት ደግሞ ግገሓት(?)፣ ኢዴኃ (EDU)፣ ኢሕአሠን በኃይል ደምስሷል፡፡ ሕዋሓት ደርግን ከመደምሰሱ በፊት አምባገነኑን ደርግን እንወጋለን ብለው ግን ደግሞ ከሱ በጥቂቱ የተለየ የፖለቲካ ፍልስፍና ይዘው ከነጉ የተሰለፉ ኃይሎችን አጥፍቷቸዋል፡፡ ይህ የጫካ አመሉ ያደገበት ሕወሓት (ኢሕአዴግን ለብሶ) ከተማ ሲገባ የቱንም ያክል "ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ አማራጭ የሌለው አማራጭ ነው" እያለ ቢፎክርም፣ የተለየ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ወገኖችን መታገስ አልቻለም፡፡

ሕወሓት/ኢሕአዴግ የተለየ አስተሳሰብ የሚያራምዱ ወገኖችን ቀርቶ በውስጡ የሚከሰቱ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን እንኳን መታገስ አይችልም፡፡ ትግል ላይ በነበሩት ጊዜ የተነሳው የመጀመሪያው ‹ሕንፍሽፍሽ› (ቀውስ) ‹የአሸዓ (አክሱም፣ ሽረ እና አደዋ) ሰዎች የሥልጣን የበላይነት (ልክ አሁን የትግራይ ልሒቃን የሥልጣን የበላይነት በፌደራል መንግሥቱ ውስጥ በዛ እንደምንለው) ፓርቲያችን ላይ እየታየ ነው› የሚል አቤቱታ ያቀረቡ አባላቱን በማስወገድ ነው የተጠናቀቀው፡፡ በ1993 በተፈጠረው ቀውስ ደግሞ የሉአላዊነት ጥያቄ ያነገቡ አባላቱን የውስጥ ሕገ-ደንቡን (ሕወሓትን በማዳን ስም) ሽሮ፣ ምርጫ ቦርድ ባለበት አገር በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ማሕተም የተፃፈ ደብዳቤ ነበር ያሰናበታቸው፡፡ ይህ ባሕል ከጫካ ተከትሏቸው የመጣ ባሕል ነው፡፡ የውብማር አስፋው ‹ፊኒክሷ ሞታም ትነሳለች› ባለችው መጽሐፏ እንዲህ ትለናለች፡-

“በሕወሓት ደንብ መሠረት አንጃ መፍጠር እስከ ሞት የሚደርስ ቅጣት ያስከትል ስለነበር፣ የሕወሓት ፖሊት ቢሮ ይህንን ሲያስቀምጥ በማኅበሩ አመራር ውስጥ የማይፈልጋቸውና የሚጠላቸው የአመራር አባላት ሊኖሩ እንደሚችሉ ያመለክት ነበር።…” (ገጽ 112፣ ጋዜጠኛ ዮናስ በላይ እንዳጣቀሰው)

እነዚህ ችግሮች ሥር ሰደው ነው የአሁኑን አማራጭ ሐሳብ የማይቋቋም ኢሕአዴግ የፈጠሩት። ይህንን የ1993ቱ የሕወሓት ቀውስ ወቅት ከፓርቲው ከወጡት ታጋዮች መካከል አረጋሽ አዳነ ለጥሕሎ መጽሔት በሰጠችው ቃለምልልስ ከሥር ከሥሩ ባለመታረሙ የመጣ ጣጣ ነው በማለት ከታሪክ እንድንማር ትመክረናለች፦

“እነዚህ ሁሉ [ጥያቄዎችን በኃይል የመጨፍለቅ] ችግሮች ገና ድሮ ከመፈጠራቸው፣ [ሥ]ር ከመስደዳቸው በፊት ቀደም ብለን ለዚህ ሁሉ መሠረት የሆኑትን ችግሮች […] አስተውለን ከሥር ከሥር ወይም ደረጃ በደረጃ እየታገልናቸው ያለመምጣታችን አሉታዊ ፍፃሜ ነበር ብዬ አስባለሁ።” (ገጽ 77፣ ዮናስ በላይ፣ የትግራይ ሕዝብ፣ ወያኔዎቹና ሸፍቶቹ)

የቀድሞ የሕወሓት ታጋዮች ፀፀትም ሆነ የአሁን ታሪኩ የሚያስተምረን ዴሞክራሲ መንገድ እንጂ መዳረሻ አለመሆኑን ነው። በዴሞክራሲያዊ መንገድ ያልመጣ ኃይል ዴሞክራሲን ሊያመጣ አይችልም።

ትምህርት ሁለት፤ ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር መቁረጥ

ሕወሓት ደርግን ወግቶ ለድል እንዲበቃ በተለይ ሁለት ዘዴዎች ረድተውታል። ሠላማዊ ታጋዮች እነዚህን ዘዴዎች በራሳቸው መንገድ ተርጉመው ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የመጀመሪያው ደርግን እራሱን መጠቀሚያ ማድረግ ነው። ሕወሓት የደርግን ክፋት ለራሱ ተቀባይነት መግዣ በማድረግ ተጠቅሟል። ለምሳሌ በትግል ወቅት የማረካቸው ወታደሮች ‹ተሐድሶ› ካሠለጠናቸው በኋላ ሁለት አማራጭ ይሰጣቸው ነበር። አንድ ከጎን ተሰልፈው ደርግን እንዲወጉ፣ አልያም ወደቀዬአቸው እንዲመለሱ። የትኛውንም ቢመርጡ ሕዋሓት ያተርፋል። ተመላሾቹ የገጠማቸውን ለቀሪው ወታደር ስለሚናገሩ ወታደሩ በወኔ ለመዋጋት ይለግማል፤ እነርሱም ተመልሰው ሕወሓትን አይወጉም። የደርግ አባል የነበሩት ሌ/ኮሎኔል ደበላ ዴንሳ ተመላሽ “ምርኮኞችን መልሶ ማዝመት” ደርግን እንዲሸነፍ ያደረጉት ብለው ከዘረዘሯቸው 13 ነጥቦች አንዱ

አድርገውታል። ሠላማዊ ታጋዮች ተቀናቃኜ የሚሉትን አካል ከጎናቸው ማስለፍ የሚችሉበትን ስልት መንደፍ አለባቸው። በሐሳብ በመብለጥ!

የሕወሓት ወገን የነበሩ በመሆናቸው ብቻ በለውጡ እንደማይቀጡ ዋስትና ይፈልጋሉ፤ ሁለተኛ በለውጡ ሐሳብ መማረክ አለባቸው።

ሁለተኛው፣ የሕዋሓት ብልሐት ደርግን የሚዋጋበትን መሣሪያ ከራሱ ከደርግ ማግኘት መቻሉ ነው። የአሁን ሠላማዊ ታጋዮች ሕዋሓት (ኢሕአዴግን ለማሸነፍ ወይም በዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና ስርዓት ለመተካት የራሱን መሣሪያዎች መጠቀም መቻል አለባቸው።) ሕገ መንግሥቱን፣ የመንግሥት መዋቅሮችን፣ የመንግሠት ሠራተኞችን፣ ወዘተርፈ ለሠላማዊው ትግል የሚፈይዱበትን ዘዴ መቀየስ ይበጃል።

ትምህርት ሦስት፤ እያዝናኑ መታገል

ሕወሓት ትግሉ ሕዝቡ ውስጥ ሥር እንዲሰድ ከረዱት መንገዶች መካከል ሳይጠቀስ የማይታለፈው ኪነትን መጠቀም መቻሉ ነው። በተለይ በዘፈን ረገድ የተሠሩ ሥራዎች በወኔ የሚቀሰቅሱ፣ ሕልም እንዲያልሙ የሚረዱ እና የራሳቸውን የዘመን ወግ (Folklore) መፍጠር የቻሉ ነበሩ። ለምሳሌ ‹ንገሪን እንደ ሐለፋይ . . . › የሚለው (በትርጉሙ "ንገሪኝ እስቲ እናቴ፣ ወዴት ነው የሔደው አባቴ?" የሚል) የማሚት እና ብርሃነ (ሐለፋይ) የቅብብሎሽ (duet) ዘፈን፣ አሳዛኝ እና የተከፈለው መስዋዕትነት ለሚመጥነው ዋጋ መሆኑን የሚዘክር ዘፈን ነው። ይህንን ዘፈን ትግሪኛ ተናጋሪ ጓደኞቼን "ንገሪኝ እስኪ እናቴ፣ ለዚህ ነበር ወይ የሞተው አባቴ?" በሚል ምፀት እንዲቀይሩት ጠይቄያቸው በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካ ቀርቷል።... ጥበብ (ኪነ ጥበብም ይሁን ሥነ ጥበብ) በጥቅሉ ከአመፃዊ ይልቅ ለሠላማዊ ትግል መሣሪያ መሆን ይችላል። በዚህ ረገድ በዓለማችን ብዙ ትምህርት የሚሆኑ ሥራዎችን አይተናል። የማርያ ማኬባ ፀረ-አፓርታይድ ዜማዎች፣ የቦብ ማርሌይ የነጻነት ሬጌምቶች፣... እና በአገራችንም የቴዲ አፍሮ "ጃ ያስተሰርያል" ከነዚሁ ተርታ ይመደባል። የቀድሞዎቹን የጦር ሽለላዎችና ቀረርቶዎች በመጠቀም ያውም ለዚህ ትውልድ ጆሮ በሚስብ መልኩ በሂፕሆፕ (ራፕ) መልኩ፣ የለውጥ ሰባኪ ግጥሞች ተጽፈውለት መሥራት ይቻላል። ኬናን የተባለ ካናዳ-ሶማሊያዊ ራፐር ይህንን አሳይቷል።

በጥበብ ረገድ የሚደረጉ ሠላማዊ ተጋድሎዎች በዘፈን ብቻ ሊገደቡ አይገባም። በሥዕል፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በቲያትር፣ ፊልም፣ ካርቱኖች እና ሌሎችም አማራጮች ቀርበው ሁሉንም እንደየፍላጎቱ ሊደርሱት ይገባል።

የአምባገነኖች ድጋፍ ማግኛ ምንጭ

ጂን ሻርፕ የዐረቡ ዓለም አብዮት የሚባለውን እንዲቀጣጠል ነዳጅ ጨምሯል የተባለለትን "ከአምባገነንነት ወደ ዴሞክራሲ" የተሰኘ መጽሐፍ ጽፏል፡፡ መጽሐፉ ውስጥ አብዛኛዎቹ አስረጂ ምሳሌዎች አምባገነኖች መሠረታቸው ሕዝብ መሆኑን ነው የሚነግሩን፡፡ ፐ/ር መስፍን ወልደማሪያም በተደጋጋሚ "ጭቆና የሚሸከመው ትከሻ ይፈልጋል" የሚሉን ይህንን ነው፡፡ አምባገነኖች ሕዝብ ጭቆና ለመሸከም ትከሻውን እንዲሰጣቸው ብዙ መንገዶችን ይጠቀማሉ፡፡ የ‹ሠላማዊ ትግል 101› ጸሐፊ ግርማ ሞገስ ሦስት ነገሮችን ይጠቅሳሉ፦ እነዚህም ፈቃደኝነት፣ ፍራቻ ወይም ግዴለሽነት ናቸው፡፡ የሚኪያቬሊ ፍልስፍናም (‹The Prince› ላይ እንደተገለጠ) "ነገሥታት በመወደድ ብቻ ሳይሆን በመፈራትም ነው የሚኖሩት"፤ ከተቻለ ወዶ እና ፈቅዶ የሚተባበር፣ የሚታዘዝና ለምዶበት የሚታመንላቸውን፤ ይህ ሲከብድ ትልቅ ሠራዊት በመገንባት ወይም የደኅንነት መረባቸው ትልቅ፣ ብልህ እና አስተማማኝ እንደሆነ በማስወራት ሕዝባቸውን እያስፈራሩ ትከሻው ላይ ይወጣሉ፡፡ ይህ ብቻውን ስለማያቆማቸው ያገኙትን ሞኝ ለማታለል ተቀባይነት የሚያስገኝላቸውን ዘዴም መዘየዳቸው አይቀርም፡፡

መንግሥታት ሥልጣን ላይ የሚቆዩት የተወሰነ ቅቡልነት (Legitimacy) እስካላቸው ድረስ ነው፡፡ የቀድሞ ነገሥታቶቻችን ራሳቸውን "ሥዩመ እግዚአብሔር" በማለት ቅቡልነትን ለማግኘት ይጥሩ ነበር፡፡ ጳጳሳቱም (ሲሦ ቀላዳቸውን ለማግኘት) ይህንኑ ለሕዝቡ ይሰብኩ ነበር፡፡ ለአሁኖቹ መሪዎች ይህ አያዋጣም፡፡ ሕዋሓት የዘውግ ብሔርተኝነትን (ዕኩልነትን አስጠብቃለሁ በሚል ሥም) ቅቡልነትን ሊገዛበት ሞክሮ ነበር፤ ብዙም አላስኬደውም፡፡ አሁን ደግሞ "ልማታዊነት" የተባለውን ጨብጧል፡፡ ድሃ ሕዝብ ኢኮኖሚያዊ ተስፋዎች እንደሚያዘናጉት በመረዳት "መጀመሪያ ዳቦ" እያለ እስከዚያው የመጨቆኛ ካርድ ለማግኘት ይጥራል፡፡ በዚህ አካሔድ ዊኒ ማንዴላ ተናግረውታል እንደሚባለው "ወፍራም ባሪያ" መፍጠር ይፈልጋሉ፡፡

አምባገነኖች፣ ልዩ ፍጡሮች?

አምባገነንነት የሚፈጠረው ሰዎች ያልተገደበ ሥልጣን ሲገጥማቸው ራሳቸውን መግዛት ስለሚከብዳቸው ነው፡፡ ብዙዎች የዓለማችን አምባገነኖች መጀመሪያ ምስኪን "ነጻ አውጪዎች" ነበሩ፡፡ ዳግማዊ ዐፄ ቴዎድሮስን እንኳን ብንወስድ ዐፄነት ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት የድሃ አባት ነበሩ፤ ያውም ከበዝባዥ ፊውዳል ባለሀብቶች እየዘረፉ ለድሃ የሚያከፋፍሉ ዓይነት፡፡ ኋላ በትረ ሥልጣኑን ሲይዙ ግን በገዳይነት የሚወዳደራቸው አጡ፡፡ "የአገሬ

ሕዝብ ስራት ያዝ ብለው እምቢ አለኝ" እያሉ በስርዓት ማስያዝ ሥም ሕዝቡን ፈጁት፡፡ ይህን ሲያደርጉ ግን ውስጣቸው የነበረው ቅንነት እየወቀሳቸው "አቤቱ አምላኬ፣ እባክህን ግደለኝ እና ሕዝብህን ነጻ አውጣ" እስከማለት ደርሰው እንደነበር እንግሊዛዊ እስረኞቻቸው ጽፈዋል፡፡ ሰዎች ሠላማዊነትን መምረጥ የሚኖርባቸው ከራሳቸው ድብቅ አውዳሚነት ራሳቸውን መጠበቅ ስለሚከብዳቸው ነው፡፡

በኢትዮጵያ - አምባገነንነት ባሕል ነው ማለት ይቻላል፡፡ አምባገነኖቻችን በቁልምጫ ነው የሚታወሱት፡፡ "መንጌ"ን መጥቀስ ይቻላል! አባወራዎች በቤተሰቡ ላይ ፍፁማዊ ሥልጣን አላቸው፡፡ መምህራን በክፍል ተማሪዎቻቸው ላይ ፍፁም የበላይ ተደርገው ይሾማሉ፡፡ አለቆችም በምንዝሮቻቸው ላይ እንዲያው ናቸው፡፡ ሁሉም አቅሙ በፈቀደው ላይ ፍፁማዊ ኃይልን እና የበላይነትን መጠቀምን ባሕላችን ያበረታታል፡፡ ዘበኛው በደጅ ጠኚው ላይ፣ አሠሪው በሠራተኛዋ ላይ ኃያል ነው፡፡ ዕድሩ ሰብሳቢው አይለወጥም፤ የትምህርት ቤት ዳይሬክተሩ እስኪሞት አይሻርም፡፡ የተቃዋሚ ፓርቲው ሊቀመንበር አይቀየርም በዚህ ባሕል ውስጥ እየኖርን የአገር መሪ ብንቀያየርም "ተረኛ ጨቋኝ" እንጂ ዴሞክራሲን አናመጣም፡፡

የአምባገነኖች አንድ ዓይነትነት

አምባገነን አገር ወይም ብሔር የለውም፡፡ ቋንቋ የለውም፡፡ ሁሉም ያልሠለጠኑ ሕዝቦች ውስጥ ያለ ዕዳ ነው፡፡ አማር ቦንጎ ጋቦንን ለ42 ዓመታት ገዝቷል፡፡ የመንግሥት ኃላፊነት ቦታዎችን ለቤተዘመዱ አከፋፍሏል፡፡ ልጁ እሱ ሲሞት ሥልጣኑን ወርሷል፡፡ ሴት ልጁ የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ኃላፊ ነበረች፡፡ ባሏ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፡፡ በሥሙ ያልተሠየመ ነገር የለም፤ ቦንጎ ዩኒቨርስቲ፣ ቦንጎ አየር ማረፊያ፣ ቦንጎ ሆስፒታል… ሌላው ቀርቶ የትውልድ ከተማው ቦንጎቪል ተብላለች፡፡ እኛም አገር ከቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ጀምሮ እስከ መለስ ዜናዊ እየሆነ ያለው ይኸው ነው፡፡

የኮትዲቯሩ ሆፎኤት-ቦይኚ 6 ጊዜ የፕሬዚዳንት ምርጫን አሸንፏል፡፡ ያውም 99.7 በመቶ አማካኝ ድምፅ አግኝቶ! የአንዱን አምባገነን ታሪክ መስማት፣ የሌላኛውን እንደመስማት ነው፡፡

አምባገነኖች ሥራቸውን ልባቸው ስለሚያውቀው ይፈራሉ፡፡ የደኅንነት ሠራተኞቻቸውም ፍርሐታቸውን ለማረጋጋት የውሸት መረጃ ይሰጧቸዋል፡፡ የዩጋንዳው ኢዲ አሚን ዳዳ ለምሳሌ "ሕዝቡ በፕሬዚዳንቱ ፍቅር አብዷል" የሚል የደኅንነት ሪፖርት ደርሶት እንደነበር ተነግሯል፡፡ አሁን፣ አሁን

የአገራችን ባለሥልጣኖችም በጋዜጣ መግለጫዎቻቸው የሚያሳዩት ባሕሪ እንዲህ ዓይነት ሪፖርት የደረሳቸው በሚመስል መልኩ ነው።

የራሺያው የቦልሼቪኮች ፓርቲ (እ.ኤ.አ. በ1917 ጀምሮ እስከ 1940 ብቻ) በ23 ዓመታት ውስጥ ከ24 የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላቱ የቀረው አንድ ጆሴፍ ስታሊን ብቻ ነበር። 8ቱ ተገደሉ፣ 7ቱ "በተፈጥሮ አጋጣሚ ሞቱ" ተባለ፣ 7ቱ "የደረሱበት ጠፋ" ተባለ፣ አንዱ ታሰረ። ቀሪው አንድ አምባገነን ብዙ ሚሊዮኖችን ፈጀ። ይህንን ስታሊኒስታዊ አመራር (ተቀናቃኞችን ማጥፋት) ከልባቸው ያሳደሩት አቶ መለስ ዜናዊ እንደስታሊን ማዕከላዊ ኮሚቴውን ባዶ ከማድረግ ይልቅ፣ ታዛዥ አላዋቂዎች እንዲሰበሰቡበት አደረጉ። ልዩነቱ ትንሽ ነው። ነገር ግን ሞት ቀደማቸው። የቀሩት አባላት የሚያደርጉት ጠፋቸው። ስለዚህ የሟቹን ሌጋሲ ("ትሩፋት") እናስቀጥላለን በማለት በመለስ የተሾሙለትን ዓላማ እያስፈፀሙ ነው።

ምርጫ በአምባገነኖች አገር

በአምባገነኖች አገር ምርጫ ማለት አሸናፊውን (ገዢውን) አጅቦ ለድል ማብቃት ማለት ነው። ወይም አምባገነኖቹ የሚፈልጉት እንደዚያ እንዲሆን ነው። ‹The Dictator› የተሰኘው ፊልም ነገሩን ግልጽ አድርጎታል። አላዲን የተባለው የዋዲያ መሪ የራሱን ኦሎምፒክ አዘጋጅቶ፣ ራሱ ተወዳድሮ ያሸንፋል። ውድድሩን ተኩሶ የሚያስጀምረው ራሱ ነው። የሚቀድሙትን ተወዳዳሪዎች እየተኮሰ ይጥላቸዋል። መጨረሻ ላይ ራሱ ያሸንፋል። ምርጫ ለአምባገነኖች እንዲህ ቀላል ነው። ተወዳዳሪዎቹ አሸንፌ ድሌ ይከበርልኛል ብለው ከሚያስቡ የአላዲንን ሽጉጥ የጨበጠ እጅ ቢይዙ የተሻለ ያዋጣቸው ነበር። የአምባገነን መንግሥት ተፎካካሪ ፓርቲዎች የአምባገነንነት መንግሥት እጅ መያዝ አለባቸው።

አገዛዙ ወይም የአገዛዙ ልሒቃን በምን ጥገኛ እንደሆኑ መለየት እና ያንን መንፈግን እንደትግል መሣሪያ (መደራደሪያነት) መጠቀም ያስፈልጋል። የእኛ አምባገነኖች ተፎካካሪዎቻቸውን የሚጥሉት በየትኛው እጃቸው ነው? የኃይል ምንጫቸው ምንድን ነው? ሠላማዊ ትግሉ ሊሠራው የሚጠብቀው የቤት ሥራ ነው።

ግብታዊ ጩኸት፣ ለቅስፈት…

ሕወሓት/ኢሕአዴግ አምባገነን መሆኑ ታውቋል። ምርጫ እንደሚያጭበረብር ታውቋል። የሲቪል ማኅበራት ፓርቲዎችን ገቢ በማሳጣት፣ መሪዎቻቸውን

በማሰር፣ ውስጣቸው ክፍፍል በመፍጠር እንደሚያዳክማቸው ታውቋል። ነጻ ፕሬሶችን እንደሚያደናቅፍ ታውቋል። ሠላማዊ ትግሉ ከነዚህ በላይ ሆኖ የሚያሸንፍበትን መንገድ (Strategy) መንደፍ አለበት። ነገር ግን ያልታወቀም ነገር አለ። ኢሕአዴግ እስካሁን አልተፈተነም። ለቀላሏ ፈተና (ድኅረ ምርጫ 97 ለገጠመው ተግዳሮት) የሰጠው ምላሽ ያልተመጣጠነ ነበር። እርግጥ ያ አጋጣሚ ተቃዋሚው ሠላማዊነቱን ያጣበት ነበር። የመንግሥት እርምጃ ግን የቻይናውን (የታይናንሜን ስኩዌር) እርምጃ ያስታውሰናል። ከ20 ዓመታት በፊት አደባባይ ወጥተው አንገባም ያሉትን ሰልፈኞች የቻይና መንግሥት ታንክ ሳይቀር ይዞ አደባባይ በመውጣት ነው ሰልፉን የበተነው። ኢሕአዴግ የደርግን ያክል ቢፈተን ከደርግ አይብስም ወይ? እነዚህን ያወቅናቸውን እና ያላወቅናቸውን የኢሕአዴግ ባሕርያት ማሰላሰል የሠላማዊ ትግሉን መሥመር ለመወጠን ወሳኝ ቁምነገር ነው። እስከአሁን የነበረው ዓይነት ሁሉም በየፊናው ያሰኘውን የሚያደርግበት፣ ያልታሰበበት መፍጨርጨር፣ በአጭር በአጭሩ ከመሰበር በቀር ምንም አልፈየዱም። ብዙ ጊዜ አምባገነኖች የሠላማዊ ትግልን አከርካሪ ለመስበር የሚጠቀሙበት ዘዴ ሠላማዊ ያልሆነ ነገር እንዲሠሩ ማድረግን ነው። ሠላማዊ ትግሉ ሁለቱን እርከኖች (ማንቃት እና ማደራጀት) አልፎ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሲጀምር ሠላማዊነቱ እና ደኅንነቱ እንዴት ይጠበቃል?

ሐዲስ ዓለማየሁ "የልምዣት" ላይ "የጨለማው ንጉሥ" የተባለ በበሻህ ዘለሌ የሚመራ ቡድን ፈጥረዋል። ቡድኑ ሕዝብ የበደሉ ባለሥልጣናትን እየገደለ፣ ለምን እንደተገደሉ የሚገልጽ ማስታወሻ ጽፎባቸው ይሰወራል። ኋላ ግን ቡድኑ ከበሻህ ዘለሌ ቁጥጥር ውጭ ሆነ። የቡድኑ አባላት መነሻቸውን ረስተው ገንዘብ ለመዝረፍ ተሰማሩ። ይህንን ቁንፅል የመጽሐፉን ታሪክ እዚህ መጥቀሴ የግብታዊ ርምጃን የመጨረሻ ውጤት ከዚህ የተሻለ የሚያሳይልኝ ምሳሌ ስለሌለ ነው።

መጀመሪያ የብብቷን...!

በተቃዋሚው ጎራ የተለመደ ድክመት አለ። ተቃዋሚው የቱንም ያክል በትንሽ አቅም ቢንቀሳቀስ፣ የሚጠብቀው ውጤት ብዙ ነው። ይህ የስስት ባሕሪ የያዘውን ጭምር ያሳጣዋል። በምርጫ 97 ተቃዋሚው ከመቼውም የበለጠ (31.6% ያህል) የፓርላማ ወንበር እንዳገኘ ኢሕአዴግ አምኖለታል። ምርጫው ነጻና ፍትሐዊ አልነበረም። ሆኖም ተቃዋሚው ‹ኢሕአዴግ ምርጫውን ቢያጭበረብርስ በማለት አማራጭ ውጥን (Plan B) ያላዘጋጀ በመሆኑ የያዘውን ይዞ ማልቀስ ሲኖርበት የያዘውንም አጥቷል› በማለት አቶ ግርማ ሞገስ ‹ሰላማዊ ትግል 101 ላይ› ይከራከራሉ፦

“በትግሉ ሜዳ መቆየት ያለብህ ያገኘኸውን ድል ሳትነጠቅ ተጨማሪ ድሎችን ማግኘት የሚያስችል ተጨማሪ አቅም እንዳለህ እርግጠኛ ስትሆን ብቻ ነው፡፡” (ገጽ 199)

“…ተቃዋሚው የነበረውን የተሻለ አማራጭ በምርጫ ያገኘውን ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ድል ከነእንክኑ መቀበል ነበር፡፡” (ገጽ 205)

የውሸት ምርጫ አምባገነኖች ዓለምዐቀፍ ድጋፍ ለማግኛ የሚጠቀሙበት ‹ዕውቅና› መግዣ ነው፡፡ የፈለገውን ያክል ተፎካካሪዎቻቸውን ቢደፈጥጡም፣ እነርሱን መጣል የሚችል ሠላማዊ ስትራቴጂ መንደፍ የሚቻለው ግን ምርጫን አስታኮ ነው፡፡ ስለዚህ ተቃዋሚዎች የያዙትን ይዘው፣ በምርጫዎች መሐል ራሳቸውን ወንበር መነቅነቅ በሚያስችላቸው መንገድ ማደራጀት እና ማዘጋጀት አለባቸው - ከነፈተናው፡፡ ፈተናው ሠላማዊ ታጋዮች ወደ ትግል የሚገቡበት እንጂ ከትግል የሚወጡበት ምክንያት መሆን የለበትም፡፡

“ምን ተይዞ ጉዞ?”

ተቃዋሚው ዘንድ በችኮላ የሚወሰኑ ግብታዊ ርምጃዎች ለዘላቂ ክሽፈት መንስኤ እንደሚሆኑ ተመልከተናል፡፡ የተደራጀ እና የነቃ ማኅበረሰብ በሌለበት ሠላማዊ ሰልፍ መጥራት - አንድም በሚገኘው ሰው ማነስ (ትግሉ የሕዳጣን እየመሰለ)፣ አንድም ለአገዛዙ ምት እየተመቸ ከሚጠራው የሚያባርረው ሰው እንዲበዛ ያደርጋል፡፡ (ከምርጫ 97 ወዲህ እንኳ አንድም ሰው ያልወጣባቸው ሁለት የአብዮት ጥሪዎች ተደርገዋል፡፡) በሌላ በኩል የተለያዩ አድማዎችን ለመጥራት ብዙ ነገሮችን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ በ1960ዎቹ የኢትዮጵያ አብዮት ባለታክሲዎች ያደረጉት አድማ ወደር የለውም፡፡ ጆን ያንግ ‘Peasants Revolution in Ethiopia’ ላይ ‹አዲስ አበባ ሽባ ሆና ዋለች› ብለው ጽፈዋል፡፡ በአምስት ሣንቲም የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ አገር ተንቀጠቀጠ፡፡ ይህንን እያስታወሱ የታክሲ ሥራ ማቆም አድማዎች በቅርብ ጊዜያትም ተጠርተዋል፡፡ ችግሩ ግን እነሱን የሚመለከት መነሻ አልነበረውም፡፡ እንዲያውም በድኅረ ምርጫ 97 የተጠራው በራሳቸው ተነሳሽነት በመሆኑ በከፊል ተሳክቷል፡፡ ግን ያለምንም ትርፍ ከ5 ቀናት በኋላ ወደነበረበት ቀስ በቀስ ተመልሷል፡፡ ለምን?፦

ሾፌሮቹ፣ ባለቤቶቹ፣ ረዳቶቹ ምን ይብሉ? ኤርምያስ ለገሠ (“የመለስ ትሩፋት” ባለው መጽሐፉ ላይ) ‹ሥራው እንዲቀጥል ከመንግሥት ጋር መሞዳሞድ የጀመሩት ሱስ ያናወዛቸው ተራ አስከባሪዎች ናቸው› ይላል፡፡ ዞሮ ዞሮ በመንግሥት ድል አድራጊነት አድማው ከሸፏል፡፡ ጥቁር አሜሪካውያን በሞንትጎምሪ ከተማ (አላባማ) የጥቁሮችን መገለል በመቃወም

በከተማ አውቶቡስ ላለመሳፈር ሲያድሙ፣ ጥቂሮች የሚጓጓዙባቸውን አማራጮች አመቻችተው ነበር፡፡ በአገራችን ሕወሓት/ኢሕአዴግን የኢኮኖሚ ትብብር ለመንፈግ ሲባል ‹ከነእከሌ አትግዙ› የሚሉ የአድማ ምክሮች ብዙ ጊዜ ተደምጠዋል፡፡ ግን አልተሳኩም፤ ምክንያቱም ሽማቹ ሌላ አማራጭ የለውም፡፡ አድማዎች የሚጠሩ ከሆነ፣ ጉዳታቸው (ተፅዕኖ ፈጣሪነታቸው) አድማ መቺው ላይ ሳይሆን አምባገነኑ አካል ላይ መሆኑን (ወይም መሆን የሚችልበት መንገድ) ማረጋገጥ የመጀመሪያው ሥራ ነው፡፡

መውጪያ

'ከታሪክ የምንማረው ከታሪክ እንደማንማር ነው' የሚለው አባባል የመጣው ለሰዎች የሚቀለው የሚያውቁትን መደጋገም ስለሆነና ያንኑ ስለሚያደርጉ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው፡፡ እንኳን በተቀናቃኝ ኃይሎች መካከል፣ ልጅ ከአባቱ ሥልጣን የሚወስደው በጦርነት ወይም በኃይል ነው፡፡ ('ታላቁ ንጉሥ ቀዳማዊ እያሱ' በ17ኛው ክ/ዘመን መስክ ጉብኝት ደርሶ ሲመለስ ጎንደር በብዙ መልኩ ተቃውሳ ጠበቀችው፡፡ በዚያ ላይ የሚወዳት እቁባቱ ሞታለች፡፡ ተስፋ በመቁረጥ ንጉሡ ጣና ደሴት ካሉ ገዳሞች ገብቶ መነነ፡፡ ልጁ ተክለሃይማኖት አጋጣሚውን ተጠቅሞ ንግሥናውን አወጀ፡፡ ሆኖም ግን አባቴ ተመልሶ ንግሥናዬን ይቀማኛል በሚል ስጋት እዚያው ጣና ደሴት ላይ አስገድሎታል፡፡)

ይህ የታሪክ ዥረት ፈሶ፣ ፈሶ እኛ ጋር ደርሷል፡፡ የእኛ ትውልድም፣ እንደቀድሞው ሁሉ በትረ-ሥልጣኑን በኃይል ከጨበጠው ኃይል ጋር ተፋጧል፡፡ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ "ዴሞክራሲ ማለት ሕዝቦች ከጦር ሠራዊት (የበላይነት) ነጻ ሲወጡ ማለት ነው" ይላል፤ እንደ ኮስታሪካ የጦር ሠራዊታችንን በትነን (እስካሁን 68 ዓመት ሞልቷቸዋል) በሠላም መኖር ባይሆንልን እንኳን ጦር ሠራዊቱን፣ ፖሊስ እና የደኅንነት አካሉን የማንፈራ እና የማናፍርበት እንዲሆን ብዙ መታገል አለብን፡፡ በመታደል የሚገኝ የለምና፡፡ ጥያቄው ‹ከትግል ሒደቱ "ጨዋ" ወይስ "ባለጌ" ይወጣን ይሆን?› የሚለው ነው፡፡

የተለመደውን የጦርነት ታሪክ እናስቀጥላለን ወይስ አዲስ ታሪክ ለመሥራት ተዘጋጅተናል?

በላ-ተኛ-አንቺን

፩
አንጎሌ አቅም አጥቶ፥ በሆዴ ሲረ:ታ፣
እንዲህ ይመስለኛል፥ የተራብኩኝ'ለታ፣
⇩
መጋቢ ሁሉ እናት፥ እንጀራም ስጦታ፣
ገበታ ዓለሜ፥ የመኖሬ አለኝታ።

፪
ከፍትፍቱ ፊቱ፥ ብለው ሲተርቱ፣
ሆዳቸው ሞልቶ ነው፥ በልተው በያይነቱ፤
እያልኩ አስባለሁ፥
ሆድና ሕሊና ሁለት መዳኒቱ፣
የመሆኑ ምሥጢር፥ ሲገለጽ እውነቱ፣
ርሀቤ ታግሶ፥ ጣም ሲያጣ ወጡ፣
እንዲህ ያስብለኛል…
…'እኒህ መጋቢዎች፥ ዛሬስ ዓይን አወጡ፣
ይገዛኝ መስሏቸው፥ የእህል መጣፈጡ፣
ግልምጫ ጨልፈው፥ ሲደልሉኝ መጡ።'

፫
እንዲ:ም ይመስለኛል ⇩
ምግቡ እኔና አንቺ፥ እኛው ራሳችን፣
ገበታው ሜዳችን፥ ለመነ:ኻሪያችን፣
ጠላታችን ደግሞ፥ የወል ባላንጣችን፣
ባልወለደ አንጀቱ፥ በልቶ አዳሪያችን፣
እየበላን ሳለ፥
አበላሁ እያለ - አታላይ ጌታችን፣
የእንጀራ አባታችን።

(ሚያዝያ 11፣ 2009)

Are Revolutions Meant to be Betrayed?

(Friday, January 31, 2014)

Revolutions are usually portrayed as the most heroic acts that can be done by a generation. Some say that they are simply shortcuts for evolution which bring immediate changes by shaking the status quo that, otherwise, might take long to; others say they are only good in clearing the way for real changes. Only a few say revolutions are means in which you throw away the evils you know to put in the evils you don't know.

During revolutions, things happen so fast that one can't actually have control nor even clear understanding of what is going on. Post revolutionary eras are mostly unpredictable. Pre-revolution is the best course of any revolutionary progress; it engages wide range of popular participation and is determined to a goal of laying tyranny down. That's not the same for post revolution era.

Revolutionaries don't usually talk to each other what kind of change they've to bring. Even if they do, they care less for the differences existed between them. They just work together to topple whom they call an obstacle for their esteemed change.

This working together towards different goal brings a problem when they succeed. It's true that predators agree until they will have to split their prey. After a revolution, come other successive revolutions. This is either because each revolutionary wants to take the key position to bring about their change or because the thrown ones want to come back in different colors.

Revolutions are participatory. Like the man behind the Jan 25/2011 Egypt revolution, Wael Ghonim, said it, they help in realizing “the power of the people is greater than the people in power". However, no one can surely tell not only whether the revolutionary people owns the fruit of the revolution or not; but also whether the change is for good or not. Now - 3 years after the revolution, in Egypt, Wael Ghonim's name is labeled as “foreign agent" and he is living in Dubai. If he goes back to Egypt, he will join his friends in jail. Friends of Mubarek are now back in power.

In Ethiopia's 1974 revolution, most of the youth who risen up to throw the feudal monarchy were killed. The feudal system was broken for good (one goal achieved) but the revolutionaries were considered the enemies of the revolution

for the years after. The people who toppled a monarchy were silenced by a militia rule.

In Kenya, too, not a few citizens believe the Mau Mau uprising was betrayed by Jomo Kenyatta who was "not actually a freedom fighter but an ordinary man who accidentally joined the fighters in prison". Now, 50 years after Kenya earned its independence, political power and the economy is dominated by two giants (Kenyatta and Odinga) who accumulated all snatching from their people. This eventually created a huge gap of social equity. In fact, the fight has got Kenya independence but Kenyans are two: the rich and the poor. The former indirectly ruling the latter. I don't think Mau Mau fought for that.

On the other hand, many a social scientists argue that it is hardly possible to measure the effect of a revolution within a short period unless for centuries. This argument, however, doesn't answer how revolutions effect change that gradual evolutions can't in this long period of time. Revolutions are meant to answer popular questions shortly.

In Ethiopian contemporary politics, the deliberately weakened oppositions are not less dictators than EPRDF wherever and whenever they can. I always bother about the destiny of Ethiopia thinking 'what if the people who are giving up with the authoritarian behavior of the regime revolt?

Is it worth the risk to revolt against EPRDF? Is there any other way to bring plurality of administration toppling this one-party rule?

ባለህበት እርገጥ

ወደፊት፣... ወደኋላ፣
ወደኋላ፣... ወደኋላ፣
ሆኗል የኛ መላ፤
መራመድ ወደፊት፥ ያለፈውን ትቶ፣
እልፍ እንደሚያ'ሳፍስ፥ የሚያሳየን ጠፍቶ፣
ሐውልት እንደሆነች፥ እንደዛች የሎጥ ሚስት፣
ከፊታችን ይልቅ፥ ለኋላው ስንሰስት፣
ቀደም፣ ቀደም ያሉት ነገሩ ገብቷቸው፣
እኛን ሐውልቶቹን፥ አልፈው በርምጃቸው፣
የፊቱን አረሱት፥ ሞላ ጎተራቸው።

እኛ እንርገጥ ብቻ፥...
መርገጥ፣ መርገጥ፣ መርገጥ፣
ያንኛውን መርገጥ፣ ይሄኛውን መርገጥ፣
ያለፈውን መርገጥ፣ ባለንበት መርገጥ፣
ድሮስ ለሐውልት ሕዝብ፥ ባቋም ለዋለለ፣
ከመርገጥ በስተቀር፣ እርምጃ የታለ?
መርገጥ ነው የተማርን፥ ከአባቶቻችን፣
መ'ረገጥ ነው የተማርን፥ ከእናቶቻችን፣
እኛም ካልተራገጥን (ወይም ካልተረገጠን)፥
ይጠፋል ባሕላችን፣
ባለህበት እርገጥ።

(ግንቦት 12፣ 2008)

Confession of the Ex-Revo

(መስከረም 2007፤ ከቂሊንጦ ወኅኒ ቤት)

ርዕሱን አላስታውሰውም'ንጂ እ.ኤ.አ በ2011 Arab Uprising በመባል የሚታወሰውን አብዮት ተከትሎ፣ ኢትዮጵያውያን ፌስቡከኞችም (በተለይ ዲያስፖራ የሚገኙ) ግንቦት 20 ላይ (ልክ በኢሕአዴግ የ20ኛ አገዛዝ ዕድሜ) "Anger day" በሚል በፌስቡክ አብዮት መጥራታቸውን ተቃውሜ አንዲት ጽሑፍ ጽፌ ነበር። በዓመቱ ደግሞ "አብዮት ወረት ነው" በሚል ርዕስ በፌስቡክ አብዮት ለማስነሳት ፍላጎት ያላቸው በርካቶች እንዳሉ ገልጬ ነገር ግን ይጎድላቸዋል የሚባሉትን ነገሮች ዘርዝሬ ጽፌ ነበር። በነዚህ ሁለት ጽሑፎች ላይ-ላዩን አብዮትን የተቃወምኩ ቢመስልም እውነታው ግን ጽሑፎቹ በተጻፉበት ወቅት ሕዝቡም፣ ተቃዋሚ ልኂቃኑም፣ ሁኔታዎቹም ለአብዮት ዝግጁ አይደሉም የሚል ዝንባሌ ማሳየቱ ነበር።

ከሌላ ዓመት በኋላደግሞ "ስለለውጥ" በሚል ርዕስ ተከታታይ ጽሑፎችን በዞን ፱ ላይ በግል ተነሳሽነት ማስፈር ጀምሬ ነበር። ጽሑፉን የጀመርኩት "ኢሕአዴግ ሥልጣኑን በምርጫ ይለቃል?" በሚል ጥያቄ ነበር። "አይለቅም" የምልባቸውን ምክንያቶች ካስቀመጥኩ በኋላ የለውጥ አማራጭ የምላቸውን (አብዮት፣ ሠላማዊ አለመታዘዝ /civil disobedience/ የመሳሰሉትን) በየዘርፉ እየቀነጫጨብኩ ለማሳየት ነበር ዓላማዬ - ከዚያም "የለውጥ ፍርሐት"፣ "የሥርዓት ለውጥ እና ሃይማኖት"፣ "የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮት እና የማኅበራት ሚና" የሚሉ ርዕሶችን በማንሳት በሐሳቦቹ ላይ በሐቀኝነት ለመከራከር ጥረት አድርጌያለሁ (ከዚህ በላይ አልገፋሁበትም እንጂ)። በበኩሌ ስለአብዮት በደንብ ያነበብኩትም፣ ያሰብኩትም፣ የጻፍኩትም፣ የተረዳሁትም ያኔ ነበር። ያኔ በአብዮት ላይ የነበረኝ እምነት ተሸርሽሮ ግማሽ ደርሶ ነበር። ተንጠፍጥፎ ያለቀው ግን አሁንም በዓመቱ (በ2006 አጋማሽ) ነው። እንባቢ ከአብዮት አድናቂነት ወደ ዝግመተ ለውጥ አራማጅነት (በ "ያ ትውልድ" ሰዎች አጠራር ከRevo ወደ Sabo) የተሸጋገርኩበትን የሐሳብ ዳገት (ከፈለጋችሁ ቁልቁለት በሉት) ይረዳ ዘንድ በመጠኑ ዘርዘር አድርጌ ማስረዳት አለብኝ። (ታዲያ የአብዮት አድናቆቱም ቢሆን ከወረቀት እንዳላለፈ ልብ በሉልኝ)።

እነዚያን ተከታታይ ጽሑፎች በጻፍኩበት ሰሞን ‹አብዮት "እቆጣጠረዋለሁ" ብለው ያሰቡትን ነገር ግን ድንገት ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን የሚችል እሳትን መለኮስ› እንደሆነ እያሰብኩ ባለሁበት ሰሞን ግብጻውያን ሙርሲን ለመጣል ያምጹ ጀመር፡፡ የግብጹ ድጋሚ አመጽ (አብዮት) በጣም የተዘበራረቀ ስሜት ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ሙርሲ እኔ በግሌ ከማምንባቸውና ቋሚም ከሆኑ የዲሞክራሲ መርሖች እያፈነገጠ ነበር፡፡ ስለዚህ የግብጾች ማበይ ምክንያታዊ ነው ብዬ አምኛለሁ፤ እንዲያውም ሕዝብ አንዴ ‹ከነቃ አይሆንም ዕቃ› ብዬ ነበር፡፡ የግብጽ ሕዝብ የሚፈልገውን ዓይነት ስርዓት እስከሚያገኝ እያበየ ይቀጥላል የሚል ግምት ነበረኝ - ልክ እንደ ፈረንሳዮቹ ተከታታይ አብዮቶች፡፡ ነገር ግን የግብጽ ሕዝብ እያበየ ቢቀጥልም እንኳን የፈለገውን ላያገኝ እንደሚችል የተረዳሁት ወታደራዊ ክንፉ ቀስ በቀስ አገሪቱን በአብዮቱ ተከልሎ ሲጠቀልላት ስመለከት ነበር ፡፡ ከአገራችን የደርግ አመጣጥ አልለይ ብሎኝ ‹አብዮቶች ሁሉ አንድ ናቸው እንዴ?› እስከሚያስብል ድረስ ተመሳስሎብኝም ነበር፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ሚዲያ እና ፕሬሶች በአንዳች ተዋስኦ ይናጡ ጀመር፡፡ ተዋስኦው የተጀመረው የጃዋር መሐመድን ‹ኦሮሞ ቅድሚያ› (Oromo First) የአልጄዚራ ምላሹን ተከትሎ ነበር፡፡ ብዙዎች ይሄን ወቅት የሚያስታውሱት እንደአላስፈላጊ የንትርክ ወቅት ቢሆንም፣ በበኩሌ ብዙዎች ቆም ብለው አቋማቸውን እና የአቋማቸውን መሠረት እንዲፈትሹ፣ በታሪካዊ እና ፖለቲካዊ ኩነቶች ላይ ንባባቸውን እንዲቀጥሉ ያስታወሰ መልካም አጋጣሚ ነው ባይ ነኝ፡፡ ይህ አጋጣሚ በሥመ ተቃዋሚ (dissent) የአንድ ኢሕአዴግን ከሥልጣን መውረድ ብቻ እንደ ለውጥ ግብ አድርገን በጋራ ስንንቀሳቀስ የነበርን ተቃዋሚ ግለሰቦች እና ቡድኖች እርስ በርስ ያሉትን ልዩነቶች እና ልዩነቶቻችንን የምናቻችልባቸውን መንገዶች እንድናስተውል መንገድ ፈጥሯል፡፡ ብዙዎቻችን የማንፈልገውን እንጂ የምንፈልገው ምን እንደሆነ በቅጡ እንደማናውቅ፣ ትግላችን ከመርሕ ይልቅ በእልሕ እንደሚመራ ያጋለጠ፣ ራሳችንን እንድንገመግም ያስገደደ አጋጣሚ ነበር፡፡

ከዚህ ድንጋጤ ውስጥ ነው ‹አምባገነን መሪዎቻችን ከሕዝብ ጉያ የወጡ› የአስተሳሰብ ችግር የወለዳቸው የመሆናቸው ሐቅ ዘልቆ የገባኝ (ወይም genuinely comprehend ማድረግ የተቻለኝ) ስለዚህ አብዮት ሲፀነስ ዓላማው ባልተለወጠ ሕዝብ ላይ የተለወጠ መሪ ማስቀመጥ ቢሆንም

ሲወለድ ግን አንድም ያልተለወጠ ሕዝብ የተለወጠ መሪ መውለድ ስለማይችል፣ አንድም ደግሞ የተለወጠ መሪ እና ያልተለወጠ ሕዝብ መዋሐድ ስለማይችሉ፣ አብዮቱ (ዓላማው) ይጨናገፋል።

በዚሁ ጊዜ ነበር የቅርብ ጊዜ ምሳሌያችንን የአረብ አብዮትን መልሼ በወፍ በረር ለመገምገም የተገደድኩት። ቱኒዚያ፣ ግብጽ፣ ሊቢያ፣ ሶሪያ… ከተሳካው የከሸፈው፣ ከለማው የወደመው ይበዛል። የአምባገነን መገርሰስ ብቻውን ለውጥ አያመጣም፤ ከነዚህኞቹ ለውጦች ይልቅ የእኛው ፊውዳሊዝምን ገርስሶ - ወታደራዊ አምባገነንነትን ያመጣው አብዮት የተሻለ ኪሳራ ነበረው ማለት ይቻላል። (እዚህጋ በኢሕአፓ፣ መኢሶን እና ሌሎችም የደርግ ፓርቲዎች መካከል የተደረገው የድኀረ አብዮት የሥልጣን ሽኩቻ ሳቢያ የጠፋውን ሕይወት ሳንቆጥር መሆኑ ነው።) ከትንሽ ጊዜ በኋላ ደግሞ በብርቱካናማ አብዮቷ የምትደነቀው ዩክሬን አበየች። (“የተውኩትን ነገር ተነግሬ፣ ተመክሬ ባገር - ምን ጎትቶ አመጣብኝ፣ የአብዮትን ነገር? Another revolution?” ብዬ ትዊት አድርጌም ነበር) አብዮቷ ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ የአካሏ ክፋይ የሆነችው ክሬሚያን በማሳጣት ይጀምራል። ምዕራብ ዩክሬናውያን ሲያብዩ ‹የአገራችን መንግሥት ከምዕብራባውያን ይልቅ ምሥራቃውያን (ራሺያ) አደላ› ብለው ቢሆንም በውጤቱ ግን ጭራሽ ራሺያ ክሬሚያን ጠቅልላ አረፈችው። ልብ በሉ! አብዮቱ ከተነሳበት 360 ዲግሪ ዞሮ ተጠናቀቀ። ለነገሩ አልተጠናቀቀም፤ አሁን ወደ እርስ በእርስ ጦርነት ተሸጋግሯል።

ይኼኔ ነበር በግል ጦማሬ ላይ ጥር 2006 “Are revolutions meant to be betrayed?” ብዬ በመጠየቅ የጻፍኩት። ዜጎች አብዮትን ሲጀምሩት የማይታዩ ችግሮች ሲጨርሱት የሚስተዋለው ‹ሌባ ሲካፈል እንጂ ሲሰርቅ አይጣላም› የሚል ነበር የጽሑፌ አንኳር ሐሳብ። “ሌባ” ያልኳቸው በሕዝባዊ አብዮት ሥም የግል ሕልማቸውን የሚያሳኩ አጀንዳ ያላቸውን ቡድኖች (interest groups) ነው። በኢትዮጵያ ነባራዊ የፖለቲካ እውነታ ደግሞ እነዚህ ዓይነቶቹ interest groups ብዙ ናቸው። ስለዚህ በአብዮት ለውጥ አማጭነት ተስፋ ስቆርጥ የመጀመሪያ ጥያቄዬ “ሳያብዩ ለውጥ ማምጣት ይቻላል?” የሚል ነበር። የመጀመሪያ መልሴ ‹እንግሊዝ› ነበረች። የእንግሊዝ ሕዝብና መንግሥት በሕግ የበላይነት ላይ ለማንም ምሳሌ መሆን የሚችል ነው። የዓለምን ግማሽ በገዙበት ጊዜም አሁንም አብየው አያውቁም -

እንግሊዛውያን። ምክንያቱም ተወያይተው ችግራቸውን መፍታት ይችላሉ። ሕዝብና መንግሥት ሲለወጡ ሁሉም በሠላም ይካሄዳል።

ይህንን የመጨረሻ አቋሜን ያውቅ የነበረ ወዳጄ፣ "እህ አሁንስ?" አለኝ ‹አብዮት ልታስነሳ አሲረሃል› ተብዬ ተጠርጥሬ ከታሰርኩ በኋላ ሊጎበኘኝ መጥቶ። "አየኸው አይደል፣ ያለአብዮት ለውጥ እንደማይመጣ?" የሚገርመው፣ የኔና የጓደኞቼ በሕገ-ወጣዊ ማን አለብኝነት መታሰርና፣ የመንግሥት (ፖሊስ) ተጠያቂነት ማጣት ውስጥም ሕዝባዊ አለመለወጥ ነው የሚታየኝ። መንግሥት አሁንም ቢሆን የሚያስጨንቀው "የውጭ ኃይሎች ጫጫታ" እንጂ የውስጥ ሰዎች ጥያቄ አይደለም። በእኛ ላይ የደረሰው (ሐሳብን በመግለጽ ጦስ መታሰር) በሌሎች ላይ ሲደርስ የነበረ፣ እየደረሰ ያለ፣ ወደፊትም የሚደርስ መሆኑ ቢታወቀውም ሕዝባችን ግን "መብቴን ማስጠበቅ አለብኝ" ከማለት ይልቅ "ዝም ብል ይሻለኛል" (ጎመን በጤና) mode ውስጥ ነው። ሕዝብ ገና አልተለወጠም፤ የለውጥ ጣዕሙም የገባው አይመስልም። ሌሎች ሠላማዊ የትግል አማራጮችም ገና በኢትዮጵያ አልተሞከሩም። ሕዝቡ ጣዕሙን የማያውቀውን ለውጥ ከመስጠት በፊት ደግሞ የለውጡን ጣዕም አውቆ ለውጡን ራሱ ጠይቆ፣ ራሱ እንዲያመጣው ማንቃት ያስፈልጋል። አለበለዚያ እንግሊዛውያኑ እንደሚሉት ‹ጋሪው ከፈረሱ ቀድሞ› አይሆንም! ለወዳጄም ይህንኑ ሐሳቤን ነበር የነገርኩት።

ለነገሩ ይህንን ሁሉ አልኩ እንጂ ክፍሉ ታደሰ በ"ያ ትውልድ" (ቅጽ 1) ላይ ‹ኃይሌፊዳ በ1965 በኢትዮጵያ በ25 ዓመት ጊዜ ውስጥ አብዮት ይነሳል ብዬ አልገምትም ብሎ ነበር› እንዳለው ካልሆንኩ በቀር እኔም በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ አብዮት ይነሳል የሚል ምንም ግምት የለኝም፤ በመጨረሻም በአቤ ቶክቻው ዋዘኛ አባባል "ካጠፋሁ፣ልጥፋ!"

‘ጨለማና ብርሃን፣ መኖርና መሞት፣
ሁሉም ተፈጥሯችን፥ ተከፍሏል በሁለት፣’
የሚል ተራ ግምት፥ ይገፄ የምጽፈው፣
ለአጨራረሴ ቢመቸኝ ብዬ ነው።

በዚህ መንደርደሪያ፣ …
የወደድኩሽ እኔ፥ የጠላሽኝ አንቺ፣
ተፈጥሮ ፍጥረቷ፥ እንዲሟላ እንጂ፣
ክፋትሽ ነው ብዬ፥ በፍፁም አላምንም፣
ተፈጥሮ‘ናት ክፉ፥ ሰው ምንም አያውቅም።

በዚህ ማዳበሪያ፣…
የልቤን ደጃፉን፥ በብርሃን አጥር፣
አድምቄ ስጠራሽ፥ እግርሽ የማይደፍር፣
እርምጃሽ የሚያጥር፣
ቀን ሆኜ ስጠብቅ፥
ልብሽ ከኔ ‘ሚርቅ፣
“ነው” ብዬ አላምንም፥ ስላለብሽ ችግር፣
…ጨለማ ነው‘ሚመች፥ ለሌሊት ወፍ እግር።

በዚህ መደምደሚያ፣…
ልባችን ውስጥ ላለው፥ የመውደድ ዕኩያ፣
ሳይኖረን አይቀርም፥ ሌላ ደሞ መጥያ፣
(እደግመዋለሁ)
አንዷን እንወድ ዘንድ፥ የምናመነጨው፣
ሳይኖረን አይቀርም፥ የጥላቻ ቅመም፣
አብረን የምንረጨው፤
የብርሃን ውበት፥ በጨለማ መኖር ይገለጻልና፣
እኔ መስዋ‘ት ልሁን፤
ያንቺ መውደድ ብርሃን፥ እንዲታይ ለሌላ።

(ግንቦት 10፣ 2008)

የ“ተቃራኒ” ወገን የትግል አጋርነት

(የካቲት 27፣ 2008)

በአፍሪካ አሜሪካውያን የሲቪል መብቶች ትግል ውስጥ እና በደቡብ አፍሪካ ነባር ጥቁሮች ከመጤ አፍሪካነሮች የተነጠቁትን የዕኩል ሰውነት መብት ለማስመለስ ሲታገሉ፣ ጥቂት የማይባሉ ነጮች (ወይም አፍሪካነሮች) የትግላቸው አጋር ሁነውላቸው ነበር። ሌሎች ጥቂቶች በደሎቹን ምክንያታዊና ተገቢ ለማድረግ (to justify) ተከራክረዋል። ብዙኃኑ ግን በገለልተኝነት እና በስጋት ተመልክተውታል። ከጥቁሮቹ ታጋዮች መካከልም ከፊሎቹ ለዕኩል የሰውነት ማዕረግ ታግለዋል። ከፊሎቹ ነጮቹን ለመበቀል ታግለዋል። ዞሮ፣ ዞሮ ግን ሁሉም ነባሩን ትርክት እና ተቀባይነት የነበረውን (mainstream) አስተሳሰብ ማፈራረስ ነበራቸው። በዚህ ግዜ ነጮቹ ቀድሞ የነበራቸውን የተለየ መብት ከጥቁሮች ጋር መጋራታቸው መብታቸውን እንደመነጠቅ ቆጥረውታል። ለምሳሌ ቅድሚያ ይሰጣቸው የነበረውን አገልግሎት ከጥቁሮች ዕኩል እንዳደራረሳቸው እየተሰለፉ እንዲያገኙ መገደዳቸውን እንደመብት ነጠቃ ይቆጥሩታል።

እነዚህ ተግዳሮቶች መገፋፋት ይፈጥሩ ነበር። በዚህ ሳቢያ ከነጮቹም፣ ከጥቁሮቹም ወገን አብረን መኖር አንችልም የሚል ሰውነትን የመጠራጠር ዝንባሌ ታይቷል። በአሜሪካ እነማልኮም ኤክስ ይመሩት የነበሩት እንቅስቃሴ የነጭ የሆነውን ሁሉ መጠየፍን እንደስትራቴጂ የቆጠረ ነው። የነሱ ተቃራኒ ዕኩያ የሚባለው ኬኬኬ የሚባሉት የነጮች ጥቁር ተጠያፊ ቡድን ነው። የማልኮሜክስ ‘ኔሽን ኦቭ ኢስላም’ እና ‘ኩ ክላክስ ክላን’ አንዴ ስምምነት ላይ ደርሰው ነበር። ጥቁሮቹም ነጭ የማያዩበት የጥቁር ዓለም፣ ነጮቹም ጥቁር የማያዩበት የነጭ ዓለም ሊመሠርቱ። አንዱ ሌላኛውን ለማግለል እንደመስማማት።

በቀድሞዋ አሜሪካ ሰሜኖቹ "ነጻ አገሮች" ሲሆኑ ደቡቦቹ "ባሪያ አሳዳሪ" ነበሩ። ሶሻሊስቶቹ በወቅቱ በሰሜን የነበረውን የጭሰኝነት ሁኔታ እያዩ በሰሜን ያለው የጭቁን ሠራተኞች ሁኔታ እና በደቡብ ያለው የባሪያዎች ሁኔታ አንድ ነው እስከማለት የሚደፍሩ ነበሩ - በመደብ ጭቆና ትንተና። ነገር ግን በወቅቱ ከደቡብ ባርነት ኮብልለው ወደሰሜን ጭሰኝነት የሚፈልሱ እልፍ ሰዎች ቢኖሩም፣ ከሰሜን ጭሰኝነት ወደደቡብ ባርነት የኮበለሉ ሰዎች አልነበሩም።

ሌላኛው ፈታኝ ነገር ያንን ጥቁሮችን የሚያንኳስስ ስርዓት የሚደግፉ ጥቁሮች መኖራቸው ለነጭ አስተባባዮች ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ ነበር።

ማልኮም ኤክስ በባርነት የነበሩ ጥቁሮችን በሁለት ይከፍላቸው ነበር። የቤት እና የመስክ ኔግሮዎች (house and field negroes) ብሎ። የቤት ኔግሮዎቹ ጥቁር ቢሆኑም ከጌታው የሚተርፈውን ከስር ከስር የመቋደስ ዕድሉ ነበራቸው (they were privileged)። ተመችቷቸዋል። ስለዚህ፣ አብዛኛውን ፍዳ እንደሚቀምሱት የመስክ ኔግሮዎች ስርዓቱን አይቃወሙትም፣ እንዲያውም በደሉን በሰበብ ያለባብሱለታል።

እንዲህ ዓይነቱ የታሪክ ትርክት መገፋፋት ኋላ ላይ የዕኩል ሰውነት ማዕረግ ለማግኘት ይታገሉ ለነበሩት ለነማርቲን ሉተር ኪንግ ፈታኝ ነበር። በግለታሪኩ ላይ ኪንግ የሲቪል መብቶች ትግሉ አንዱ ፈተና ይህ እንደነበር ገልጿል። *መጨረሻ ላይ ስሌታማ የሆነው ግን፣ የአግላዮቹ ሳይሆን የአካታቾቹ ትግል ነው።* ጥቁሮቹ ዕኩል መብቱን ሲያገኙ ቀድሞ ነጮቹ "ይፈሩት እንደነበረው" ዓይነት ጥፋት አልደረሰም።

በደቡብ አፍሪካ ኤኤንሲ ጥቁሮች ብቻ ሳይሆን ነጮችንም በአባልነት ይቀበል ነበር። የነማርቲን ሉተር ኪንግ እንቅስቃሴም በርካታ ነጭ አጋሮች ነበሩት። ማልኮም ኤክስ ከመገደሉ ጥቂት ቀደም ብሎ ስለሚፀፀተው ነገር ሲናገር አንዲት ታዳጊ ልጅ ጠቅሷል። ከዓመታት በፊት ማልኮም የአግላዩ ትግል ሊቀ ጳጳስ እያ፡ለ አንዲት የ10 ዓመት ሕፃን ልጅ እቅፍ አበባ ይዛ ለጥቁሮች ትግል አጋርነቷን ለማሳየት ስትወጣ 'ሂጅ ከዚህ፤ እኛ ከነጮች ጋር አጋርነት የለንም' ብሎ አባሯት ነበር። ኋላ፣ እየበሰለ ሲመጣ ተፀፅቷል።

እኛ አገር በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የፆታን ጨምሮ፣ ከፊሉ በመደብ፣ ከፊሉ በማንነት፣ ከፊሉ በመደብ እና በማንነት ምክንያት በሚሉት መሠረት (መሠረቱን ባለሙያዎች በጥናት ሊበይኑልን ሲገባ እኛ ባላዋቂነት ጭቃ እየተለቃለቅንበት እንገኛለን፣ ለማንኛውም) ለዘመናት በገዢዎች እና በተገዢዎች መካከል (ወይም ዘመንና በሕል ባፈረጠማቸው እና ባንኳሰሳቸው የማኅበረሰብ ክፍሎች /ምሳሌ ወንዶች እና ሴቶች/) ለደረሱት በደሎች እና በዘለቄታው ላስከተሉት በማንነት ላይ የተመሠረተ የተጠቃሚነት ጉዳትን ለማስተካከል (undoing sustained system of repression) አንዱ የሌላው አጋር በመሆን አካታች የመብት ትግል በማድረግ ፈንታ አግላይ ትግል እያደረግን ሁሉንም አሸናፊ የሚያደርግ አማራጭ እያለን፣ ሁሉንም ተሸናፊ የሚያደርገውን አማራጭ እየተከተልን እንገኛን።

ብዙ ጊዜ አጋርነትን አለመከተል ጦስ አለው። "ችግር የለም" በሚል በክህደት (denial) የተጀመረው፣ ወደ ፍረጃ ወይም መጥሌ (prejudice) ያድግና ውጤቱ የእርስበርስ እልቂት ይሆናል። ለዕኩል ዕድል እና መብት የሚታገሉት ቡድኖች በአግላይ ትርክት ጠላት የሚል ሥም የሚያወጡለት

ቡድን ስለሚኖረው "ተቃራኒያችን" የሚሉትን ወገን ይገፋሉ። በሌላ በኩል ያንኛው ወገንም አንዳንድ ነባር ጥቅሞቼ ሊሸረሸሩብኝ ነው፣ ከሌሎች የዕኩል ባለመብቶች ጋር ልጋራው ነው በማለት የአፀፋ ግፊት ይገፋሉ።

የአንዱ እምነት ተከታይ ይሄ በደል ነበረብኝ፣ አለብኝ፣ በዘዴ እንዲቀጥል እየተደረገብኝ ነው ሲል፤ አንዱ ብሔርተኛ በማንነቴ ምክንያት እንዲህ ዓይነት በደል ይደርስብኝ ነበር፣ አሁንም አለብኝ፣ በዚህ አካሔድ ወደፊትም በደሉ ይቀጥልብኛል ሲል፤ አንዷ ሴት በመሆኔ ብቻ ወንዶች በቀላሉ የሚያገኙትን መብትና ዕድል ተነፈግኩ ስትል፣ "እኔ አለሁልህ/ሽ" በማለት ሰው ሠራሽ የእምነት እና የማንነት ድንበሮችን መስበር ካልቻልን ለሰውነት ማዕረግ ብቁ ነን ማለት አይቻልም። ተበዳይም በአርቲፊሻል ሰበቦች ላይ ተመሥርቶ 'አንተማ በድለኸኛል፣ ወግድልኝ' ካለ ትግሉ የሚገባውን የሰውነት ማዕረግ ለማግኘት ሳይሆን በተራው የሌሎችን ለመግፈፍ ነው ማለት ነው። ዳር ላይ ቁሞ ችግሩን ለመፍታት የሚፍጨረጨሩትን ፀጉር እየሰነጠቁ በማብጠልጠልም ግድግዳው አይፈርስም። የሚከፋፍለን ግድግዳ ፈርሶ፥ የሚያቀራርበን ድልድይ የሚሠራው እያንዳንዳችን ሌሎች በሚያደርጉት ትግል ውስጥ አጋርነታችንን በተግባር መግለጽ ስንችል ነው።

መጤ ሃይማኖት፣ ከመጤ ሃይማኖት በመምረጥ፣ (ግን በመሠረቱ ለገዢዎቹ ዋናው ሃይማኖቱ ሳይሆን በሥመ ሥዩመ-ፈጣሪነት የገዢነት ዕድል እና ተገዢ የማግኘት ጥረት ነው።) በወንዜ ማንነት ላይ በመመሥረት አገር ሲገዙ የነበሩ ሰዎች በነበሩበት አገር ውስጥ ያንን የሚያስተባብሉ (justify-ers) መኖራቸው አይገርምም። ይልቁን ከዚያ የአስተሳሰብ እስራት ወጥቶ ሰው ሆኖ መገኘት ነው ቁም ነገሩ።

ከገዢዎች እስራት ነጻ ከመውጣት በፊት ከገዛ ኋላ ቀር አስተሳሰባችን ነጻ መውጣት ይኖርብናል። መሬት የረገጠ ለውጥ ሊያመጡ እውነተኛውን ሥራ እየሠሩ ላሉት አጋር መሆን ካቃተን፣ ቢያንስ አደናቃፊ ላለመሆን መጣር ነው።

‘ኑ፦ ድልድይ እንገንባ’

የቻይና ግዙፍ ግንብ፥
የበርሊን ግድግዳ፣
የሐረርም አጥር፥
የባቢሎን ዙርያ፣
ሽቅብና አግድም የተገደገደ፣
ሰውና ሰው መሐል፥
መንገድ እያገደ፣
ላፍታ ሳይገናኝ፥
ስንት ትውልድ ሄደ?
ስንት ዓመት ነጎደ?!

ክፋት ነው ሲሚንቶው፥
ሰው ከሰው ለይቶ፣
ወዳጅና ጠላት፥
የሚል ሥም አውጥቶ፣
ግድግዳ ያቆመ፣
ጥፋት የቀመመ፣
ሰውን ከሰውነት፥
ሊከልል ያለመ።

ኑ፦ ግድግዳ እናፍርስ
የዘመናት እንባ፥
በአብሮነት እናብስ፤
ፍቅር የተራበውን፥
አንጀት እናረስርስ።

ፍርስራሹን ጠርገን፥
ኑ፦ ድልድይ እንገንባ፣
ሰው ከሰውነቱ፥
መልሶ እንዲግባባ፣
ጥሎት ከሄደው ቤት፣
ተሻግሮ እንዲገባ።

(ጥር 22፣ 2008)

ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት እስከ ማበሳጨት

(*ታኅሣሥ* 3፣ 2008)

“ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት ምንድን ነው? ማበሳጨትን ካላካተተ፣ ሕልውና የለውም።።” ~ ሰልማን ሩሽዲ

፩ - ማበሳጨት

> *“በመስከረም ወር 1997፣ ዢላንድስ ፖስተን የተባለ የዴንማርክ ጋዜጣ ነብዩ መሐመድ ላይ የሚሳለቁ ካርቱኖችን ይዞ ወጣ። የዚህ ሕትመት ዜና በመላው ዓለም እንደተሰማ በየቦታው ያሉ ሙስሊሞች ቁጣቸውን በአደባባይ መግለጽ ጀመሩ። የተቃዋሚዎቹ ምክንያቶቻቸው ሁለት ናቸው፤ አንደኛ፣ ነብዩ መሐመድን በምስል መግለጽ በእስልምና ሃይማኖት አይፈቀድም የሚልና፤ ሁለተኛ፣ ካርቱኖቹ በጥቅሉ እስልምናን እና ሙስሊሞችን ከሽብር ጋር አቆራኝተው ይገልጻሉ የሚል ናቸው። ሠላማዊ ሰልፎችና ሕዝባዊ ተቃውሞዎች በጋዜጣው አዘጋጆች እና በዴንማርክ መንግሥት ላይ ተቀሰቀሰ። ከነዚህ ውስጥ አንዳንዶቹ ሕይወት እስከመቅጠፍ የዘለቀ አመጽ የተቀላቀለባቸው የተቃውሞ ሰልፎች ነበሩ። ካርቱኖቹ ግን በመላው ዓለም በሚገኙ በሌሎች ጋዜጦች ላይ ለዢላንድስ ፖስተን ጋዜጠኞች የሞራል አጋርነት ለማሳየት በሚል ሰበብ ድጋሚ ታትመው ይበልጥ ተሰራጩ።”* (Paul Sturges, 2006)

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ። አንድ ወንድ “‹ሴቶችን ማስተማር የአገርን ሀብት ማባከን ነው፤ ስለዚህ ሴቶችን ማስተማር ካለብን የቤት አያያዝ፣ ምግብ ማብሰል እና ልጅ አስተዳደግ እናስተምር እንጂ ሌላ ‹የነጭ ኮሌታ› ሥራ የሚያስይዝ ትምህርት ማስተማር የለብንም› የሚል አስተያየት ሲሰጥ በቴሌቪዥን ተላለፈ። ይህን ተከትሎ የከተማው ሴቶች የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ። ወንድ አሽከርካሪዎች የሚነዷቸውን መኪኖች ሰባበሩ። ወንዶችን እያሳደዱ ደበደቡ።” በዚህ የፈጠራ ታሪክ ውስጥ የአስተያየት ሰጪው ሐሳብ ሴቶቹን አበሳጭቷቸው ይሆናል። ነገር ግን ለአመፁ እነርሱን አነሳስቷቸዋል ብሎ መደምደም ከባድ ይሆናል። አማፂዎቹ ሴቶች ስሜታቸውን መቆጣጠርና ሐሳቡን በሐሳብ መመከት ካልቻሉ ድክመቱ የነርሱ የራሳቸው ይሆናል።

የዴንማርክ ፍርድቤት የፈረደውም፣ እኔ በላይኛው አንቀጽ አመጻኞቹ ሴቶች ላይ የሰጠሁትን ዓይነት ብይን ነው። “እርግጥ ነው ስዕሎቹ የተወሰኑ

ሙስሊሞችን ማበሳጨታቸው አይካድም፤ ነገር ግን የካርቱኖቹ ዓላማ ሙስሊሞችን ማንኳሰስ አልነበረም" ብሏል ፍ/ቤቱ። ሲያብራራውም፣ "ስዕሎቹን አመፅ ወይም ቦንብ የመወርወር ድርጊት በእስልምና ሥም እየተደረገ ነው፤" በሚል መረዳት የካርቱኖቹ ተመልካቾች ድርሻ ነበር ብሏል። የዴንማርክ ፍርድ ቤት ብይን ለካርቱኒስቶቹ ያደላ ቢመስልም ካርቱኒስቶች ራሳቸው ላይ ቅድመ ምርመራ እንዲያደርጉ ክስተቱ አስገድዷቸዋል። ነገር ግን የአንድ ሐሳብ (expression) አንባቢ፣ ተመልካች ወይም አድማጭ የራሱን ስሜት መቆጣጠር ድርሻ የራሱ መሆን ካልቻለ ቢያንስ የሆነ ሰውን የማያበሳጭ ሐሳብ ማፍለቅ በጣም አስቸጋሪ ስለሚሆን፣ ‹በነጻ› ቀርቶ ሐሳብን መግለጽ የሚባለው ጉዳይ ራሱ አይኖርም።

አምና የፈረንሳዩ ‹ሼርሎ ሆብዶ› መጽሔት ባወጣቸው ካርቱኖች ተበሳጭተው ጋዜጠኞችን፣ ካርቱኒስቶችን እና ፖሊሶችን የገደሉ ፅንፈኛ - ሃይማኖተኞች ጉዳይም ሊታይ የሚችለው በዚሁ ዓይን ነው። ፅንፈኞቹ የእነርሱን እሴት ያላከበረ፣ በእነርሱ እሴት መሠረት መቀጣት አለበት የሚል እርምጃ ነው የወሰዱት። ክስተቱ ለሐሳብ ነጻነት አራማጆች መርዶ ነው። አጋጣሚውን ተከትሎ ተቀጣጥሎ የመጣውም ውይይት ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው ሳንሱር እንዲያደርጉ የሚያስፈራራ ነው። ይሁን እንጂ አጋጣሚው የኢትዮጵያውን ጨምሮ ለአምባገነን (authoritarian) መንግሥታት ፕሮፓጋንዳ ምቹ ሁኔታን ፈጥሯል። ሐሳብ እንዴት መገደብ እንዳለበት ክስተቱን አስታክከው ደስኩረዋል። እነዚህ መንግሥታት ሊያስተውሉት ያልፈለጉት ነገር ቢኖር ከዴንማርክ እስከ ፓሪስ የተከሰተው ነገር ጋዜጠኞች ሐሳባቸውን በነጻነት ሲገልጹ የመንግሥት ከለላ እንደሚያስፈልጋቸው እንጂ ሐሳባቸውን በነጻነት ከመግለጽ እንዲቆጠቡ የሚመክራቸው አልነበረም።

ሌሎችን ማበሳጨት የተወሰኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች ላይ ወይም ግለሰቦች ላይ ሲከሰት ከሞላ ጎደል ከላይ ባየነው ሁኔታ ሊያልፍ ይችላል። ችግሩ የተበሳጨው አምባገነን መንግሥት (የመንግሥት ባለሥልጣናት) ሲሆኑ ነው። እነ ኤልያስ ገብሩ (አምሳሉ ገ/ኪዳን ዕንቁ መጽሔት ላይ በሚያዝያ ወር 2006 የጻፈውን ጽሑፍ ተከትሎ ጅማ ዩንቨርስቲ አካባቢ በተነሳው የተቃውሞ ብጥብጥ ሳቢያ) የተከፈተባቸው የአመጽ ማነሳሳት ክስ መታየት የሚኖርበት በዚህ ዓይን ነው። መንግሥት ጸሐፊዎቹንም፣ ለጽሑፉ የጽሑፍ ምላሽ በመስጠት ፈንታ በኃይል የጸሐፊውን ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት የተቃወሙትን፣ ሁለቱንም በክስ በማስተናገድ ጉዳዩን ለመፍታት እየጣረ፣ ጉዳዩ እስካሁን በእንጥልጥል ነው። ተመስገን ደሳለኝ ሦስት ዓመት የተፈረደበት የመንግሥት ባለሥልጣናትን የማያስደስት አልፎም የሚያበሳጭ ጽሑፍ ስለጻፈ ነው። የዚህ ጽሑፍ ጸሐፊ ክሱ ከሽብር ወደ ‹በጽሑፍ አመጽ

ማነሳሳት› የተቀየረው በተመሳሳይ ምክንያት ነው፡፡ ተጠያቂነት የሌለባቸው የመንግሥት ባለሥልጣናት በሐሳብ ሲበሳጩ ውጤቱ የከፋ ይሆናል፡፡

፪ - የጥላቻ ንግግር እና አመጽ ማነሳሳት

በ1987 ሩዋንዳ በዓለማችን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ ሰቅጣጭ የሆነውን ዜና ለዓለም አርድታለች፡፡ በ100 ቀናት ውስጥ 800 ሺሕ ያህል ሰዎች ተጨፍጭፈዋል፡፡ በጭፍጨፋው 70 በመቶ ቱትሲዎች (ወይም 20 በመቶ ሩዋንዳውያን አልቀዋል)፡፡ የጭፍጨፋው መነሾ ላይ የታሪክ ባለሙያዎች ሙሉ ለሙሉ ባይስማሙም በጎሳ ሥም አመጽ እንዲቀጣጠል ያደረገው ግን የሚዲያ የጥላቻ ንግግር እንደሆነ ብዙዎቹ ይስማማሉ፡፡ ከዘር ጭፍጨፋው ዓመት ቀድሞ የተቋቋመው ሬዲዮ-ቴሌቪዥን ሊብሬ ደስ ሚል ኮሊንስ (አር.ቲ.ኤል.ኤም.ሲ) ዋነኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች በዘር ጭፍጨፋው የዚህን ሚዲያ ተቋም ሚና እስከ 10 በመቶ ያደርሱታል፡፡ ሬዲዮው በጣም ተወዳጅ ከመሆኑ የተነሳ ከዜናዎቹ ጋር በአጭር ጊዜ ለመዋሃድ በቅቷል፡፡ ይህ ሬዲዮ ነበር ቱትሲዎችን "በረሮ" ብሎ መጥራት የጀመረው፡፡ "በረሮዎቹን ደግሞ ማስወገድ አስፈላጊ ነበር፡፡" አለበለዚያ ችግር ያስከትላሉ፡፡ ሬዲዮው በተጨማሪም "በረሮ" ብሎ የጠራቸውን ዜጎች ማስወገድ ስለማስፈለጉ ብቻ ሳይሆን እንዴት መወገድ እንዳለባቸው ጭምር ተንትኗል፡፡ የጭፍጨፋው ፈፃሚዎች በአንድ እጃቸው ቆንጨራ፣ በሌላኛው ሬዲዮ ይዘው እንደነበር ሪፖርት ተደርጓል፡፡

በሩዋንዳ ጭፍጨፋ የነበረው ሬዲዮ ብቻ አልነበረም፡፡ ጋዜጣም የበኩሉን ተጫውቷል፡፡ ካንጉራ የተባለ ሳምንታዊ ጋዜጣ ‹የሁቱ ዐሥርቱ ትዕዛዛት› የተሰኘ ተወዳጅ አምድ ነበረው፡፡ ጋዜጣው በይፋ ሁቱዎች ከቱትሲዎች ጋር ምንም ወዳጅነት እንደሌላቸው አውጇል፡፡ ጠላት ናቸው በሚል ሚስቶች በባሎቻቸው፣ ጎረቤት በጎረቤቱ ላይ በዚህ የማንነት ጠላትነት ላይ ተመሥርተው እንዲነሱ አድርጓል፡፡

የሩዋንዳ ሚዲያዎች የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ እና ዘመቻ ውጤቱ እልቂት ሆኗል፡፡ ሚዲያዎቹ ወደዘር ጭፍጨፋ የደረሱት በሦስት ደረጃዎች ነው፤ መንግሥት ሚዲያውን በተሳሳተ መንገድ ተጠቅሞበታል - በጥላቻ ፕሮፓጋንዳ ለዘር ጭፍጨፋ ማዘጋጃ አድርጎታል - አንድ፣ በጭፍጨፋው ወቅት አመፁን አቀጣጥሏል - ሁለት፣ ከዚያም የጥፋቱ መጠን በትክክል ለሕዝብ እንዳይደርስ አድርጓል - ሦስት፡፡

አሁን የሩዋንዳ መንግሥት ያንን መጥፎ ጠባሳ የጣለበትን ታሪክ ለማጥፋት በማሰብ የሁለቱንም ጎሳዎች ማንነት ክዷል፡፡ በሩዋንዳ አንዱ ሌላውን የእከሌ

ጎሳ አባል ነው ብሎ በይፋ መናገር አይፈቀድለትም። ይህንን የዘር ጭፍጨፋን በማፈን ፈንታ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን ያፈነ እርምጃ እንደሆነ አጥኚዎች ይከራከራሉ። (Yakaré-Oulé (Nani) Jansen, 2014) ለሩዋንዳ መንግሥት ግን ጉዳዩ ግራ አጋቢ ነው። ለሩዋንዳ መንግሥት ብቻ ሳይሆን ለብዙዎች ሌሎችን እስከ ማበሳጨት በሚደርሰው ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት፣ በጥላቻ ንግግር እና በአመጽ ቅስቀሳ መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት አስቸጋሪ ፈተና ይሆንባቸዋል።

ኢትዮጵያም ጭምር የፈረመችው የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ዓለምዐቀፍ ቃልኪዳን እንደሚለው “ማንኛውም ዓይነት በብሔር፣ ዘር፣ ወይም ሃይማኖት ላይ የተመሠረተ የማግለል፣ ጠላትነት ወይም አመፅ የሚያነሳሳ መልዕክት በሕግ መከልከል አለበት።” ሆኖም አንድ ንግግር ወይም መልዕክት የጥላቻ ሊባል የሚችለው የትኛው ደረጃ ላይ ሲደርስ እንደሆነ መግባቢያ የለም።

አስቀድመን ባየናቸው ምሳሌዎች የሚዲያ እና አመፅን ግንኙነት ስንመለከት፤ አበሳጭ የተባሉ ይዘቶችን ይዘው የወጡ የሕትመት ውጤቶች፣ አመፅ አልቀሰቀሱም። ይልቁንም የተቃውሞ አመፅ ተቀስቅሶባቸዋል። የሩዋንዳው የዘር ጭፍጨፋ ደግሞ በተቃራኒው አመፅ የተካሔደው በሚዲያዎቹ የጥላቻና ጥፋት ስብከት መሪነት ነው። በነዚህ ሁለት ምሳሌዎች መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ከባድ ላይሆን ይችላል። የአመፅ ቅስቀሳ ከመደረጉ በፊት ለመከላከል ያንን ዓይነት አዝማሚያ ያለውን የሚዲያ ተቋም ቀድሞ መቆጣጠር ግን ከባድ ይሆናል። የማይቻል ግን አይደለም። ይህንን የሚቻል - ከባድ የመንግሥት ሥራ ክፍተት የሚረዱ አምባገነኖች ሚዲያን (ወይም ሐሳብን የመግለጽ ነጻነትን) ለማፈኛ እንደምክንያት ይጠቀሙበታል፣ እየተጠቀሙበትም ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው መንግሥት በብሔር ላይ ያተኮሩ አንዱን የሚያጠለሹ፣ ሌላውን ተበዳይ የሚያደርጉ የቁርሾ ታሪኮችን እንዲያውም በበጎ ሲመለከታቸውና ሲታገሳቸው ይታያል። የገዢው ፓርቲ አመሠራረትም ሆነ አቋቋም የብሔር በዳይ-ተበዳይ ግንኙነትን አጠፋለሁ በሚል ሥም ስለሆነ እነዚህ ዓይነቶቹ ትረካዎች የተስማሙት ይመስላል። ነገር ግን መንግሥት ለእነዚህ አደገኛ አዝማሚያ ላላቸው ሐሳቦች/ጽሑፎች ያለውን ትዕግሥት ቅንጣት ታክል እንኳን ስርዓቱን ለሚተቹት የለውም። ይህም የሚያስገነዝበው መንግሥት ለሐሳብ ነጻነትም፣ ይሁን ሕዝቦች ላይ ለሚደርሰው አመፅ እንደማይጨነቅ፤ ይልቁንም ለሥልጣኑ ብቻ እንደሚሳሳ ነው። ሐሳብን በመግለጽ ነጻነት እና አመጽ በመቀስቀስ መካከል ያለው ልዩነት ጠርቶ በሕግና መመሪያ እንዲደነገግ የማይፈልገውም ለዚያው ነው።

“ማንም ከብስጭት የመጠበቅ መብት የለውም። ይህ መብት እስከዛሬ ባነበብኳቸው ድንጋጌዎች ሁሉ ላይ የለም። ከተበሳጫችሁ፣ የራሳችሁ ችግር ነው፤ እንደእውነቱ ብዙ ነገሮች ብዙ ሰዎችን ያበሳጫቸዋል።” ~ አሕመድ ሰልማን ሩሽዲ!

\- - -

ለገጣሚዬ

ግጥም እወዳለሁ፥ ብለሽ ታወሪያለሽ፣
በጅምር የቆመ፥ ግጥም እዚ እያየሽ።

ቤት አይመታም፥ ብሎ ሰው ከሚስቅብኝ፣
ዘርፈሽ ውሰጂና፥ እዛ ውስጥ ደብቂኝ፣
ቢነቁብሽ’ንኳ፥ ቅኔ ነው በያቸው፣
ቅኔ ለዘረፈ ምሕረት አላቸው።

(መስከረም 22፣ 2006)

(ይገሉናል ገና)

እንደኗሪ ቆጥረው፥ ከቋሚ ደምረው፣
እኛ የናቅነውን፥ ሰውነት አክብረው፣
መቃብር ቆፍረው፥ ቀለሀ ገብረው፣
ሁሉም ይገሉናል፡፡
አይሲስም ገሎናል፣
መንግሥትም ገሎናል፣
ታጣቂም ገሎናል፡፡
ሞትን በያይነቱ፥ ገዳይ እየቀየርን፣
ደጋግመን ሞተናል፤…
"ታዲያስ" ስንባል ግን፣
ሞትን በጀርባ አዝለን፥
"አለን" እንላለን፤
ኗሪዎች ነን ብለን፡፡
ህም…
አሟሟታችንን፣
ገዳዮቻችንን፣
ባለማወቃችን!
ይኸው እስከዛሬ፥
"አለች" ትንፋሻችን፣
እኛ ግን ሞተናል፤
ለሐውልት ማዕረግ፥ የበቃን እንደሆን፣
ማስታወሻ 'ሚሆን ቁጥር ይቀረናል፣
ነገር ግን ሞተናል፡፡
ገና ይገሉናል፥ እንሞታለን ገና፣
ግዳይ ለመሰዋት፥ ገዳይ ለጅገና፣
የማያበቃ ሞት፥ እንሞታለን ገና፤
ይሄው ነው ልካችን፣
ወራዳ ኑሯችን፣
ወራዳ ሞታችን፣
ይሄው ነው ልካችን፡፡
እንዲያውም፣
ከኑሯችን ይልቅ፥ ድንቅ ነው ሞታችን፡፡
ይግደሉን ደጋግመው፥ ሞት ነው የሚያምርብን፣
አቁመው በሕይወት፥ ከሚቀልዱብን፡፡
(ሚያዝያ 9፣ 2008)

፫ - አባታዊው ስርዓት እና ሴታዊነት

የፌሚኒዝም ሀሁ...

(መጋቢት 1፣ 2009)

ፌሚኒዝምን በተመለከተ ሊያወዛግቡ የማይገባቸው ጥያቄዎች ሲያወዛግቡ እመለከታለሁ። ጥያቄዎቹን የማያነሷቸው ገና ውይይቱ ውስጥ ብዙም ያልቆዩ ሰዎች ናቸው እንዳልል አምናና ካቻምናም ይህንኑ ሲከራከሩ የነበሩ ሰዎች አሉ። አንዳንዶቹ በንባብ የበሰሉ ይመስላሉ፤ መጽሐፍ አሳትመው ፌሚኒዝምን ሊታገሉ የሞከሩም አልጠፉም። ስለዚህ እስኪ ምናልባት ‹በፌሚኒዝም ሀሁ› አልተግባባን እንደሆን በማለት ይህንን ጻፍኩ፣

ፌሚኒዝም ምንድን ነው?

ፌሚኒዝም "ሴቶች ከወንዶች ዕኩል መብት እና ዕኩል ዕድል እንዲያገኙ የሚጥር ንቅናቄ" ነው። ፌሚኒስት ማለትም (ሴትም ትሁን ወንድ) የዓለማችን ስርዓተ ማኅበር አባታዊ (patriarchal ወይም ለወንዶች የሚያደላ ወይም የወንዶች የበላይነት ያለበት) መሆኑን በማመን፣ እንዲለወጥ በየዘርፉ ወይም በአኗኗር የተደራጀ ወይም ያልተደራጀ ጥረት የሚያደርጉ ሰዎች ናቸው።

ፌሚኒዝም ብዙዎች እንደሚፈሩት አባታዊውን ስርዓት አፍርሶ በሴት የበላይነት የሚተካ ንቅናቄ አይደለም። እርግጥ ስር የሰደደው አባታዊው ስርዓተ ማኅበር በሴቶች የበላይነት ልተካህ ቢሉት እንኳን በቀላሉ እና በቅርብ ጊዜ የሚተካ አይደለም። በሌላ በኩል ፌሚኒዝም ሴቶችን ወንድ የማድረግ ንቅናቄም አይደለም። ዕኩልነት ሲባል - የመብት፣ የትምህርት እና የሥራ - እንጂ የቁመት፣ የጡንቻ እና የመሳሰሉት አይደለም። ፌሚኒዝም ሴቶች በራሳቸው እና በዓለማቸው ዕጣ ፈንታ ላይ መወሰን የሚስችላቸውን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ዕድል ሁሉ ከወንዶች ጋር እንዲጋሩ ለማስቻል የሚደረግ ጥረት ነው። እርግጥ ነው ሴቶች ዕኩል መብት እና ዕኩል ዕድል ማግኘታቸው መብቱን እና ዕድሉን የተቀማ/የተካፈሉት የሚመስለው ወንድ መኖሩ የሚገመት ነው። ትግሉ ብዙ ተጉዟል። ሕጋዊ ጥያቄዎች በብዛት መልስ እያገኙ ነው፤ ማኅበራዊው ግን

ገና ብዙ ግዜ ይወስዳል፡፡ ስርዓተ ማኅበሩ እንዳለ የሚመቻቸውን ሳያንገራግጭ የሚመጣ ለውጥም አይሆንም፡፡

ከዚህ ውጪ (ለምሳሌ ብዙ ባያስጋም የአባታዊውን ስርዓት በሴቶች የበላይነት ለመተካት) የሚደረግ ንቅናቄ ከገጠማችሁ ፌሚኒዝም አይደለም፡፡ አነቃናቂዎቹም ፌሚኒስቶች አይደሉም፡፡ በዚህ መፍታት ይቻላል፡፡

ፌሚኒዝም ዘር አለው?

"ፌሚኒዝም አፍሪካዊ እሳቤ አይደለም፤ ምዕራባዊያን የጫኑብን አስተሳሰብ ነው" የሚሉ አስተያየቶች ደጋግመው ይደመጣሉ፡፡ ‹የአፍሪካ፣ የአሜሪካ የሚባል ሥልጣኔ ወይም እሳቤ የለም፤ የሰው ልጅ እንጂ ወይም ሥልጣኔው የተከሰተበት ወይም ያደገበት ቦታ እንጂ› ብሎ ለሚያምን የኔ ብጤ አስተያየቱ በጣም የሚያናድድ ነው፡፡ ትልልቅ አገራዊ እሴቶቻችን ብለን የምንላቸው፣ ለምሳሌ ሃይማኖቶቻችን ሳይቀር (ክርስትና እና እስልምና ከመካከለኛው ምሥራቅ መጤ ናቸው) ከውጪ ተቀብለን እንደራሳችን፣ ከከባቢያዊ ሁነታችን ጋር አስማምተን እንዳልኖርን፣ አባታዊ ስርዓተ ማኅበር (patriarchy) ለማፍረስ ከምዕራባውያኑ ጋር በአንድ ሥም፣ አንድ ንቅናቄ ማድረግ መጤ እሳቤ እንደማስተናገድ ሊቆጠር አይገባውም፡፡ ሴቶቹም የኛው፣ ጭቆናውም የኛው ነው፡፡ የዚህ አቤቱታ አቅራቢዎች፣ ከፌሚኒዝም የተሻለ የመፍትሔ ሐሳብ ካለ ቢጠቁሙ፣ ፌሚኒዝምን በደረቁ ከሚተቹ የተሻለ ይረቱ ነበር፡፡ ፀባቸው ከሥሙ ከሆነ በአማርኛ - ሴታዊነት - በሚል ለመተርጎም ተሞክሯል፡፡

አንዳንዶች፣ ‹የሴት ልጅ ጭቆና ከአፍሪካ ይልቅ ምዕራባውያን ጋር የከፋ እንደሆነ፣ እዚያ ሴት ልጅ እንደሸቀጥ እንደምትታይ እየተከራከሩ፤ የኛውን በፈቃደኝነት ላይ እና ለተፈጥሮ ተስማሚ በሆነ መልኩ የተዘረጋ ስርዓተ ፆታ እንጂ ፆታዊ መድሎ አይደለም፡፡ የምዕራቡን መፍትሔ ስናመጣ ይህንን እሴት እናፈርሰዋለን› የሚል ስጋት አላቸው፡፡ ስጋቱ ራሱ የተሳሳተ ስጋት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ ችግሩ እኛ ጋር ብቻ ሳይሆን ምዕራባውያን ጋር መኖሩም ነው የጋራ መፍትሔ እንድንቀርፅ የሚያስገድደን፡፡ ሌላው ጉዳይ የምናሽሞነሙነው የእኛ የስርዓተ ፆታ ምድድቦሽ ራሱ ትግል የሚያስፈልገው ሌላ ዓይነት የጭቆና አካል እንጂ ለምዕራባውያኑ ሴትን እንደሸቀጥ የሚመለከት ስርዓት የመፍትሔ ትይዩ አማራጭ አይደለም፡፡

‹ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከቀሪው ዓለም የተለየ ነው፤ ልዕለ ኃያሏ አሜሪካ ለሴቶች የመምረጥ መብት ሳትሰጥ የኛ ሴቶች መንበረ ንግሥናውን ያሾሩት ነበር› የሚል መከራከሪያ አለን፡፡ እውነትም እንደሚመስለን የሴቶች

መብትን አስቀድመን ማክበር ጀምረን ከሆነ መንገዱ ቀላል ነው ማለት ነው፡፡ እርግጥ ነው፣ ቢቢሲ ሴት ዜና አንባቢ ከመቅጠሩ በፊት፣ የኢትዮጵያ ሬድዮ ሴት አንባቢ ነበረው፡፡ የኢትዮጵያ ፓርላማ ሲመሠረት ብዙ ሴቶችን ባያገኝም፣ ሴት አባላት እንዳይኖሩት ግን በመከልከል አልጀመረም፡፡ የንግሥተ ሳባ ተረትም ኢትዮጵያውያን ሴትን ቁንጮ የማድረግ ፍርሐት እንዳይኖርባቸው ያደረገ ይመስለኛል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክብረ ነገሥት ከንግሥተ ሳባ በኋላ ሴት ንግሥተ ነገሥት እንዳትሆን ያግዳል፡፡ (?) እነእቴጌ ጣይቱ ቤተ መንግሥቱን የመሩት በንጉሠ ነገሥቱ በኩል ባላቸው ተደማጭነት እንጂ በቀጥታ አይደለም፡፡ ንግሥተ ነገሥት ዘውዲቱ ሲሾሙ፣ ሥራው ግን ይሠራ የነበረው በአልጋ ወራሻቸው ተፈሪ መኮንን ነበር፡፡ መንበሩ የተሰጣቸው የዳግማዊ ዐፄ ምኒልክን ተቀባይነት ለማግኘት ሲባል ነው፡፡ በሌሎች ትውፊታዊ ስርዓቶችም ቢሆን ሴቶች የተገለሉ ናቸው፡፡ በገዳ ስርዓት ለምሳሌ ሴቶች የሉበትም፡፡ ይልቁንም ወንዶች በአስተዳደሩ ሲተጉ፣ ሴቶቹ ተፈጥሮን (በአቴቴ) እንዲለማመኑ ነው የተተዉት፡፡ አሁን በ"ዘመናዊቷ" ኢትዮጵያ ደግሞ ችግሩ የተባባሰ ነው፡፡ የሴት መብት ማክበር ላይ ቀድመናቸዋል የምንላቸው አገሮች የትናየት ጥለውን ሲሔዱ እኛ ለምኒስትርነት እና ለአንዳንድ የመንግሥት ኃላፊነት የምንሾማቸውን ሴቶች ማብቃት እንኳን አቅቶናል፡፡

(አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ የፆታ መድልዖ የለም ብሎ የሚያምን ሰው ካለ የእሸቱ ድባቡን ‹ተባእታይ አገዛዝ በኢትዮጵያ› የሚል እና ፆታዊ መድልዖው ምን ያህል ማኅበረሰቡ ውስጥ ሥር የሰደደ እንደሆነ የሚያሳይ፣ ጥልቅ ጥናት በ20 ብር ገዝቶ ማንበብ ይችላል፡፡)

ፌሚኒዝም ‹ጠላት› ብሎ የፈረጃቸው…

አንዱና ትልቁ ስጋት እየተባለ የሚወራው "ፌሚኒዝም ወንዶችን እንደጠላት ፈርጇል" የሚለው ስጋት ነው፡፡ እርግጥ የሴቶች የመብት እና የዕድል (opportunity) ዕኩልነት ጥያቄ የሚቀርበው ከወንዶች አንፃር ነው፡፡ ዕኩልነት እንዳይሰፍን እንቅፋት የሚፈጥረው ደግሞ አባታዊው ስርዓተ ማኅበር ነው፡፡ ስርዓተ ማኅበሩ ከወንዶች ባልተናነሰ በሴቶችም ነው የቆመው፡፡ ከብዙ ሺሕ ዓመታት ማኅበራዊ ዝግመተ ለውጥ በኋላ ሴቶችም ይሁኑ ወንዶች፣ ስርዓተ ማኅበሩ የወንድ የበላይነት እንዳለበት እንኳ እስከማይረዱበት ሁኔታ ድረስ ሥር ሰዷል፡፡ ፆተኝነት (sexism) ከቋንቋችን አንስቶ እስከ እያንዳንዷ የአኗኗር ዘይቤያችን ድረስ የበላይነትን ማፅኛ መሣሪያ ነው፡፡ የዚህ ሰለባዎች ደግሞ ወንዶችም ሴቶችም ናቸው፡፡ ስለዚህ የፌሚኒዝም የመጀመሪያው ጠላት ስርዓተ ማኅበሩ፣ በተለይም ይህን የሚያፀናው ፆተኝነት ነው፡፡

አንድ ምሳሌ እጠቅሳለሁ። የምዕራባውያን እና የአገራችን የሥም አሰያየም ስርዓትን ስንመለከት ሁለቱም ሴቷን ከነመፈጠሯ ለመዘንጋት ወንዱን ዘላለም ለማኖር የሚተጉ ናቸው። ፈረንጆች የቤተሰብ ሥም በሚባል ይጠራሉ፣ ሴት ልጅ የአባቷን የቤተሰብ ሥም ትወርስና ትጠራበታለች፤ ትዳር ስትይዝ ደግሞ "አሳዳሪዋ" ባሏ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ በባሏ የቤተሰብ ሥም መጠራት ትጀምራለች። እንግዲህ ያተኘነቱ ከመጠሪያ ሥሟ ይጀምራል ማለት ነው። በአገራችን ደግሞ ልጅ ባባቱ እና በወንድ አያቱ ሥም ይጠራል። እናቱ በልጇ ሥም ውስጥ ቦታ የላትም። ሃይማኖቶችም (ክርስትናን እንደምሳሌ ብንወስድ) ሴትን እስከነመፈጠሯ የሚዘነጉበት ግዜ ብዙ ነው። ኦሪት ዘ ፍጥረት ላይ እከሌ እከሌን ወለደ እያለ ሲዘረዝር ሰዎቹ ሴት ወልደው የማያውቁ ይመስላል። እስልምናን እንደምሳሌ ስንወስድ በቁርኣን ሥሟ የተጠቀሰችው ብቸኛዋ ሴት መርየም ብቻ ናት።

በሃይማኖት፣ ልማድ እና ባሕል የተሰናሰሉት ያተኘነቶች ሁሉ የፌሚኒዝም ጠላቶች ናቸው። ፌሚኒስቶች ጥያቄያቸው ቢለጠጥ ቢለጠጥ ምናልባት ልጅ በአባቱም፣ በእናቱም ሥም ይጠራ፤ ወይም ከሁለት በአንዱ (በልጁ ምርጫ) ይጠራ ሊሉ ይችላሉ። (ምሳሌ ነው እንጂ እንዲህ ዓይነት ንቅናቄ እስካሁን አልገጠመኝም) ይህ ለወንዱ የቀድሞ ዕድሉን ተሻሚ ስለሚሆን በጠላትነት የተፈረጀ ሊመስለው ይችላል። (ፌሚኒስቶቹ የቀድሞው በወንድ ሥም መጠራት ቀርቶ በሴት በምንጠራበት ስርዓት ይተካ ብለው ከተከራከሩ፣ ስለሴቶች የበላይነት መስበክ ጀምረዋል ማለት ነው - ይህ ወደፅንፈኛ ፌሚኒስትነት ያሻግረናል። ግን ‹ፅንፈኝነት› ያልነው አሁን አባታዊው ስርዓት የሚከተለው ስርዓተ ማኅበር ቀጥተኛ ግልባጭ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።)

‹ፅንፈኛ ፌሚኒዝም› አደጋው ምንድን ነው?

‹ፅንፈኛ ፌሚኒዝም› አንዳንዶች ‹የሴቶች የበላይነትን ለመፍጠር የሚደረግ ንቅናቄ ነው› ብለው ይላሉ፣ ሌሎች፣ ‹ፅንፈኛ ፌሚኒዝም ብሎ ነገር የለም፤ ቁርጠኛ ፌሚኒዝም ነው› ብለው ይከራከራሉ።

ብዙዎቹን ፌሚኒስቶች የሚያስማማው ትርጉሙ ‹ፅንፈኛ ፌሚኒዝም› (radical feminism) የሚባለው ፖለቲካን እንደመሣሪያ በመጠቀም (የፖለቲካ ሥልጣን በመያዝ) አሁን ያለውን አባታዊ ስርዓት በሕግ በማስገደድ በፈጣን ሒደት በመቀልበስ የዓለም ስርዓተ ማኅበርን አናውጦ፣ የወንዶች የበላይነትን በማስቆም፣ ወንዶች እና ሴቶች ዕኩል የሚታዩበት ዓለም መፍጠርን ግብ ያደረገ ንቅናቄ ነው። በግብ ደረጃ ከተራው ፌሚኒዝም የሚለይበት መሥፈርት ባይኖርም አካሔዱ ላይ ልዩነት አለው። ስኬት ማስመዝገብ ይችላል ወይ የሚለው ምናልባት ያጠራጥራል።

አንዳንድ ‹ፅንፈኛ ፌሚኒስቶች›፣ የፆታ መድልዖን ሲተረጉሙት በመደብ ይለዩታል፤ ‹ወንዶች ጨቋኝ መደብ፣ ሴቶች ተጨቋኝ መደብ ናቸው› በማለት፡፡ መፍትሔው ጨቋኙን መደብ መታገል ይሆናል፡፡ ሴቶች ወንዶችንም ሴቶችንም ጠቅልለው መግዛት ካልጀመሩ ለውጥ እንደማይመጣ የሚናገሩ አሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሴትን ያሳንሳል ብለው ያሰቡትን አቀራረብ በመቀየር የሴቷን መጽሐፍ ቅዱስ (Woman's Bible) ያዘጋጁ ሴቶች አሉ፡፡ ባስ ሲል ከወንድ ዕኩል የማያየኝን ሃይማኖት አልቀበልም በሚል ሃይማኖታቸውን እርግፍ አድርገው የተዉ አሉ፡፡ በወሲብም ላይ ወንድ ከላዬ አይሆንም ከሚሉ ጀምሮ ከወንድ ጋር አልተኛም እስከሚሉ ‹ፅንፈኛ ፌሚኒስቶች› አሉ፡፡

ትልቁ የፌሚኒዝም ተግዳሮት፣ እና ማንኛውንም ፌሚኒዝም በፅንፈኝነት እያስፈረጀ ያስቸገረው አስተሳሰብ ሴትን እንደተፈጥሮ አሽከር የመመልከት አባዜ ነው፡፡ ሴት ልጅን ለማሞካሸት ሌላ ምክንያት የሌለ ይመስል "ዘጠኝ ወር ማርገዟ" እና "እናትነቷ" ብቻ ነው ሲጠቀስ የሚሰማው፡፡ ይህም ማለት የሴት ልጅ ተግባር ‹መውለድ› እና የሰው ዘርን ማስቀጠል ብቻ ነው የሚል መደምደሚያ በውስጡ አዝሏል፡፡ ተፈጥሮ የእናትነትን ፀጋ፣ ከመምረጥ መብቷ ጋር ነው ለሴት የሰጠቻት፡፡ አባታዊው ስርዓት ሴትን ያለፈቃዷ የተፈጥሮ አሽከር እንድትሆን ይደነግጋል፡፡ ውሎዋም ከልጆቿ ጋር ማጀት ውስጥ መወሰን እንዳለበት ያምናል፡፡ ከዚህ አስተሳሰብ አንፃር መውለድን በራሷ ምርጫ እንድትወስን የሚታገለው ፌሚኒዝም ሁሌም ‹ፅንፈኛ› ነው፡፡

‹የፌሚኒዝምን ፅንፈኝነት› ጠለቅ ብሎ ላሰበው አስደንጋጭነቱ (ወይም ስጋትነቱ) ምንም ነው፡፡ የሚያስደነግጠው በአባታዊ ስርዓተ ማኅበር የሐሳብ አድማስ (mind-set) ውስጥ ቆመን ስለምናስበው ነው፡፡ ሲጀመር በትህትና ‹ወንድና ሴትን ዕኩል ማኖር እና ማየት› ከሚለው ንግግር ይልቅ ‹የወንዶች የበላይነትን ማፈራረስ› የሚለው ቃል ፅንፈኛ ቢመስልም፣ የሁለቱም ግብ የተንሰራፋውን ፆታዊ መድልዖን ማስቀረት ነው፡፡

የልኂቃን ፌሚኒስቶቹ ሥራ፣ ለገጠር ኮረዳ ምኗ ነው?

ፌሚኒዝምን ፍሬ አልባ እንደሆነ ለማስረዳት ከሚሰጡ ምሳሌዎች ዋነኛው ‹ከሥሙ ጋር ያልተዋወቁትን ሴቶች አልበጀም› የሚለው ትችት ነው፡፡ ሁሉም ፌሚኒስቶች እያንዳንዱን ጓዳ እያንኳኩ፣ እያንዳንዷን ሴት ነጻ ያወጣሉ ብሎ መመኘት የዋህነት ነው፡፡ እያንዳንዷ ፌሚኒስት ራሷን ነጻ ካወጣች፣ እያንዳንዱ ፌሚኒስት ራሱን ከፆተኝነት ነጻ ካወጣ ትልቅ ድል

ነው፡፡ የተደራጁት ፌሚኒስቶች የውጤታማነት (effectiveness) ችግር እንዳለባቸው እና መሬት በረገጡ የብዙኃኑ ሴቶች ችግር ላይ ከማተኮር ይልቅ በምናባዊው ርዕዮተ-ዓለማዊ ክርክር ግዜያቸውን እና አቅማቸውን እንደሚያባክኑ ይነገራል፡፡ እውነት ነው፡፡ ነገር ግን የፌሚኒስቶቹ ድክመት የፌሚኒዝምን አስፈላጊነት አያራክሰውም፡፡

የፌሚኒዝም ንቅናቄ ከገጠር ማጀት እስከ ከተማ ቤተ መንግሥት ድረስ መሆን አለበት፡፡ ልኂቃኑ ሴቶች ፓርላማ እንዲገቡ፣ ምኒስትር ሆነው እንዲሾሙ ጥረት ሲደረግ የገጠር ማጀት ውስጥ ላለች ኮረዳ ቀጥተኛም ባይሆን ተዘዋዋሪ ጥቅሞች አሉት፡፡ ካለችበት እርከን እስከላይኛው ጣሪያ እንደተምሳሌት የምታያት ሴት እና የሚበጃትን ሕግ እንዲወጣ የምትታገልላት ሴት ታገኛለች፡፡ እያንዳንዷ ፌሚኒስት ከሷ የሚጠበቀው ራሷን በአስተሳሰብ እና በኢኮኖሚ ነጻ ማውጣት ነው፡፡ የገጠር ኮረዳዋም ልኂቃኑ ሴቶች ከአባታዊው ስርዓተ ማኅበር ነጻ እያወጡ በመጡ ቀጥር ነጻ የመውጣት ዕድሏ እየሰፋ ይመጣል፡፡

ከዚህ በተረፈ፣ ፌሚኒዝም ሥሙ የሚጎድፈው ያለባሕሪው ነው፡፡ እጅግ በጣም ጥቂት ሴቶች መጠጥ ቤት ሲያዘወትሩ ወይም በሱስ ሲጠመዱ ፌሚኒዝም ይወቀሳል፡፡ ሴት ልጅ ‹በማጀት መወሰን የለባቸውም› መባሉ ሴቶችን አበላሸ ይባላል፡፡ የነዚህ ችግሮች ሰለባ የሆኑ ብዙ ወንዶች ጉዳይ ግን ተድበስብሶ ያልፋል፡፡ ይህ ትችት በራሱ አባታዊው ስርዓት ፌሚኒዝምን መልሶ ከሚታገልባቸው ሰበብ አስባቦች አንዱ ነው፡፡ ሱሰኝነትን የመሳሰሉ ችግሮች ለወንዶችም ለሴቶችም ችግሮች ናቸው፡፡ "በሴት አያምርም" የሚለው አስተያየት በራሱ ፆተኝነት ነው፡፡

እንደመደምደሚያ፣ የፆታ መድልዎን ለማስቀረት ሴት ልጅ ስትደፈር መቅጣት በቂ አይደለም፤ ሴት ልጅን የመድፈር ሐሳብ የማይመጣለት ወንድ መፍጠርን ይጠይቃል፡፡ ሴት ልጅ ትምህርት ቤት እንድትሔድ መፍቀድ አይበቃም፤ ተመልሳ የቤት ሥራ የምትሠራበት ጊዜ መስጠት ብቻም አይበቃም፤ ከወንድሟ ያነሰች እንደሆነች በቃልም ይሁን በተግባር የምናሳይበትን ፆተኝነት ከቋንቋችንም ይሁን ከባሕላችን ነቅለን መጣል አለብን፡፡

"...ለፍቅር ተኝተው፥ ለፀብ የወለዱኝ"
በምድር እንድኖር፥ ምክንያት ባይሰጡኝ
አገኝ እንደሁ ብዬ፥ ፍለጋ ጀመርኩኝ፣...።

...ፈልጌ፣ ፈልጌ - ፈልጌ፣ ፈልጌ...
ከመኝታ ቤቴ፥ ራስጌና ግርጌ፣
ከዓለሜ ወለል፣ ጣሪያና ግድግዳ
ያገኘሁት ነገር፣ ለኔ ሁሉ እንግዳ
ዓለም ሙሉ 'ቤቶች'፣ እኔ ብቻ ባዳ።

ተወልዶ እና ኑሮ በፈተና መሐል
መሞት "መርዶ" ሆኖ እንዴት ይለቀሳል?
ለማይቀሩለት ሞት፣ በስቃይ መሰንበት
ኮሶ እየጨለጡ፣ ይጣፍጣል ማለት
በሽታ እየጠጡ፥ መዳንን መመኘት
በከንቱ መሞኘት፤
'ኑሮ' ማለት 'ሞት' ነው፣
ምጡ የሚጀምር የተወለዱ'ለት።

እያልኩኝ ሳማርር፣
ሞትን ለማዋለድ፥ እያማጥኩኝ ሳድር፣
'መውደድሽ ገጠመኝ፣
እመንገዴ ቆሞ፥ ከምጤ አናጠበኝ፣
ያለምንም ምክንያት፣
ዝ'ምምም... ብሎ መውደድ፥ ለመወደድ ማማጥ
ለመሞት ከመኖር፣
ለመኖር ሞክሮ፥ ተፍጨርጭሮ ማጣት፤'

ከምክንያት ቀሎ፣ ከሞት ምጥ ግን ከብዶ
ፊትለፊቴ ቆመ፣
...ቢሞቱለት አይቆጭ፣ ኗሪ ምክንያት ወልዶ።

(ታኅሣሥ 4፣ 2008)

“ፆተኝነት” (sexism) ውስጤ ነው

(ሰኔ 19፣ 2008)

ምናልባት ራሴን “ውስጥ ውስጡን ፌሚኒስት ነኝ” እያልኩ ስገልጽ ሰምታችሁ ታውቁ ይሆናል። እውነት ነው። ነገር ግን ፆተኛም ነኝ።

’ዛራ እና ቻንድራ’ በቃና ቲቪ እየታየ ያለ ተከታታይ ፊልም ነው። አልከታተለውም፤ ግን ርዕሱ ላይ የተጠቀሱት ሰዎች የተፋቃሪ ጥንዶች ሥሞች መሆናቸው ግልጽ ነው። እናም፣ በተደጋጋሚ ቻንድራን የሚለውን ሥም የሴቷ፣ ዛራ የሚለውን ደግሞ የወንዱ ሥም አድርጌ ስወስደው ነበር። ተራ ስህተት ነው ብዬ አልተቀበልኩትም። ውስጤ ያለው ፆተኝነት ቀድሞ የሚጻፈው የወንዱ ሥም ነው እያለ ስለሚነግረኝ ነው። በሕይወቴ ሲነገረኝ የነበረው በዚህ ቅደም ተከተል ነው፤ አዳም እና ሔዋን፣ ሮሜዎ እና ጁሊዬት… የወንዱ ሥም ሁሌ ቀድሞ ይመጣል።

በየለት ሕይወቴ፣ ፆታቸው ሳይገለጽልኝ ጎበዝ፣ የተማሩ እና ስኬታማ ስለሆኑ ሰዎች ሲነገረኝ ሳላስተውል የማስበው ወንድ እንደሆኑ ነው። የቢሮ ጸሐፊ ሳስብ ሴት፣ ማናጀሩ ደግሞ ወንድ እንደሆነ አድርጌ ነው። ይህ የሆነው ጥሩ ሰው ስላልሆንኩ አይደለም። ይህ የሆነው ባለፉት ምዕተ ዓመታት አባታዊው ስርዓት የአደባባይ ሚናዎችን ለወንዶች ብቻ ገድቦ፣ ወንዶች ተወዳድረው ወንዶች እንዲያሸንፉ ስለሚያደርግ ነው። ቀልቤ ግምት የሚያሳልፈው ታሪክ አስልቶ ነው። ምክንያቱ - ያም ሆነ ይህ፣ ፆተኝነቴን አይቀንስልኝም።

ሌላው ቀርቶ ስለወሲብ ሳስብ ሳይቀር ለተወሳሳቢዎቹ ጥንዶች የተለያየ ሚና ሰጥቼ ነው። ወንዱን እንደአድራጊ፣ ሴቷን እንደተደራጊ። ብዙ ግዜ ‘ይች ሴት በብዙ ወንዶች ተደርጋለች’ ብዬ ሳስብ ራሴን ይዤዋለሁ፤ ነገር ግን ‘ይህ ሰው በብዙ ሴቶች ተደርጓል’ ብዬ አስቤ አላውቅም፤ ወይም ለወንዱ ሲሆን ጀብዱ ነው፣ ለሴቷ ሲሆን ሽርሙ*ና።

በአማርኛ ቋንቋ፣ ‘ወንድ’ የሚለው ቃል ‘ጎበዝ’ ከሚለው’ጋ አንድ ዓይነት ትርጉም ይሰጣል። ይሄን ቃል ላለመጠቀም እፈልጋለሁ፤ ነገር ግን የሆነ አሪፍ ነገር ያደረገ ሰው ሲገጥመኝ ለማበረታቻ ‘ወንዳታ’ እያልኩ ሳወድስ በተደጋጋሚ ራሴን ታዝቤዋለሁ። ስኬታማ መሆን ወንድ መሆን ይጠይቅ ይመስል!

ነገር ግን እኔ ብቸኛው ፆተኛ አደለሁም። ሁላችንም ነን። በየለት ተግባራችን ፆታዊ መድሎዎችን እንተገብራለን። የየለት ፆተኝነት አደገኛ ነው። ምክንያቱም ታግለን እንዳንቀርፋቸው እንኳን ጥቃቅንና ከመልመዳችን የተነሳ የማናስተውላቸው ናቸው። በቋንቋችን፣ በሐሳባችን፣ በቤት ውስጥ፣ በሥራ ቦታ፣ በመዝናኛ ቦታዎች እና በየለቱ እግራችን በሚረግጥባቸው ሥፍራዎች ውስጥ የሴቶችና የወንዶች ሚና ከፋፍለን ሳይታወቀን ፆተኝነትን እንድናራምድ ያደርገናል - የየለት ፆተኝነት።

ስለዚህ፣ ፆተኝነትን እየታገልኩ ከሆነ፣ በዙሪያዬ ያለውን ያክል በውስጤ ያለውንም ፆተኝነት መዋጋት አለብኝ።

የተዋሐደን ፆተኝነት

(ነሐሴ 17፣ 2009)

ይህ ጽሑፍ ስለ ፍትሕ ነው። አንባቢዎቼን በትህትና አስቀድሜ የምጠይቀው ነገር ቢኖር የፆታ፣ የሃይማኖት፣ የባሕል፣ የፖለቲካ ወገንተኝነት መነፅሮቻችሁን አውልቃችሁ በፍትሕ መነፅራችሁ እንድታነቡኝ ነው።

የተዋሐደን ፆተኝነት ስንል ምን ማለታችን ነው? ምንጮቹ ምን ምን ናቸው? ውስጣችን ያለው ይህ ፆተኝነት ምን ያህል ችግር ይፈጥራል? የተዋሐደንን ፆተኝነትን እንዴት እንቅረፈው?

መግባቢያ ስለፆተኝነት

ፆተኝነት ማለት በአጭሩ 'ፆታዊ መድልዖ' ማለት ነው። በዓለማችን እጅግ የተንሰራፋው ለወንዶች የሚያደላው ወይም አባታዊው ስርዓተ ማኅበር ነው። (እርግጥ እጅግ ጥቂት ሆኑ እንጂ እናታዊ ስርዓተ ማኅበሮችም አሉ። ለምሳሌ ሕንድ አገር ሜጋላያ ስቴት ውስጥ የሚገኙት ጎሳዎች ሀብት የሚተላለፈው ከእናት ወደሴት ልጅ ነው። በዚህ ስርዓተ ማኅበር የትምህርትና መሰል ዕድሎች ከወንዶች ይልቅ ለሴቶች ይመቻቻሉ። ይህን ምሳሌ በዓለም ከተንሰራፋው አባታዊው ስርዓት አንፃር ከቁብ ሳልቆጥረው ላልፍ እችል ነበር። ነገር ግን የእነዚህ ጎሳዎች እናታዊ ስርዓት ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ እዚህ መድረሱ አባታዊው ስርዓትም ሆነ እናታዊዋ በማኅበራዊ ብሒል የሚገኙ እንጂ ተፈጥሮ ያከፋፈለችን ሚና አለመሆኑን ስለሚያሳይ ነው።) የአገራችን ስርዓተ ማኅበር ከጥግ እስከ ጥግ አባታዊ ነው። ይህንን ስርዓተ ማኅበር ለመቀልበስ እና ፍትሐዊ ስርዓተ ማኅበር ለመመሥረት የሚደረጉ የተደራጁም ይሁን ያልተደራጁ ንቅናቄዎችን ሴታዊነት እንላቸዋለን። ('እንስታዊነት' የእንግሊዝኛውን 'Feminism' በቀጥታ የሚተካ ቢሆንም፣ አማርኛችን ስርዓተ ፆታ (gender) ያልተጫነው 'ሴት' የሚል ሥነ ተፈጥሯዊ (biological) ልዩነቱን ብቻ የሚገልጽ ቃል ስላለው 'ሴታዊነት' የሚለውን መርጫለሁ። በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ሴታዊነት ማለት "ፆታዊነትን መቃወም እንዲሁም ሴቶች ከወንዶች ዕኩል መብትና ዕኩል ዕድል እንዲያገኙ መታገል" የሚል ብያኔ ይኖረዋል።)

የተዋሐደን ያተኝነት…

ስልካችንን የኋላ ኪሳችን አስቀምጠነው ብንሰረቅ ማነው ተወቃሹ? እንዝህላልነታችን ወይስ ሌብነቱ? በመርሕ ደረጃ ሌብነት በማንኛውም ሁኔታ ነውር ነው። ይህ ምሳሌ “ነውር ማለት ሁላችንም በራሳችን ላይ እንዲደረግብን የማንፈልገው ነገር ነው” የሚል ብያኔ እንድናገኝ ይረዳናል። ስለዚህ "ቤታቸውን ከፍተው ሰውን ሌባ ያሰኛሉ" የሚለው አባባል የሌብነትን ነውር አቃልሎ ያሳያል እንጂ አያስቀረውም። ልክ እንደዚህ ሁሉ የሴት ልጅ መደፈርን ነውርነትም እንዲህ በሰበብ ሊያስተባብሉ የሚሞክሩ ብዙ ናቸው። ነገር ግን በአገራችን ኢትዮጵያም ሆነ በአህጉራችን አፍሪካ ለሴቷ መደፈር እራሷኑ ተጠያቂ ማድረግ የተዋሐደን ያተኝነት ማሳያ ነው። ዩጋንዳ በየካቲት 2006 አጭር ቀሚስ የሚከለክል ሕግ አውጥታ ነበር። ከዚያ ቀደም ብለው የወጣቶች ሚኒስትሩ "ጨዋነት የጎደለው አለባበስ የለበሱ ሴቶች ሲደፈሩ ከራሳቸው በቀር ማንም ተጠያቂ መሆን የለበትም" ብለው ተናግረው ነበር። ተመሳሳይ ንግግሮች በሁሉም የአፍሪካ አካባቢዎች የተለመዱ ናቸው። በአገራችንም፣ አንዲት ሴት በወንድ ጥቃት ደረሰባት የሚለው ዜና ሲሰማ ገና፥ “ምን አድርጋው?” የሚለው ምላሽ ይከተላል። ጥያቄው፣ ሴት ልጅ ምክንያታዊ ጥቃት ይገባታል ከሚል የተዋሐደን አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው። ለጥቃቱ ከማዘናችን በፊት ቀድሞ የሚመጣብን ጥያቄ “ምን አድርጋው?” የሚለው ከሆነ የተዋሐደን ያተኝነት ሥር የሰደደ ነው ማለት ነው።

በቅርቡ ይፋ የሆነ (ነገር ግን ውጤቱ ከቀደምት ጥናቶች ጋር የሚመሳሰል) ጥናት እንደሚያስረዳን፣ በኢትዮጵያ 63% የሚሆኑት ሴቶች "ባል ሚስቱን ወጥ ካሳረረች፣ ከጨቀጨቀችው፣ ሳትነግረው ዙረት ከሔደች ወይም መሰል ጥፋት ካጠፋች… ቢመታት ምንም አይደል" ብለው ያምናሉ። ባንፃሩ አሳማኝ ምክንያት ካለ ሴት ልጅ መመታት አለባት ብለው የሚያምኑት 28% የሚሆኑት ወንዶች ብቻ ናቸው። ለምን ሴቶች የገዛ ራሳቸውን ጥቃት ተገቢ ነው አሉ። ለምን ከሴቶቹ ቁጥር ያነሱ ወንዶች መምታቱ ተገቢነት ላይ ተስማሙ? መልሱ ቀላል ነው። የተዋሐደን ያተኝነት የገዛ ጥቃታችንን በራሱ ተቀባይነት እንዳለው ነገር እንድንቀበለው ያታልለናል። ወንዶች ከሴቶች የተሻለ፣ የትምህርትና የመረጃ ዕድል ስላላቸው የሴት ልጅ ጥቃት በማንኛውም ሁኔታ ተገቢ አለመሆኑን መረዳታቸውንም ውጤቱ ይጠቁመናል። በዚህም ያተኝነት በትምህርት የሚቀረፍ ነገር መሆኑን በቀላሉ ማየት ይቻላል።

የተዋሐደን ፆተኝነት ከማኅበረሰቡ የተማርነው፣ የኑሮ ዘዬያችን የተገነባበት እና በየዕለቱ የምንከተለው ነገር ግን ጨርሶ የማናስተውለው ከመሆኑ የተነሳ "ትክክለኛ" የሚመስለን ነገር ነው። ሆስፒታል ሔደን ነጭ ጋዋን የለበሰች ሴት ስትገጥመን [ነርስ እንደሆነች እርግጠኛ በመሆን] "ሲስተር" የምንላት፣ ነጭ ጋዋን የለበሰ ሲገጥመን "ዶክተር" የምንለው የተዋሐደን ፆተኝነት አስገድዶን ነው። አንድ ቀን መሳሳታችንን ብናውቅ እንኳን ደግመን መሳሳታችንን እንቀጥላለን። በተመሳሳይ የቢሮው ሥራ አስኪያጅ እንዲሁ ስናስበው ወንድ አድርገን ነው፤ ጸሐፊዋን ደግሞ ሴት። "ማናጀሩ የታል?" ስንል ወንድ እንደሆነ አንጠራጠርም። የኩሽና ሥራ በጥቅሉ የሴት ነው ብለን ነው የምናስበው። ምግብ አብሳይ ስንባል በምናባችን ሴት እንስላለን፤ የትልቅ ሆቴል ሼፍ ስናስብ ግን ወንድ ነው በምናባችን የሚመጣው። ምክንያቱም ምግብ አብሳይነትም ቢሆን ደረጃው እያደገ ሲመጣ ለሴት እንደማይገባ የተዋሐደን ፆተኝነት ሹክ ይለናል።

የፍቅር ግንኙነቶች ላይ ወንዱ ራስ፣ ሴቷ ንዑስ ናት። በታዋቂ የፍቅር ትርክቶቻችን የወንዶቹን ሥም የምናስቀድመው ያለነገር አይደለም። ሮሚዮ እና ጁልየት። መጽሐፍ ቅዱስ ላይም አዳምና ሔዋን፣ አብርሃምና ሳራ ሲባል ነው እየሰማን ነው የኖርነው። ተራ ነገር ይመስላል፤ ነገር ግን አዕምሯችን ወንድና ሴትን የሚያስቀምጥበት ቅደም ተከተል አሳባቂ ነው። ለዚህም ይመስላል ባለትዳሮችን ስንጠራ ‹ባል እና ሚስት› እንጂ ‹ሚስት እና ባል› የሚለው አማርኛ አፋችን ላይ የማይመጣልን። የተዋሐደን ፆተኝነት በይፋ የሚጋለጠው በንግግራችን ስለሆነ እንጂ በተግባርም (መብትና ዕድል በመስጠት) የምናስቀድመው ወንዱን ነው። ማኅበረሰቡ ወንዱን ለቤተሰቡ እንደብቸኛ የገቢ አስገኚ ይቆጥረዋል፤ ስለዚህ የፍቅር ግንኙነቶች በወንዱ የኢኮኖሚ የበላይነት ላይ ነው የሚመሠረተው። በፍቅር ግንኙነቶች ሴቷ በትምህርት ደረጃ፣ በኢኮኖሚ አቅም፣ በቁመት… ወዘተ በልጣ ከታየች ግንኙነቱ ውስጥ የሆነ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል። ምክንያቱም የተዋሐደን ፆተኝነት ያስተማረን እና አምነን የተቀበልነው መብለጥ የወንዱ ድርሻ እንደሆነ ብቻ ነው።

የወሲብ ግንኙነታችን ሳይቀር ለወንዱና ሴቷ የተለያየ ነገር እንደሆነ አስመስሎ የተዋሐደን ፆተኝነት ይነግረናል። ጥንዶች ፍቅር ሲሰሩ ወንዱ ‘አድራጊ’ ሲሆን፣ ሴቷ ‘ተደራጊ’ ነች ተብላ ነው የምትታሰበው። በዚህ አይወሰንም፣ ድርጊቱ ለእሱ ጀብዱ ሲሆን፣ ለሷ ግን እንደብልግና ይቆጠራል። በአንድ ቀን ትውውቅ አንድ ወንድ ከሴት ጋር ቢያድር እሱ በጀብድ ሲደነቅ፣ እሷ በአመንዝራነት ትወቀሳለች። ሴት ስትሰደብ ‘ሸርሙጣ’ ተብላ ከሆነ፣ ወንዱ ግን ‘የሸርሙጣ ልጅ’ ነው የሚባለው። አድሎው በስድብ ሳይቀር ይንፀባረቃል። ‘እናትህ እንዲህ ትሁን’ የሚለው ስድብ የሚሆነው

በሴቷ ዙሪያ ስለሚያጠነጥን ነው። ብቻውን የሚኖር ወንድ ላጤ ይባላል፤ ላጤ የሚለው ቃል ውስጥ ‹አንድ ብቻ› ከመሆን በስተቀር የሚናገረው ነገር የለም። ሴት ግን ብቻዋን ስትኖር ‘ጋለሞታ’ ነው የምትባለው፤ መንፈሱ ሴት ካለወንድ ዋጋ የላትም የሚል ነው። ‘ጋለሞታ’ የሚለውን ቃል የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ማዕከል ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሲተረጉመው እንዲህ ነው፣ “1. ዕድሜዋ ለትዳር ደርሶ ያላገባችና ብቻዋን የምትኖር ሴት። 2. ባል አግብታ የሞተባትና ብቻዋን የምትኖር ሴት። 3. ሸርሙጣ፣ አመንዝራ ሴት። 4. ባል ፈታ ብቻዋን የምትኖር ሴት።”

የሃይማኖት አመለካከቶች

በኢትዮጵያ አብዛኞቹ ሰዎች የክርስትና እና እስልምና እምነቶች ተከታይ ናቸው። የሕዝቡ ባሕልም በሃይማኖታዊ እሴቶች ላይ የተመሠረተ ነው ቢባል የተጋነነ አይሆንም። በሚገርም ሁኔታ ሁለቱም እምነቶች ወንድን የበላይ፣ ሴትን የበታች አድርገው ይስላሉ። ጉዳዩ ከሥነ ፍጥረት ይጀምራል። በሁለቱም እምነቶች አምላክ ወንዱን ከፈጠረ በኋላ ሴቲቱን ከወንዱ አካል ስባሪ ነው የፈጠራት።

በክርስትና ለሰው ልጅ ከገነት መባረር ተወቃሽዋ ሴት ናት። ለዚህም “በፀነስሽ ግዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ። ፈቃድሽም ወደባልሽ ይሆናል። እርሱም ገዥሽ ይሆናል” ይላል (ዘ ፍጥረት 3/16)። ሌሎችም ተመሳሳይ አንቀፆች አሉ። "ቅዱስ" መጽሐፎች ውስጥ እንዲህ ዓይነት ነገሮች መጻፋቸው ያስደነግጣል። ለዚህም ይመስላል ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓያቆብ "ይህ የሙሴ ሕግ ሴትን ከፈጠረ አምላክ የመጣ ሊሆን አይችልም" ያለው። ነገር ግን መሰል አንቀፆች ያሉት በኦሪት ብቻ ሳይሆን በአዲስ ኪዳንም ጭምር ነው፤ ወደቆሮንቶስ ሰዎች 1ኛ፣ ምዕራፍ 11፣ ቁጥር 3 ‹የሴት ራስ ወንድ ነው› ይላል። ብሉይ ኪዳን የዘር ሐረግ ሲቆጥር የወንዶቹን ነበር የሚቆጥረው፤ ሐዲስ ኪዳን ላይ ደግሞ የሕዝቦች ብዛት ሲጠቀስ የሴቶችን እና የሕፃናትን ቁጥር አይጨምርም።

በእስልምና ሥሟ ቁራን ላይ የተጠቀሰችው ብቸኛዋ ሴት መሪየም ናት። በተጨማሪም (የሴቶች ምዕራፍ እየተባለ በሚጠራው) ምዕራፍ 4፣ ቁጥር 11 ላይ “አላህ በልጆቻችሁ (ውርስ በሚከተለው)፣ ያዛችኋል፣ ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ቢጤ አለው” በማለት በቁጥር አንድ ወንድ የሁለት ሴቶች ዋጋ እንዳለው ለማስቀመጥ ይሞክራል። በተመሳሳይ፣ ምዕራፍ 2 (አል-በቀራህ) ቁጥር 282 ላይም ለምስክርነት ከአንድ ወንድ ጋር ዕኩል የሚቆጠሩት ሁለት ሴቶች መሆናቸውን ይናገራል።

እምነቶቻችን ከልጅነታችን እስከ እውቀታችን ድረስ ሲሰበኩልን ያደግን እንደመሆኑ ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ትውልድ ሲቀባበልባቸው እዚህ የደረሱ እንደመሆኑ መጠን ውስጣችን የተዋሐዱ አስተሳሰቦችን የመቅረፅ ኃይላቸው ከፍተኛ ነው።

ሥነ ጽሑፍ፣ ጥበብ እና ሚዲያ

"ድንበር ስታቋርጥ የተገኘች በሕግ ትቀጣለች" የሚል ማሳሰቢያ ብትመለከቱ ለወንዱም ተግባራዊ የሚሆን ይመስላችኋል? "ድንበር ሲያቋርጥ የተገኘ በሕግ ይቀጣል" የሚል ቢሆንስ? ይህ የተዋሐደን ፆተኝነት ውጤት ነው። የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ‹ሰው› የሚለውን በተባእታዊ ፆታ ሲገልጹት በውስጠ ታዋቂነት ሴቷ መኖሯ ይታወቃል። ይህንኑ በእንስታዊ ፆታ ብንገልጸው ግን የሚሠራው ለሴቷ ብቻ ነው። በጉልህ ስንመለከተው ችግር ያለው አይመስልም ምክንያቱም ሴቷን ንዑስ የማድረጉን ነገር የተዋሐደን ፆተኝነት እንደ "ትክክል" (normal) እንድናየው አለማምዶናል።

ብዙ ቃላቶቻችን እና ተረትና ምሣሌዎቻችን ፆተኝነት የተዋሐዳቸው ናቸው። እኛ ግን ሳናስተውል በየዕለቱ እንጠቀምባቸዋለን። ይህም ማለት አስተሳሰቦቹን በማኅበረሰባችን እናፀናባቸዋለን፤ ለቀጣዩ ትውልድም እናወርሰዋለን።

የጥንት እና መካከለኛው ዘመን ፈላስፎችም ስለሰው ልጅ ሲጽፉ ሴትን እየገደፉ ነው። ጆን ሎክ 'ሁሉም ሰዎች የተወለዱት ዕኩል ነጻ ሁነው ነው' ("All men are born equally free") ብሎ ከጻፈ ከአንድ ክፍለ ዘመን በኋላ እነቶማስ ጀፈርሰን የአሜሪካንን "ሁሉም ሰዎች ዕኩል ነው የተፈጠሩት" የሚል መሪ ሐረግ ሕገ መንግሥታቸው ውስጥ በመከተት የወንዶች (በርግጥ ያውም የነጭ ወንዶች ነው) መንግሥት መሥርተዋል። ምንም እንኳን በእንግሊዝኛው 'man' የሚለው እና በአማርኛ 'ሰው' የሚለው ለወንዱም፣ ለሴቷም የወል መጠሪያ መስሎ ቢታይም፣ ሴቷን እንዴት ሊገድፍ እንደሚችል ከላይ የጠቀስነው ጥሩ ማሳያ ይመስላል።

ቮልቴር የፈረንሳይ አብዮትን ያነሳሳ ጸሐፊ ነው ተብሎ ይታመናል። የቮልቴር ፍትሐዊነት ሴት ጋር ሲደርስ ይቆም ነበር። ‹ካንዲድ› የተሰኘው የተውኔት ሥራው ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው ይባላል። ቮልቴር ሴትን አሳንሶ ከማየቱ የተነሳ በጣም የሚወዳትን ሚስቱን ሲያቆላምጣት "ሴት ከመሆኗ በቀር እንከን የሌለባት ሰው" እያለ ነበር። የዓለምን ልማዳዊ አስተሳሰብ የፈተኑ ፈላስፎች ሳይቀሩ በዚህ ጉዳይ ወድቀው ተገኝተዋል። ዕውቁ ፈረንሳዊ ፈላስፋ ዣን ዣክ ሩሶ "የሴቶች ተግባር መሆን ያለበት ባሎቻቸውን ማስደሰት፣

ማፍቀር፣ ማገልገልና መጥቀም እንዲሁም ሕፃናትን ማስተማር፣ መንከባከብና ማሳደግ ነው። ሴቶች የሚማሩት ትምህርትም በዚህ ዓላማ መቀረፅ አለበት" ብሏል። ይህንን የሚያስተጋቡ ዛሬም አሉ። የሴትን ተፈጥሯዊ የመውለድ ፀጋ ለባርነቷ እንዲዳርጋት የሚከራከሩት የተዋሐደን ፆተኝነት ቢጋርዳቸው እንጂ ከክፋት አይመስለኝም።

የታይም መጽሔት ከዓመታት በፊት ‹ፓሪስ ሒልተን፣ ሊንድሴይ ሎሃን እና ብሪትኒ ስፒርስ› የዱርዬ ባሕሪ አሳዩ ተብሎ ትልቅ አጀንዳ በሆነበት ግዜ ‹Girls gone bad› (ሴቶች መረን ወጡ) የሚል አስተያየት አትሟል። ሦስት ዝነኛ ወንዶች በየፊናቸው ጋጠ ወጥነት የተሞላበት ድርጊት ቢያደርጉ (ያደርጉማል) ግን ‹ወንዶች ሁሉ ተበላሹ› የሚል ርዕሰ ዜና ይዞ ይወጣል ብሎ ማሰብ ይከብዳል። በቅርቡ የእንግሊዟ ጠቅላይ ሚኒስትር ከስኮትላንዷ ቀዳማይ ሚኒስትር ጋር ኒኮላ ስቱርጂዮን ጋር ያደረጉትን ስብሰባ በሽፋን ገጹ ይዞ የወጣው ‹ዴይሊ ሜይል› የተባለ ጋዜጣ እንደትልቅ ጉዳይ ያወራው አጭር ቀሚስ ለብሰው እግራቸው መታየቱን ነበር (‘Never mind Brexit, who won Legs-it’)። በቅርብ ግዜ ውስጥ የወንድ መራሔ መንግሥታት ስብሰባ ላይ አለባበሳቸው የሽፋን ገጽ ዜና ሆኖ የሚያውቅ አይመስለኝም። (ከተዋሐደን ፆተኝነት አንፃር “የወንዶቹ አለባበስ ኖርማል ስለሆነ ነው” የሚል አስተያየት ሰጪ እንደማይጠፋ እገምታለሁ።)

‘የቤክዴል ፈተና’ የሚባል ፊልሞች ላይ የሚደረግ የሴታዊነት ፈተና አለ። መለኪያው ቀላል ነው። ፊልሙ ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ ሴት ገጸ ባሕሪዎች ወንድ በሌለበት ትዕይንት ላይ ቀርበው ከወንድ ውጪ ሌላ ወሬ ካላወሩ ፊልሙ ፈተናውን ይወድቃል። ይህንን ፈተና የምንወዳቸው ፊልሞች ሁሉ ይወድቃሉ። ይህ የሚሆነው ደራሲዎች የእውነታውን ዓለም ስለሚያንፀባርቁ [ብቻ] አይደለም፤ የተዋሐደን ፆተኝነት ሴቶች ከወንዶች ውጪ አጀንዳ የላቸውም ብለው እንዲያስቡ ስለሚያስገድዳቸው እና በዚያው መሠረት ገጸ ባሕሪዎቻቸውን ስለሚስሉ ነው። የአገራችን ፊልሞች የፆታ መድልዖን ለማውገዝ ገጸ ባሕሪ ሲፈጥሩ አይታዩም። ይልቁንም የፆታ መድልዖውን የሚና ክፍፍል እንደሆነ ለማሳመር ሲውተረተሩ እንጂ።

የአገራችን ጋዜጠኞች እና ጸሐፍት መጽሐፍም ይሆን መጣጥፍ ሲጽፉ ሴት አንባቢ ያላቸው አይመስሉም። “አንባቢ ሆይ፣ ከዚህ በመቀጠል የምጽፍልህ ታሪክ…” ዓይነት ይዘት ያለው ትረካ ይከተላሉ። ይህ ግን ድንገት የበቀለ አይደለም። የጥንት ሊቃውንት ሲጽፉ ያነበናል ብለው የሚያስቡት ወንዱን ብቻ ስለነበር፣ ለተባእት አንባቢ ነበር የሚጽፉት። የጥንት አዋጆች አገር የወንዱ እንደሆነ ነበር የሚናገሩት። ዐፄ ዮሐንስ (አራተኛ) አገርን በእናት፣ በሚስት፣ በሴት ልጅ ሲመስሉ እያናገሩ ያሉት ወንዱን መሆኑ

አያጠራጥርም። ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ የአድዋ ጦርነትን ሲያውጁ “ያለህን ይዘህ ተከተለኝ” ሲሉ ለወንዱ ነው ጥሪ ያቀረቡት። ሴቷ ምንም እንኳን ከዘማቹም ከደጀኑም ወገን ብትኖርም በአዋጅ ለመጠራት ቁብ አትበቃም ነበር። ይህ ዘመን ተሻግሮም አልቀረም። ዛሬ፣ ዛሬ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋዜጣዊ መግለጫ ሲያወጡ እና የምርጫ ቅስቀሳ ሲያደርጉ፣ “የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፣ ገዢው ፓርቲ ያደረሰብህን በደል እኔ አቀልልሃለሁ” በማለት ነው። አገርን የተባእቱ ብቻ ማድረግ የተዋሐደን ፆተኝነት ክፉ ስጦታ ነው።

የአባት ውርስ

የአባታዊው ስርዓተ ማኅበር ክብርን ከአባት ወደ ወንድ ልጅ ነው የሚያወርሰው። በቅርብ ግዜ በአዋጅ እስከሚቀየር ድረስ አባት እና እናት ያፈሩት ሀብት እና ንብረት ሕጋዊ ወራሽ ወንድ ልጅ ነበር። ሴት አማራጭ ሲጠፋ ነው አባቷን የምትወርሰው። በፖለቲካውም፣ የአባቱን ንግሥና ለመውረስ የሚበቃው ወንድ ልጅ ነው። የልጅ እያሱ የዳግማዊ ምኒልክን መንበር ለመውረስ (ልጅ እያለች የልጅ ልጅ) መታጨቱ፣ የአልጋወራሽ ተፈሪ መኮንን ባለ ሙሉ ሥልጣን የንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ እንደራሴነት ሴት ለቦታው አትመጥንም ከሚለው እሳቤ የሚመነጭ ነው። (በነገራችን ላይ 10 ዓመት ኢትዮጵያን በአስቸኳይ ግዜ አዋጅ የመራው የደርግ ኮሚቴ አንዲት ሴት እንኳ አባል አልነበረውም። ሕወሓት አማፂ ቡድን እያለ "የፌሚኒዝም ዝንባሌ የታየባቸው" አባላቱ ላይ ክስ ያቀርብ ነበር። አሁንም ድረስ በውሳኔ ሰጭ ቦታዎች ላይ የሚገኙት ሴቶች ቁጥር በጣም ትንሽ ነው። የመንግሥታት ስርዓቶቻችንን የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር ሁሉም ለሴት ዕድል አለመስጠታቸው አንዱ ነው።)

ሌላው ቀርቶ ሥም አወጣጥ ላይ የአባት እና የወንድ አያት ሥምን የሚከተል መሆኑ በአባት መጠራትን አኩሪ ያስመስለዋል፤ ‹የሴት ልጅ› የሚለው ሐረግ ስድብ የሆነውም ያለነገር አይደለም። የተዋሐደን ፆተኝነት ወንድነትን እንደታላቅነት ከአያት ላባት፣ ካባት ለልጅ እያወረሰን ስለመጣ ነው። አሁን ጥያቄው፣ ‘እኛስ ለልጆቻችን ምንድን ነው የምናወርሳቸው?’ የሚለው ነው።

ምን ይበጃል?

ስር የሰደደ ባሕላችንን፣ እምነታችንን፣ ቋንቋ እና ልማዳዊ አሠራራችንን ፍትሐዊ ማድረግ ቀላል ሥራ አይደለም፤ በአንድ ትውልድ የሚጠናቀቅም ነገር አይሆንም። ያውም ደግሞ ጉዳዩ ብዙ ተቃዋሚ አለው። ምክንያቱም አባታዊው ስርዓተ ማኅበር የመቀልበሱን ሒደት የሚቋቋምበት ልማድን

የማፅኛ መከራከሪያዎች አሉት። የሆነ ሆኖ፣ ስርዓተ ማኅበሩ በፍትሐዊ ስርዓተ ማኅበር መተካት አለበት የሚሉ ሁሉ የበኩላቸውን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ መነሻ ሊሆኑ ይችላሉ፣

1. ሴቶችን እና ወንዶችን የምንመለከትበት መንታ ምድብ (double standard) እንዳለን ነገር ግን በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ሴቶች ከወንዶች ዕኩል መታየት እንዳለባቸው አምኖ መቀበል እና እያንዳንዷን የሕይወት እርምጃ መመርመር፣

2. የሥነ ጽሑፍ ሰዎች እና ደራሲዎች ከሥራዎቻቸው ውስጥ ፆተኝነትን ለማስወገድ መትጋት፣ በትረካቸው ለተባእት በመተረክ ፈንታ ለብዙኃን (ወይም እንደተቀናቃኝ አማራጭ ለእንስት) ማድረግ፣ ሴታዊነትን የሚያራምዱ ሥራዎችን በማዘጋጀት የባሕል አብዮቱን መምራት፣

3. ዝነኞች እና ሕዝባዊ ተፅዕኖ መፍጠር የሚችሉ ሰዎች፣ የቴሌቪዥን እና የሬዲዮ ፕሮግራም አቅራቢዎች ራሳቸውን የሴታዊነት አራማጅ እንዲያደርጉ ንቅናቄ ማድረግ፣ በተገኘው አጋጣሚ ፆተኝነትን የሚዋጉ መልዕክቶች እንዲያስተላልፉ ማድረግ፣

4. የሴታዊነት አራማጅ የሕትመት ውጤቶችን ማዘጋጀት፣ በተለያዩ ጦማሮች የአደባባይ ፆተኝነትን መተቸት እና ለጥበብ ሥራዎች የፆተኝነት እና ከፆተኝነት የፀዳ ምድብ ማውጣት፣ ወዘተረፈ።

ልጅ ሳለሁ የቸገረኝን፥ ያማረኝን ሁሉ፣
ገዛሁና ኮተት፥ በእቅፌ ሙሉ፣
ደስታዬን ፈለግኩት፥ ከሸቀጡ ተርታ፣
እንዲህ በቀላሉ፥ መች ልቤ ሊረታ?

ባ‘ለም ላይ ሲኖሩ…
‘የልጅነት አምሮት፥ አድገው ቢፈልጉት፣
አንዴ ፈቀቅ ካለ፥ የትም አያገኙት።’
ሆነና ነገሩ፣

አምሮቴን ፍለጋ፥ ልጅ መንደር ገብቼ፣
የኔን ዓይነት ምኞት፥ ያለው ልጅ አግኝቼ፣
አምሮቱን ልቅረፈው፥ ብዬ ተመኝቼ፣
ከራሴ ሰስቼ፥ ለእሱ ግን አብዝቼ፣
ስለግስ ብታዩኝ፥ በጣም ተደስቼ፣
ደግ ሆኜ አይደለም፤
ከራሴ አስበልጬ ለሰው የምሳሳ፣
ድውይ ልጅነቴን፣
ላክመው ብዬ‘ነው፥ ብወድቅም፣ ብነሳ!

(ታኅሣሥ 23፣ 2008)

የቃላት ጥቃት ጠባሳው አይሽርም!

(ሕዳር 22፣ 2006)

ሰዎችን ለማድነቅ የምንጠቀምበት ቃል ‹ወንድ› ወይም ‹ወንዳታ› በሆነበት ማኅበረሰባዊ አስተሳሰብ የምትደነቅ ሴት ማብቀል ይከብዳል፡፡ የምትደነቅ ሴት ብትበቅል እንኳ የማኅበረሰቡ ውጤት ነው ማለት አይቻልም ባይ ነኝ፤ የግል ጥረቷ ውጤት ነው የምትሆነው!

ቋንቋ፣ አባባሎች እንዲሁም ተረትና ምሳሌዎች ማኅበረሰቡ አባላቱን የሚያሳድግበትን (nurture የሚያደርግበትን) መንገድ ያሳብቃሉ፡፡ ያልዘሩትን አናጭድም፤ ስለዚህ አጋጣሚውን ተጠቅመን ከቃላት አጠቃቀማችን ጀምሮ ራሳችንን መገምገም መጀመር ሲኖርብን ነው፡፡

ለመሆኑ የአማርኛ ተረትና ምሳሌዎቻችን ስለሴት ምን ይላሉ?

1. ሴት ሲበዛ ጎመን ጠነዛ
2. ሴትና ዶሮ ዱር ከሄዱ ቤታቸውን ይክዳሉ
3. ሴት ከወንድ፣ እህል ከሆድ
4. ሴት ለቤት፣ ወፍጮ ለዱቄት
5. ሴትና መሬት የማይችሉት የለም
6. ሴት ማገዶ ሲቸግራት ምሰሶ ትነቅላለች
7. ሴት በማጀት፣ ወንድ በችሎት
8. ሴት በጳጳስ፣ ኳደሬ በንጉሥ
9. ሴት ብታውቅ፣ በወንድ ያልቅ
10. ሴት ሲያፏጩላት፣ ያረሱላት ይመስላታል
11. ሴት አማት የመረዘው፣ ኮሶ ያነዘዘው
12. ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ፣ የት አለ ንግዱ
13. ሴት ከጠላች፣ በቅሎ ከበላች አመል አወጣች
14. ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም
15. ሴት ያመነ ጉም የዘገነ
16. ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም
17. ሴት ይወዷል ማጀት ያንጎዳጉዷል
18. ሴትና ቂስ ቀስ
19. ሴትና በቅሎ እንደገሪዋ ነው
20. ሴትና አህያ ዱላ ይወዳል
21. ሴትና ድመት ወደ ሞቀበት
22. ሴትና ድስት ወደ ማጀት

23. ሴትና ዶሮ ሳያብድ አይውልም
24. ሴትና ፈረስ እንደኩሬ ውሀ እያደር ማነስ
25. ሴትና ፈረስ የሰጡትን ይቀምስ
26. ነፍስ በፈጣሪዋ፣ ሴት ባሳዳሪዋ
27. ወጭትና ሴት ሲከናነቡ ይሻላል
28. ወንድ ልጅ ለፈረስ ሴት ልጅ ለበርኖስ
29. የመንገድ ዳር እሸት ባል የሌላት ሴት
30. ዝናብ ካልጣለ ሁሉ ቤት፣ እንግዳ ካልመጣ ሁሉ ሴት

ተረትና ምሳሌ፤ የእምነት-እውነት ነው!

ተረትና ምሳሌዎች እንደባሕላዊ እሴት ወይም ብልሐት (wisdom) የተለመደ ነው፡፡ በሙግት ለመርታት ብዙ ተረት መቻል በቂ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ተረትና ምሳሌዎች፣ ልክ እንደሌሎቹ ሁሉ የተገነቡት በተጠራቀመ የማኅበረሰብ የእምነት-እውነታ ላይ ነው፡፡ አሁን፣ አሁን ከከተማ እየተመናመኑ ቢሆንም በብዙኃኑ ገጠሬ እና ጥቂት በማይባሉ ከተሜዎችም ውስጥ ስር የሰደደ እምነት የተጣለባቸው አፍራሽ ተረቶች ናቸው፡፡ ደግነቱ፣ ተረት በተጠራቀመ ዕውቀት - ተረትም፣ በተረት ይተካል፡፡

ለተረትና ምሳሌዎቻችን ትንሽ ጥብቅና ለመቆም ያክል፣ እጅግ በጣም ጥቂት ቢሆኑም በሴቶች ዙሪያ ገንቢ የሆኑ ተረትና ምሳሌዎችም አሉን፡፡ እንደምሳሌ "ሴትና ጭስ መውጫ አያጣም" የሚለውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህንኑ ይዘው ይመስለኛል ብዙዎች "ሴት አይደለሽ እንዴ መላ አምጪ እንጂ!" የሚሉት - ተረት ምን ያህል የምር እንደሚወሰድ የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡ ተረትና ምሳሌዎች በጊዜ ብዛት በሰዎች ልቦና ውስጥ የእምነት-እውነት የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡

ማርክ ትዌይን ‹The Awful German Language› ባሰኘው ጽሑፉ "በስርዓተ ጾታ ጉዳይ እንደጀርመኖች አዳላጭ ቃል የለም" ይልና እንደምሳሌ በጀርመን ቋንቋ ዛፍ ወንድ ይሆንና ቅርንጫፎቹ ግን በሴት ይጠራሉ ይላል (ገጽ 16)፡፡ ማርክ ትዌይን ይህንን ያለው እኛን ስለማያውቀን ነው እንጂ አማርኛን ቢያውቅ ኖሮ ቢያንስ ለጀርመኖች ተፎካካሪ ያደርገን ነበር፡፡ በአማርኛችን ግዙፍ፣ ጠንካራ ነገሮች ጾታቸው ‹ወንድ› ነው፤ ትናንሽና እና ደካማ ግዑዝ ነገሮች ግን ‹አንቺ› እያልን ነው የምንጠራቸው፡፡ ምናልባት ከጀርመኖቹ የምንለየው ጾታ-አልባ ሥያሜ ስለሌለን ብቻ ነው፡፡ "የአበበ ቤት ትልቅ ነው፣" ወይም "የአበበ ቤት ትንሽ ነች፣" እንላለን እንጂ አናገላብጠውም፡፡ እዚህጋ በተገላቢጦሽ ይባል፣ አይባል የሚል መውጫ የሌለው ሙግት ውስጥ መግባት አልፈልግም፡፡ ነገር ግን አባባሉ የተፈጠረው

ከምን ዓይነት ማኅበራዊ እሳቤ ነው የሚለውን አውቀን እንግባበት ነው የምለው።

\- - -

ለያዥ ለገናዡ እንዳላስቸገረ፣
ማን ሊደፍረኝ ብሎ ሰርክ እንዳልፎከረ፣
እንደደፋር አውሬ ጮሆ እንዳላቅራራ፣
ዛሬስ አያ ጥይት፥ ብዕር አይቶ ፈራ።

(ታኅሣሥ 14፣ 2006)

፬ - ምርቃት

ቋንቋችንን እንታዘበው

(ነሐሴ 2፣ 2008)

፩. Independence, Freedom, Liberty
(ነጻነት የቱ ነው? የቱስ አይደለም?)

"ነጻነት ውስብስብ ነው" ብዬ ልጀምር። 'ነጻነት' የሚለውን የአማርኛ ቃል በተለምዶ ከላይ የዘረዘርኳቸውን ሦስቱንም የእንግሊዝኛ ቃላት ለመተርጎም እንጠቀምበታለን። ትርጉሙ ግን ሁሌም አጥጋቢ አይሆንም።

ቃላት ባብዛኛው ደረቅ አይደሉም ፅንሰ-ሐሳብ (concept) ያዝላሉ። የሆነ ፅንሰ-ሐሳብን የሚወክሉ ቃላቶች በሆነ ቋንቋ ውስጥ የሉም ማለት የዚያ ፅንሰ-ሐሳብ በቋንቋው ተናጋሪው ማኅበረሰብ ዘንድ እምብዛም አይታወቅም እንደ ማለት ነው። ፅንሰ-ሐሳቡን በቃላት ቀንብቦ ማስቀመጥ መቻልና ብዙኃን በየ'ለት ንግራቸው እንዲጠቀሙበት ማድረግ መቻል ቃሉን ከነፅንሰ-ሐሳቡ በማኅበረሰቡ ውስጥ ማስረፅ ማለት ነው። ይህንን ለማስረዳት ቀላሉ መንገድ የአየር ሁኔታን መግለጽ ነው። በረዶ (Ice) እና snow (የበረዶ ብናኝ እንበለው) ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤ በአማርኛ ግን የሚጠሩት በአንድ ሥም - በረዶ - ተብለው ነው። Frost (snow ወይም የበረዶ ብናኝ የለበሰ ተራራ) አመዳይ ይባላል። በአገራችን የሌለ በመሆኑ ሥሙ የውሰት እና እምብዛም የማይታወቅ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ (መዝ 147: 16) ከመገኘቱ በቀር ቃሉም፣ ሐሳቡም በማኅበረሰቦቻችን ዘንድ የሌለ ነገር ነው። Tornado የሚለው ቃል የአማርኛ አቻ የለውም፤ ምክንያቱም በሐሳብ ደረጃም እምብዛም አይታወቅም። ሩቅ ምሥራቃውያን በየጊዜው ለሚያጠቃቸው የነፋስ እና የማዕበል ዓይነት (ነፋስን ከነፋስ፣ ማዕበልን ከማዕበል) የሚለዩባቸው እልፍ ቃላት አሏቸው። የቃላት እና ሐሳብ ቁርኝት እንዲህ ይገለጻል።

ኢትዮጵያ ውስጥ 'ነጻነት' የሚለው ቃል እና ፅንሰ-ሐሳብ በአማርኛ ተናጋሪው ዘንድ እንዴት ነው እየታየ ያለው? መነባንቡ (rhetoric) ብቻ ነው ወይስ ግንዛቤውም አብሮት አለ? አብረን እንፈትሽ።

ምሳሌ ፩፦

A) Ethiopia is an independent country.
B) Zone 9 is an independent blogosphere.
C) She is an independent woman.

በሚሉት ሦስት ዓ/ነገሮች ውስጥ 'independent' የሚለው ቃል ሦስት ተለምዷዊ ትርጉሞች አሉት፣

ሀ) ኢትዮጵያ "ነጻ" አገር ናት።
ለ) ዞን ፱ "ነጻ" የጡመራ መድረክ ነው።
ሐ) እሷ "ነጻ" ሴት ናት።

ሦስቱ ቃላቶች በዐውድ (context) የተለያዩ ቢመስሉም በመሠረታቸው አንድ ናቸው። ሁሉም፣ "ማንም ላይ ጥገኛ ያልሆነ/ች" ወይም "ራሱ/ሷን የቻለ/ች" የሚለውን ሐሳብ ያዘሉ ናቸው። ነገርዬው በራስ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመስጠት ወይም በሌሎች ጉዳይ ላይ አቋም ለመያዝ የማንም ተፅዕኖ የሌለበት እንደማለት ነው። መቶ በመቶ ራስን መቻል ወይም ከሌሎች ተፅዕኖ መላቀቅ የሚባል ነገር አለ ብዬ ባላምንም የሌሎችን በራስ ጉዳይ ጣልቃ ገብነት በእጅጉ መቀነስ መቻልን "ራስን መቻል" ብለን ብንጠራው አይከፋኝም። በላይኞቹ ምሳሌዎች ላይ 'independence' ራስን መቻል ወይም ገለልተኛ የሚሉት ቃላቶች ሊተኩት ይችላሉ።

ምሳሌ ፪፦

Eritrea became an independent country since 1991.

በተለምዶ ሲተረጎም፣

ኤርትራ ከ1983 ጀምሮ ነጻ ወጥታለች (ነጻ አገር ሆናለች)።

ከላይ ያለው አተረጓጎም አስተዳደራዊ መገንጠልን (secession) እንደ ነጻነት መቁጠር ነው። ጎረቤቶቻችንን እየወሰድን ብንነጋገር እንኳ ደቡብ ሱዳን እና ኤርትራ እንደ "ራሱን የቻለ" አገር የደረሱበት ደረጃ ከነጻነት በስተቀር በሌላ ሥም ሊጠራ ይችላል። ነጻ ወጥቷል የሚለው ቃል ‹independent› የሚለውን ቃል አይገልጸውም ማለት ነው። በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያ 'ኢንዲፔንደንት' ሆና ቆይታ ሊሆን ይችላል። ይህንን ግን 'ነጻ' ቆይታ ነበር

ብሎ መተርጎም አሳሳች ይሆናል፤ አሊያም የአገሪቷን መንግሥት የመወሰን ነጻነት ብቻ ይወክላል ማለት ነው። ይህ ሁሉ፣ የነጻነት ትርጉም የተዛባ እንዲሆን ያደርግብናል።

ነጻነት (freedom) ~ "ያለምንም ክልከላ ወይም ዕቀባ የሚፈልጉትን የማድረግ፣ የመናገር ሥልጣን ወይም መብት ነው።" Independence ("ራስን–መቻል") ግን ለነጻነት ቅድመ ሁኔታ እንጂ ነጻነት ራሱ አይደለም። ኤርትራውያን የ‹ሪፈረንደሙ› ጊዜ 'ነጻነት' ወይስ 'ባርነት' የሚል ምርጫ ነበር የተሰጣቸው። ትክክለኛው ምርጫ 'መገንጠል' ወይስ 'አለመገንጠል' ብቻ ነበር ~ ራሱን የቻለ የራስ ገዝ አስተዳደር መፍጠር ወይም አለመፍጠር።

በአማርኛችን በጣም የተበደለው እና በባሕላችን እምብዛም የማይታወቀው፣ ቢታወቅም በወግ አጥባቂነታችን ተቀባይነት የማያገኝ የሚመስለኝ ቃል ደግሞ ‹liberty› ነው። የጉግል ተርጓሚ ሦስቱን ቃላቶች እንዲህ ይፈታቸዋል፦

Independence (ሦስት ተቀራራቢ ትርጉሞች አሉት) ~ the fact of being,

(1) free from outside control; not depending on another's authority. (ከውጭ አካል ቁጥጥር ነጻ መሆን፤ በሌሎች ትዕዛዝ ሥር አለመሆን፤ "ራስ-ገዝነት" እንበለው።)

(2) not depending on another for livelihood or subsistence. (ለኑሮ ሌሎች ላይ ጥገኛ አለመሆን፤ "ራስን-መቻል" እንበለው።)

(3) not connected with another or with each other; separate. (ከማንም ጋር ያልተነካካ፣ የተነጠለ፤ "ገለልተኝነት" እንበለው።) በዚህ መንገድ የቃላት አጠቃቀሙን ባበዛነው ቁጥር ፅንሰ-ሐሳቡን በውስጣችን የማስረፅ ዕድል ይኖረናል።

Freedom ~

the power or right to act, speak, or think as one wants without hindrance or restraint. (ያለምንም ክልከላ ወይም ዕቀባ የሚፈልጉትን የማድረግ፣ የመናገር ሥልጣን ወይም መብት፤ "ነጻነት" እንበለው።)

Liberty ~

(1) the state of being free within society from oppressive restrictions imposed by authority on one's way of life,

behavior, or political views. (በማኅበረሰቡ ውስጥ ሥልጣን ባለው አካል ተጭኖ በግለሰብ የኑሮ ዘዬ፣ ባሕሪ ወይም ፖለቲካዊ አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩዕቀባዎች ነጻ መሆን፤ "ግላዊ-ነጻነት" እንበለው:: /አንዳንዶች ‹አርነት› የሚለው ይተካዋል ይላሉ::)

(3) the power or scope to act as one pleases. (የአንድ ሰው እንደፈለገው የመሆን ልክ፤ "ግለኝነት" እንበለው::)

ሦስቱን የእንግሊዝኛ ቃላት በኦሮምኛ ከአማርኛ በተሻለ መረዳት ይቻል እንደሆነ ለማጣራት ሞክሬ ነበር:: ነገር ግን ኦሮምኛችንም ልክ እንዳማርኛችን ‹ነጻነት›ን የመረዳት ገደብ አለበት:: ከነዚህ ትርጉም እጥረቶች የምንረዳው ነገር ቢኖር ብዙ ኢትዮጵያውያን ነጻነትን በቅጡ ተረድተነው የማናነበንበው መሆኑን ነው:: እንዲሁ ሥሙ ደስ ስለሚል ብቻ 'ነጻነት'-'ነጻነት' እንላለን::

፪. Government, State (የቱ መንግሥት ነው? የትኛው አይደለም?)

ስለመብቶች እናውራ:: በተለይ ደግሞ ስለሰብኣዊ መብቶች:: ሰብኣዊ መብቶች በማንም የሚሰጡን አይደሉም:: በተፈጥሮ የምናገኛቸው ናቸው:: ይህንን መንግሥታት በሕግ ለማስከበር ቃል ይገባሉ:: መንግሥታት ይህንን ቃልኪዳናቸውን የሚገቡት መብቶቻችንን ሊጠብቁ እና ሊያስጠብቁ ነው፤ እኛ [ዜጎች] ደግሞ በምላሹ በሹመት ኃላፊነቶችን እንሰጣቸዋለን:: አምባገነኖች ግን ይህን መሠረታዊ የመንግሥት እና ዜጎች የግንኙነት መሥፈርት ስተው ራሳቸውን የመብት ሰጪ እና ነሺ አስመስለው ያቀርባሉ:: ይህንን ተገዢዎችም ሳይታወቃቸው ይቀበሉታል:: "መንግሥት የሰጠኝን መብቴን…" ሲባል እንሰማለን:: ዜጎች መብታቸውን መንግሥት እንደሰጣቸው ካሰቡ አለቀ፣ ደቀቀ:: ሊቀማቸው እንደሚችልም ያስባሉ:: ስጦታውን እንዳይቀማቸው በመፍራት ሰጥ-ለጥ ብለው ይገዙለታል፤ በእጅ አዙር መብታቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ ማለት ነው:: በነገራችን ላይ አምባገነኖች ዜጎች እንዳይቀሟቸው የሚፈሩትን መብት በመንጠቅ በዜጎቻቸው መብት ላይ ያላቸውን "ሥልጣን" በማሳየት የበለጠ ዜጎች እንዲግገዙ ያደርጋሉ እንጂ 'መብቴን እንዳይነጥቀኝ ብሎ ታዝዞልኛለች/ታዝዞልኛልና አልነጥቀውም' ብለው አያስቡላቸውም::

የቋንቋ አጠቃቀማችን የነገሮች አረዳዳችንን፣… የነገሮች አረዳዳችን ደግሞ አኗኗራችንን፣… አኗኗራችን ደግሞ የመንግሥታችንን ዓይነት ይወስናል::

በማኅበረሰባችን ዐሳብ ውስጥ መንግሥት የአገር መሪው (head of State) ነው። ትንሽ ሲያድግ ደግሞ መንግሥት ገዢው ፓርቲ ነው። አንዳንዴ በሌላ መንገድ ደግሞ በአገር እና በመንግሥት መካከል ያለው ልዩነት ይምታታል። በመንግሥት የተማረሩ ዜጎች የአገሪቱን ሥም እንኳን መስማት እስከመጠየፍ የሚደርሱት በመንግሥት፣ በሕዝቡ እና በአገሪቱ መካከል ያለው ልዩነት ሲምታታባቸው ነው። ችግሩ ከመንግሥቱ ይሁን ከአገረ-መንግሥቱ (ወደታች እንበይነዋለን) ወይም ከሕዝቡ/ከአገሩ ለመለየት የተቸገረ ሕዝብ/ልኂቅ እንደመገንጠል፣ እንደመሰደድ ያሉ መፍትሔዎችን ይመርጣል።

ይህንን ለመጻፍ የተገደድኩት የተለያዩ ሰዎች ‹መንግሥት› ወይም ‹ኢትዮጵያ› እያሉ ሲጽፉ እነዚህን (ከታች የምዘረዝራቸውን ልዩነቶች) ሳያጤኑ ይሆንና በተለይ ማንን ለማለት እንደፈለጉ ግራ የሚገባኝ ግዜ እየበረከተ ስለመጣ ነው። በአንድ ቋንቋ እያወራን መሆናችንን በመጠራጠር!

በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ‘Government’ (‹መንግሥት›) እና ‘State’ (አሁን አሁን ‹አገረ-መንግሥት› እየተባለ ያለው) ቃላት ‘መንግሥት’ በሚለው ቃል ነው በጥቅሉ የሚተረጎሙት። በፖለቲካዊ እሳቤ ግን እነኚህ ሁለቱ የተለያየ ትርጉም ነው ያላቸው። የጉግል ተርጓሚን ተውሰን ብያኔያቸውን እናጢን፣

Government (መንግሥት) ~

> “the group of people with the authority to govern a country or state.” (በግርድፉ፣ “አንድን አገር ለማስተዳደር/ለመምራት ሥልጣኑ ያላቸው ሰዎች ስብስብ”)

State (አገረ-መንግሥት) ~

> “a nation or territory considered as an organized political community under one government.” (በግርድፉ፣ “በአንድ መንግሥት ሥር የተዋቀረ የአንድ ‘ሕዝብ’ ወይም አካባቢ የፖለቲካ ማኅበረሰብ”)

የላይኛው ፍቺ መንግሥት (government) እና አገረ-መንግሥት (State) መካከል ያለውን ልዩነት ቁልጭ አድርጎ ለማስረዳት በቂ ነው። በምሳሌ ብንመለከተው፣ አሁን የኢትዮጵያ መንግሥት ሕወሓት/ኢሕአዴግ ነው። ቀደም ሲል ደርግ (ወታደራዊ ኮሚቴው) ነበር። መንግሥት ይቀያየራል። አገረ-መንግሥት ግን ከአንድ መንግሥት የበለጠ ዕድሜ አለው። ለምሳሌ የአሁኒቷ ኢትዮጵያ አገረ-መንግሥት ከዐፄ ምኒልክ ዘመነ-መንግሥት ጀምሮ በአንድ ዓይነት ካርታ (ከመጠነኛ የአጭር ወቅቶች ልዩነት ጋር) እስካሁን

አለ፡፡ ነገር ግን የተለያዩ መንግሥታት መጥተው ሲያልፉ የተለያየ አስተዳደር ተከትለዋል፡፡

አንዳንድ ሰዎች የኢትዮጵያን አገረ-መንግሥት ይቃወማሉ፡፡ ይህም ማለት ኢትዮጵያ አሁን ባላት ቅርፅ መቀጠል የለባትም እያሉ ነው ማለት ነው፡፡ ሌሎች የኢትዮጵያን መንግሥት ይቃወማሉ፤ እነዚህኞቹ ፀባቸው አገሪቱን ከሚያስተዳድሩት ቡድኖች ጋር ነው ማለት ነው፡፡ አገረ-መንግሥቱን እና መንግሥቱን በመቃወም መካከል ያለውን ልዩነት የማያስተውለው ብዙኃን ደግሞ በመሐል ቤት ከነፈሰው ጋር ይነፍሳል፡፡ ልዩነቱን የማይረዳ ብዙኃን እንደሌለ ለመረዳት ፅንሰ-ሐሳቦቹን ነጣጥለው የሚገልጹ ቃላት ብዙኃን የሚናገሯቸው የአማርኛ ወይም የኦሮምኛ ቋንቋዎች ውስጥ አለመኖራቸውን እንደማስረጃ ወስጄ ነው፡፡ በኦሮምኛ ‹mootummaa› የሚለው ቃል ሁለቱንም 'Government' እና 'State' የሚሉትን ቃላት ለመተርጎም ይውላል፡፡ (በነገራችን ላይ ተቋማት የማይፀኑልን አዲሱ መንግሥት ሲመጣ የአሮጌውን መንግሥት አሻራ ለማጥፋት የአገረ-መንግሥቱን ቅርፅ ድራሹን በማጥፋት ስለሚጀምር ነው፡፡ ምክንያቱም አገረ-መንግሥቱን ከመንግሥቱ ለይቶ አያየውም፡፡)

በአሁኒቷ ኢትዮጵያ ዘጠኝ የክልል አገረ-መንግሥታት እና አንድ የፌዴራል አገረ-መንግሥት አለ፡፡ ይህ የቅርፅ ጉዳይ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ፦

> ፩ኛ፣ እኛ በፌዴሬሽኑ ውስጥ መሆን አንፈልግም፣ ‹መነጠል› እንፈልጋለን የሚሉትም፤
>
> ፪ኛ፣ ፌዴሬሽኑ አያስፈልግም ማዕከላዊ አገረ-መንግሥት ይኑረን የሚሉትም፤
>
> ፫ኛ፣ የፌዴሬሽኑ አወቃቀር ላይ ችግር የለብንም ሥልጣን ክፍፍሉ እና አተገባበሩ ላይ እንጂ የሚሉትም፤
>
> ፬ኛ፣ ፌዴሬሽን መሆኑ ላይ ሳይሆን አወቃቀሩ ላይ ችግር አለብን የሚሉትም፤…

ሁሉም መንግሥትን ይቃወማሉ፡፡ ነገር ግን ምክንያታቸው አንድ አይደለም፡፡ አንዳንዶቹ አገረ-መንግሥቱንም ጭምር ነው የሚቃወሙት ነገር ግን ራሳቸውን ግልጽ ማድረጊያ ቋንቋ ስለሚያጥራቸው ሁሉም ቡድኖች ሳይግባቡ እንደተግባቡ ሆነው አብረው ይሠራሉ፡፡

፫. Nation, Country, State
(የትኛው ነው አገር? የትኛው አይደለም?)

ለዚህንኛው ንዑስ ርዕስ እንደመንደርደሪያ፣ ‹ፌሚኒዝምን› በተመለከተ ደጋግሞ የሚነሳ አንድ ክርክር ላስታውስ፡፡ ‹ፌሚኒዝም› በአጭሩ፣ በራሴ አተረጓጎም የሴቶች የዕኩልነት ንቅናቄ ነው፡፡ ንቅናቄው በተለይ በባሕል እና በቅርፅ ‹ወንዳዊ› የሆነውን ዓለም ለሴትም ዕኩል ዕድል (opportunity) እንዲሰጥ (‹ሴታዊ› የማድረግ ሳይሆን ‹ሴታዊ›ም) የማድረግ ዓለምዐቀፍ ንቅናቄ ነው፡፡ ነገር ግን አንዳንዶች "‹ፌሚኒዝም› ከምዕራባውያን የተጫነብን፣ ለአፍሪካውያን እንግዳ አስተሳሰብ ነው፤ ማስረጃውም ቃሉን የሚተካ ለምሳሌ አማርኛ የለም" የሚል ዓይነት "ሙግት" ነው፡፡ ተመሳሳይ ሙግቶች ‹ሊብራሊዝም›ን በተመለከተም ሲሰነዘር ሰምቻለሁ፡፡ ‹ፌሚኒዝም› ለአፍሪካ እንግዳ ሐሳብ ነው በሚለው ላይ አልስማማም፣ ነገር ግን ሐሳቡ እንግዳ ነው ለሚለው ተጨባጭ ማስረጃ ቢኖርም እንኳን ሙግቱ ቂላቂል ነው፤ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ዘመን አመጣሽ ‹ቴክኖሎጂዎች› (ራሱን ይሄን ቃል ጨምሮ) እንደ ዘመን አመጣሽ አስተሳሰቦች ሁሉ የአገር ውስጥ አቻ ቃል የላቸውም፡፡ ነገር ግን ከተቻለ የቴክኖሎጂዎቹን ሥራ የሚገልጽ ቃል ፈልገን እንጠቀማለን፣ ካልሆነ ደግሞ ከቴክኖሎጂዎቹ ጋር ተያይዞ የመጣውን የባዕድ አገር ቃል እየተጠቀምን እንቀጥላለን እንጂ ቴክኖሎጂው አፍሪካዊ አይደለም፣ ከምዕራብ የመጣ ነው ብለን ሳንጠቀምበት አንቀርም፡፡

ባሕል እና ሥልጣኔም እንዲሁ ነው፤ ከባዕድ አገራት (ባዕድ የሚለው አግላይ በመሆኑ ባልጠቀምበት እመርጥ ነበር) ሲመጡ ከትውፊታዊው ባሕላችን እና ሥልጣኔ የተሻለ ከሆነ እንኳን በዘመነ ሉላዊነት በጋርዮሽ ዘመንም ቢሆን ከመቀበል እና የራስን ከመጣል አንተርፍም፡፡ ቋንቋ ደግሞ የባሕል ዋና ቅንጣት ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋችን እና የቋንቋ ክኅሎታችን ዘመኑ መስጠት የሚችለውን ያህል እንዲረዳ እና እንዲያስረዳ የተቻለውን ያህል መለጠጥ አለበት፡፡

‹አገር› ስንል ምን ማለታችን ነው?

ቀደም ብዬ፣ "‹State› የሚለውንና ‹አገረ-መንግሥት› እያልን አሁን-አሁን የምንተረጉመውን ቃል ከ‹መንግሥት› የሰፋ ትርጉም ይሰጣል፤ ፅንሰ-ሐሳቡ ግን ለኢትዮጵያውያን እንግዳ ነው" ብዬ ነበር፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ቃሉ (‹State›) ‹መንግሥት› ከሚለው’ጋ ብቻ ሳይሆን የሚምታታው ‹አገር› ከሚለውም ጋር ነው፡፡ እንደሚመስለኝ ቃሉ ‹መንግሥት› የሚለውን በከፊል፣ ‹አገር› የሚለውንም በከፊል እንደሚገልጽ በመረዳቷ/ቱ ነው ‹አገረ-

መንግሥት› የሚለውን ጥምረ-ቃል መጀመሪያ የተጠቀመ/ች/በት ሰው የመረጠ/ች/ው፡፡ ‹country› የሚለው ቃል አገር፣ ‹nation› የሚለው ቃል ደግሞ ‹ሕዝብ› ተብለው በቀላሉ (በተለምዶ) ይተረጎማሉ፡፡ ነገር ግን ትርጉሞቹ እውን እያግባቡን ነው? ምሳሌ በማንሳት እንጀምር!

ዞን ፱ የበኩር የበይነመረብ ዘመቻውን ‹ሕገ-መንግሥቱ ይከበር!› በሚል ርዕስ ሲያደርግ የተጠቀመበት (እና ኋላ በአንዳንዶች ተቃውሞ ስለገጠመው፣ ሁሉን ዐቀፍ ለማድረግ ሲባል የተፋቀው) ዓ/ነገር ‹Our Nation is Ethiopia, Our Nationality is Ethiopian and We are the People of Ethiopia.› የሚል ነበር፡፡ በወቅቱ ትርጉሙን በአማርኛ ለማስቀመጥ አልሞከርንም ነበር፡፡ ምናልባት ብንሞክር ኖሮ እንዲህ የሚሆን ይመስለኛል ‹አገራችን ኢትዮጵያ፣ ዜግነታችን ኢትዮጵያዊ፣ እኛ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ነን›፡፡ ነገሩ ችግር ያለው አይመስልም፤ አንዳንድ የበይነመረብ ላይ የዘውግ-ብሔርተኝነት (ethno-nationalist) አራማጆች ግን በዚህ መንገድ አልተረዱንም ወይም ሊረዱን አልፈለጉም ነበር፡፡ ‹Ethiopia is not a nation; it is an empire› (‹ኢትዮጵያ ‹ብሔር› አደለችም፤ ግዛተ-ዐፄ ናት› እንደማለት) የሚል ነበር አንዱ አስተያየታቸው፡፡

“ኢትዮጵያ ‹ብሔር› አይደለችም፤ የ‹ብሔሮች› ስብስብ ነች” የሚለው አስተሳሰብ መንግሥታዊ ዕውቅና ያለው አባባል ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ስሌት ‹ብሔራዊ› መዝሙር፣ ‹ብሔራዊ ቡድን› እና ‹ብሔራዊ ደኅንነት› የሚባሉት ነገሮች ትርጉማቸው ምንድን ነው? ለመመለስ ያስቸግራል፡፡ ነው ወይስ ‹አገራዊ› እየተባሉ መተካት አለባቸው? “የኢትዮጵያ ብሔራዊ…” የሚባል ነገር ካለ ኢትዮጵያ “ብሔር” ናት የሚል ሐሳብ ውስጡ ያለ ይመስለኛል፡፡

“Nation-State” የሚል ፖለቲካዊ ቃል አለ፤ በቀላሉ ሲተረጎም ‹አንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦችን ያቀፈ አገረ-መንግሥት ማለት ነው›፤ ለምሳሌ እንግሊዝ ‹ኔሽን-ስቴት› ናት፡፡

በ dictionary.com ብያኔ መሠረት፦

Nation ~

> a large body of people, associated with a particular territory, that is sufficiently conscious of its unity to seek or to possess a government peculiarly its own. (‹ብሔር›፡ የራሳችን የሚሉት መንግሥት ያላቸው/የሚፈልጉ እና ኅብረታቸውን የሚያውቁ፣ በአንድ ግዛት ሥር የተሰባሰቡ ሕዝቦች ናቸው፡፡)

ወይም

the territory or country itself (ግዛት ወይም አገር)

Nation-state: a sovereign state inhabited by a relatively homogenous group of people who share a feeling of common nationality. (‹ብሔረ-መንግሥት›፡ የወል ብሔርተኝነት ስሜት በሚጋሩ አንፃራዊ ወጥ ማንነት ባላቸው ሕዝቦች የተመሠረተ ሉዓላዊ አገረ-መንግሥት)

Country ~
a state or nation (‹አገር›፡ አገረ-መንግሥት ወይም ብሔር)

ወይም

the territory of a nation (የአንድ ብሔር ግዛት)

ኢትዮጵያ የብሔረ-መንግሥታት ፌዴሬሽን ነች፤ ቢያንስ በሕግ ድንጋጌ መሠረት፡፡ ነገር ግን የደቡብ ክልልን እንደምሳሌ ብንወስድ ደግሞ ክልሉን ብሔረ-መንግሥት ብለን ለመጥራት ከላይ ከሰጠነው ብያኔ አንፃር መግባባት አንችልም፡፡ ‹ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት› የሚባል ነገር አለ/የለም የሚለው ጭቅጭቅ መቋጫ ሊያገኝ ያልቻለው ‹ብሔር› በሚለው ቃል ላይ መግባቢያ ላይ መድረስ ስላልቻልን ይመስለኛል፡፡ ‹ብሔርተኛ› የሚለው ቃል ያለው ትርጉም በራሱ አዎንታዊ ይሁን አሉታዊ መገመት እንኳን አልተቻለም፡፡

በኢትዮጵያ ያለው ችግር ‹ብሔር› (Nation) የሚለውን የመበየን አይደለም፡፡ ዘውግ (ethnicity)፣ አንድ የ‹ብሔር› ንዑስ ስብስብ ነው፡፡ ማለትም አንድ ብሔር ውስጥ ብዙ ዘውጎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ የዘውግን የፖለቲካ ትርጉም ስንመለከት ደግሞ በኢትዮጵያ በተለምዶ ‹ብሔር› የሚለውን ከምንበይንበት የተለየ አይደለም፡፡ ዘውግ በዋነኝነት በቋንቋ ላይ የተመሠረተ ነገር ግን በቋንቋ ብቻ ያልተወሰነ የሕዝቦች የወል ማንነት ነው፡፡ ይህ ትርጉም ኢትዮጵያ ውስጥ ‹ብሔር› እያልን የምንጠራቸው ቡድኖችን በትክክል ይገልጻቸዋል ወይ የሚለው አጠያያቂ ነው፡፡

ኦሮምኛ ሁለቱን ቃላት (ብሔር፡ saba; አገር: biyyaa) የተሻለ የሚገልጻቸው ይመስላል፡፡ አማርኛ የተዋሰው ቃል ‹ጎሳ›ም፣ ምንጩ ከዚያው ነው የተቀዳው፡፡ በኦሮምኛ ‹ጎሳ› የሚለውን ቃል፣ ዘውግ ከምንለው ጋር ዕኩያ ነው የሚሉ አሉ፤ ከዚያም አጥብበው በእንግሊዝኛ ‘tribe’ ከሚለው እና በዘር

ሐረግ ከሚቆጠረው ጋር የሚያመሳስሉት አሉ (በእርግጥም ይህንኛው ለእውነታው የቀረበ ይመስላል)። ‹ጎሳ› የምንለውን ቃል በነባራዊው ሁኔታ ‹ብሔር› የምንለውን ነው የሚተካው ‹ብሔር› እነዚህን ጎሳዎች ዐቀፏ ኢትዮጵያ ናት የሚሉ አሉ። የጎሳ ፌዴራሊዝም፣ የዘውግ ፌዴራሊዝም፣ የብሔር ፌዴራሊዝም እያልን በምንፈልገው ሥም በጠራነው ቁጥር ፌዴራሊዝሙም የተለያየ ትርጉም ያለው ፌዴራሊዝም ይሆናል ማለት ነው። ስንቃወመው ወይም ስንደግፈውም (እንደአጠራራችን/አተያያችን) የተለያየ ዓይነት ፌዴራሊዝም ነው የምንደግፈው ወይም የምንቃወመው ማለት ነው።

፬. Nationalism, Ethnocentrism, Racism (የትኛው ዘረኝነት ነው? የትኛው አይደለም?)

የኢትዮጵያ ፖለቲካ በብዙ አደናጋሪ ቃላት የታጨቀ ነው። 'Nationalist' (‹ብሔርተኛ›) የሚለውን ቃል በብዙ መልኩ መስማት የተለመደ ነው፤ አንዳንዴ አዎንታዊ ትርጉም ሲኖረው፣ ሌላ ጊዜ አሉታዊ ይሆናል። በሌላ በኩል በፊት፣ በፊት ‹ኢትዮጵያዊ› ኅብረት አራማጅ የሆነ ሰው ነበር ‹ብሔርተኛ› ተብሎ የሚጠራው፥ አሁን፣ አሁን ደግሞ የዘውግ ብሔርተኛው (ethnonationalist) ነው ‹ብሔርተኛ› የሚባለው።

በብሪታኒካ እንሳይክሎፒዲያ ብያኔ መሠረት፦
Nationalism ~

> ideology based on the premise that the individual's loyalty and devotion to the nation-state surpass other individual or group interests. (ብሔርተኝነት ~ አንድ ግለሰብ ለብሔረ መንግሥቱ ያለው ታማኝነት እና ቁርጠኝነት የግለሰብ ወይም የቡድን ፍላጎቶችን የሚያልፍበት ርዕዮተ ዓለም ነው።)

ወይም

> Nationalism, translated into world politics, implies the identification of the state or nation with the people–or at least the desirability of determining the extent of the state according to ethnographic principles. (ብሔርተኝነት ~ በፖለቲካ ቋንቋ ሲተረጎም - አገረ መንግሥትን ወይም አገርን በሕዝቡ መግለጽ፣ ወይም ደግሞ ቢያንስ አገረ መንግሥቱ በዘውጋዊ መሠረታዊ መርሖች እንዲገለጽ ያለ የፍላጎት መጠን ነው።)

Racism ~

any action, practice, or belief that reflects the racial worldview–the ideology that humans are divided into separate and exclusive biological entities called "races," that there is a causal link between inherited physical traits and traits of personality, intellect, morality, and other cultural behavioral features, and that some races are innately superior to others. (ዘረኝነት ~ ሰዎች የተለያዩ እና ግንኙነት የሌላቸው "ዝርያ" የምንላቸው፣ በዘር ሐረግ በሚወረሱ አካላዊ፣ ሰብኣዊ፣ ንቃተ ሕሊናዊ፣ ሞራላዊ እና ሌሎችም ባሕላዊ መገለጫዎች የሚለዩ እና አንዳንድ ዘሮች ከሌሎች የበለጡ ናቸው በሚል ርዕዮተዓለም ላይ የተመሠረተ ተግባር ወይም እምነትን የሚያንፀባርቅ ዓለማዊ በዘር ላይ የተመሠረተ ምልከታ ነው፡፡)

‹ብሔርተኝነት› እና ‹ዘረኝነት› የሚሉት ሁለቱ ትርጉሞች ስንመለከት፤ ‹ብሔርተኝነት› በአብዛኛው በፖለቲካ ፍላጎት የሚደነገግ ሲሆን፣ ዘረኝነት ተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ሆኖም፣ በኢትዮጵያችን የፖለቲካ ንግግር ውስጥ በዘውግ (ethnicity) ላይ የተመሠረተውን ማንነት ‹ዘር› እያሉ መጥራት የተለመደ ነው፡፡ የብሪታኒካ ኢንሳይክሎፔድያ በዘር እና ዘውግ መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚከተለው ነው የሚያስረዳው፦

"የዘውግ ማንነት እና መገለጫዎች በ[ማኅበራዊ] ትምህርት የሚገኝ ነገር ነው፡፡ ዘር ግን በደም የሚወረስ እና መለወጥ የማይቻል ነገር ነው ተብሎ የሚታመን ነው፡፡ የዘውግ ማንነት ጊዜያዊ እና ሥር የሰደደ ላይሆን ይችላል፡፡ ዘር ግን በተፈጥሯዊ እውነታዎች ላይ የተመሠረተ እና የማይቀየር እንደሆነ ነው የሚታመነው፡፡"

ይህ የዘውግ እና የዘር ልዩነት ነው የ'ethnocentrism' (ዘውገኝነት)ን ትክክለኛ ትርጉም እንድናገኝ የሚረዳን፡፡ በዚሁ መሠረት፣ ዘውገኝነት ማለት የአንድ ዘውግ ሕዝብ ባሕል ከሌላው ይበልጣል ብሎ ማሰብ ማለት ነው፤ ይህም ዘውገኝነት እንደዘውጋዊው ማንነት ጊዜያዊና ሥር ያልሰደደ ነው፡፡

ስለዚህ የሦስቱ ማለትም ብሔርተኝነት (Nationalism)፣ ዘውገኝነት (Ethnocentrism) እና ዘረኝነት (Racism) ልዩነት - የመጀመሪያው ፖለቲካዊ፣ ሁለተኛው ባሕላዊ፣ ሦስተኛው ተፈጥሯዊ የማንነት ብያኔዎች ላይ መሠረት በመጣላቸው የሚገኝ ነው፡፡ (ይህ እንግዲህ ብሔራዊ ማንነትን

ብቻ ሳይሆን በ‹ዘር› ላይ የተመሠረተውን ማንነት በራሱ “የለም” የሚል አቋም የሚያራምዱትን ምሁራን ሐሳባዊ ክርክር ሳናነሳ ከቀረን ነው።)

በኢትዮጵያ ‹ዘረኝነት› የሚለው ቃል በዘውግ ላይ የተመሠረተ ማበላለጥን ለመጥቀስ አገልግሎት ነው የሚውለው። ይሁን እንጂ፣ ብዙዎችን የሚያስማማው የዘር ትርጉም ተፈጥሮ ላይ የተንጠለጠለ ነው፤ የሚመሠረተውም “የቆዳ ቀለም፣ የፊት ቅርፅ እና የፀጉር ዓይነት ልዩነትን” በማስቀመጥ ነው። በኢትዮጵያ ደግሞ፣ ለምሳሌ በፖለቲካ ተቀናቃኝነታቸው የምናውቃቸውና ብዛታቸውን ብንደምራቸው ከ80 በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብን የሚወክሉትን ሦስቱን - የኦሮሚያ፣ የአማራ እና የትግራይ ክልል ሕዝቦች በሕግ ድንጋጌ ‹ብሔር› ተብለው ቢጠሩም በፖለቲካ ተዋስኦ ውስጥ እንደ‹ዘር› የሚቆጥሯቸው ብዙዎች ናቸው። ነገር ግን እነዚህን ሕዝቦች የቆዳ ቀለማቸውን፣ የፊት ቅርፅ እና የፀጉራቸውን ዓይነት አይቶ መለየት አይቻልም።

ስለዚህ በተለይ በአማርኛ ‹ዘረኝነት› የምንለው እና ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን በዘውገኛ ልኂቃን መካከል የሚነሳ ሽኩቻ ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ትክክለኛ አገላለጽ አይደለም ማለት ይቻላል። የኢትዮጵያው የማንነት ሽኩቻ ከዘረኝነት ይጠብባል፤ ዘውገኝነት ነው። ብሔርተኝነት ደግሞ የፖለቲካ ኅብረት ለመፍጠር ሲባል በግለሰቦች እና በግለሰቦች ስብስብ የሚገባ ቃል ኪዳን ነው ልንል እንችላለን። በዚህም ረገድ፣ በኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ያለው ነባራዊ ሁኔታ ጥቂት ብሔርተኝነት እና ብዙ ዘውገኝነት ነው ማለት ይቻላል። አሁን በተዋስኦዋችን ውስጥ የምንመለከተው ኢትዮጵያዊነትንም፣ ዘውጋዊነትንም ‹ብሔርተኝነት› እያሉ የመጥራት ድንግርግር የሚወለደው የፖለቲካዊ ቁርጠኝነታችን ለየትኛው ቡድን ነው የሚለውን ካለመመርመር ነው።

አባቴ…
የ‹ያ ትውልዱ› ጀግና፣
የ‹ያ ትውልዱ› ሳተና፣
ና እንጂ… ፌስቡክ ላይ እጨድ
የዘራኸውን ትውልድ፣
የእሳትነትክን አመድ፡፡
(ታኅሳስ 19፣ 2006)